# ትግላችን ዜና

በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር የተዘጋ

Prepared by the Ethiopian Students Union in Europe

Vol.2. No 4    P.O.Box 3198, 10364 Stockholm 3 SWEDEN

•ስለመሬት አዋጁ ከአኢተማ ሥ/አ/ኮሚቴ የተሰጠ መግለጫ

•የማን አርስት ለማን ?!

•የጦር ኃይሎች ደርግና የተራማጆች አቋም

•አንደገና ስለጊዜያዊ መንግስት

•ግንቦት 1፤/አሌአ/ የዓለም ዐቀፍ ወዛደር የትግል ቀን

•የኢንዶቻይና ሕዝቦች ድል

•ለጦር ኃይሎች ደርግ የተላከው ቴሌግራም

•ከብሪታንያ ቅ/ማህበር የደረሰን

ግንቦት፣1967    ሜይ –ጁን 1975

## የተራማጆች መገደል

ባለፈው መጋቢት ወር የ"ጊዜያዊ" ወታደራዊ መንግስት "ልዩ የጦር ፍርድ ቤት" መለስ ተክሌ፣ ረዘነ ኪዳኔ፣ ገደይ ገብረዋህድ በተባሉት ወጣት አገር ወዳዶች ላይ የሞት ቅጣት በመፍረዱ በጦር ኃይሎች ደርግ ተገለዋል:: ደርጉ እነዚህን ወጣት ተራማጆች ለመገደል የሰጠው ምክንያት "ቦንብ ወርውረዋል..." የሚል ነው::

ከአገር ቤት የደረሱን ዜናዎች ቦንቡ በአዲስ አበባ ማዘጋጃ ቤት ላይ በተወረወረበት ጊዜ ከተገደሉት አብዛኖዎቹ በከተማው ውስጥ እንዳልነበሩ ሁሉ ይናገራሉ:: ከሁሉም በላይ ግን በወጣቶቹ ላይ ምንም የተጨበጠ ማስረጃ እንዳልቀረበና ዴሞክራሲያዊ የፍርድ ችሎት እንዳልነበረ ያረጋግጣሉ::

በግፍ የተገደሉት እነዚህ ተራማጆች ረዥም የትግል ታሪክ ያላቸው ናቸው:: ገደይ ገብረዋህድ በተማሪ ንቅናቄ ውስጥ በዙ ጊዜ ሲተካረል ከመሆኑም በላይ ጥላሁን ግዛው በመራው የዩሶዋ ኩንግረስ አባል ነበር:: መለስ ተክሌም በተማሪ ንቅናቄ ውስጥ ባደረገው ተጋድሎ በኃይለ ሥላሴ መንግሥት እስር ቤት ከፍተኛ ሥቃይ የደረሰበት ታጋይ ነበር:: አብዮቱ በዚህ ዓመት እስከፈረሰበት ጊዜ ድረስ የስትራገል አዘጋጅ ነበር::

እነዚህ ወጣት ተራማጆች የኢትዮጵያ ረቮሉሽን ጠላቶች እንዳልነበሩ ግልጽ ነው:: "ረቮሉሽናዊ" ደርግና "ዴሞክራቲክ" ያልሆነ መንግስት በኢትዮጵያ ረቮሉሽን ስም ተራማጆችን ሊቀጣ አይችልም:: የጦር ኃይሎች ደርግ በነዚህ ተራማጆች ላይና በተቀሩትም የሕዝብ ወገኖች ላይ በሚፈጽማቸው ወንጀል የኢትዮጵያ ሕዝቦች እንደሚፋረዱት ግልጽ ነገር ነው::

የተራማጆች የነመለስ መገደል፣ የታሰሩት የሕዝብ ወገን የሆኑት የፖለቲካ እስረኞች እንዲፈቱ፣ ዴሞክራቲክ መብቶች ከሥራ ላይ እንዲውሉ ከደርጉ ጋር የምናደርገውን ትግል እንድናፋፍም የበለጠ የሚገፋፋን እንጂ፣ ደርጉ ምናልባትም እንደሚገምተው ከትግሉ ሜዳ የሚያስወጣን አይደለም::

የአውሮፓ ማህበር የመጽሄት ቦርድ የጦር ኃይሎች ደርግ የወሰደውን እርምጃ እያወገዘ፣ በዚሁ አጋጣሚ ለሟቾች ታጋዮች ቤተሰቦችና ጓደኞች የኀዘን ተካፋይነቱን ይገልጻል::

የሕዝብ ወገን የሆኑ የፖለቲካ እስረኞች ይፈቱ!
የደርጉ ፀረ ሕዝብ አዋጆች ይነሱ!
ተራማጆች በግፍ ለማይገደሉባት ኢትዮጵያ እንታገል!



## በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር የሥራ አስኪያጅ ኮሚቴ ስለመሬት ድልድል የተሰጠ መግለጫ

ፓሪስ 10/3/75

የኢትዮጵያን ጊዜያዊ ሁኔታ እየተከታተለን በአገራችን የሚካሄዱትን አበይት ጉዳዮች እያነሳን ሃሳባችንን በመግለፅ ቆይተናል:: የየካቲት የኢትዮጵያ ሕዝቦች አብዮታዊ እንቅስቃሴ ከጀመረበት ጊዜ ጀምሮ እስከ "ኢትዮጵያ ትቅደም" "ሶሻሊዝም" እርምጃ ድረስ የነበረውን ሁኔታ እንዴት እንደተመለከትነው ለአባል ማህበራት አስታውቀናል:: ወደፊትም በዚሁ አንፃር አዲስ ለሚፈጠሩ ሁኔታዎች ሁሉ አስተያየታችንን በመስጠት ወደኋላ አንልም::

በአገራችን ያለው አብዮታዊ እንቅስቃሴ ባላከተመበት ባሁኑ ጊዜ በኢትዮጵያ ለሚደረገው አብዮት መሰረታዊ ጥያቄ ነው ብለን የምናምነው "መሬት ላራሹ" በወታደራዊው መንግስት ታወጀ:: የካቲት 25 ቀን 1967 የወጣው አዲስ ዘመን "የገጠር መሬትን የመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ሆነ" በሚል ርዕስ ሥር አዋጁን እንዳለ አስፍሮአል :: አዋጁን የሚያብራሩ በርከት ያሉ መግለጫዎችም አብረው ወጥተዋል :: በየካቲት 26 ቀን 1967 የ"መሬት ላራሹን" አዋጅ በመደገፍ ቀትረ ወደ "ገባሽ ሚኒኛ" ሕዝብ የሚሄድ ተከልክሏል :: አዋጁም ከየካቲት /5 ቀን 1967 ዓ.ም. ጀምሮ እንደሚፀና ራሱን በቻለ አንቀጽ ቀርቧል ::

አዋጁ በሃገሪቱ የተለያዩ የመሬት ሥሪት የሚገኙባቸውን ቦታዎች ሁሉ ይመለከታል :: በበኩላችን የዚህን አዋጅ ታሪካዊነትና አዋጁም የከፈተውን የድል በር ከመናገራችን በፊት ከአዋጁ ጋር ጥያቄዎችና ይህ አዋጅ በወጣበት ጊዜ ወታደራዊው መንግሥት የሰጣቸውን መግለጫዎች ጭብጥ መጥቀስ ይኖርብናል ::

የአዋጁ ምዕራፍ ሁለት ፪ መሬት በግል ባለቤትነት የተያዙባቸውን ማለትም የደቡብ ክፍለ ሃገር የሚመለከት ነው :: በዚሁ ምዕራፍ አንቀጽ አራት "የግል ባለቤትነት ሥሪት ባለባቸው ክፍለ ሃገራት መሬት ለአራሹ በይዞታ ስለመስጠት" ይልና በቁጥር አንድ "ጾታ ሳይለይ ማንኛውም ለማረስ ፍቃደኛ የሆነ ሰው ለራሱና ለቤተሰቡ ኑሮ በቂ የሆነ መሬት በይዞታ ያገኛል" ይላል:: በአንቀጽ አራት ሥር የሚገኙት ቁጥሮች የሚገልጹት ለአራሾች እኩል የሆነ /ሩብ ጋሻ ወይም 10 ሄክታር/ መሬት ድልድል ስለማድረግ ነው :: አንቀጽ አምስት መሬትን መሸጥ መለወጥ የማውረስም ሆነ በወለድ አገድ ማስያዝ እንደማይቻል ይናገራል :: አንቀጽ ስድስት ቁጥር አንድ "በገበሬዎች ማህበር መሬት እስኪደላደል ድረስ ማንኛውም ጭሰኛ ወይም የቅጥር ገበሬ በሚያርሰው መሬት ላይ የይዞታ መብት ይኖረዋል ::

ሌላው ዋና ነጥብ በምዕራፍ ሶስት ሥር የሰፈረት የገበሬዎች ማህበርን ስለ ማቋቋም የሚመለከቱት አንቀጾች ናቸው ። በአዋጁ መሰረት በ20 ጋሻ መሬት ከለለ /800 ሄክታር/ ውስጥ አንድ የገበሬዎች ማህበር ይቋቋማል ። አንቀጽ ዘጠኝ ቁጥር አንድ እንደሚለው ከሆነ ፣ የገበሬዎች ማህበር አባል ለመሆን የሚችለው ጥሰኛ የነበረው መሬትና መተዳደሪያ የሌለው፣ ተቀጥሮ የሚሰራና የእርሻ ሠራተኛ፣ ከ10 ሄክታር /ሩብ ጋሻ/ ያልበለጠ መሬት የነበረው ባለርስት ነው ። በአንቀጽ አስር ደግሞ የገበሬዎች ተግባር ምን እንደሆነ በሰፊው ተተንትኗል ።

ከዋና ዋናዎቹ ተግባሮች ፣ ቁጥር አንድ ፣ በ20 ጋሻ ከለለ ውስጥ ያለውን መሬት አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ መንግስት ዐርዳታ እየተጠየቀ በተቻለ መጠን በእኩልነት በሚከተለው ቅደም ተከተል መሠረት ማደላደል ወዘተ ፣ ቁጥር ሰባት ፣ በክልሉ ውስጥ የሚገኘውን ማንኛውንም የሕዝብ ንብረት መጠበቅና ማስተዳደር በተለይም የእርሻ የውኃ የደን ሃብት መጠበቅና መቆጣጠር ፣ ቁጥር አራት ፣ በክልሉ ውስጥ የሚነሳውን ክርክር ለማየት የፍርድ ሸንጎ ማቋቋም ። እና ሌሎችም የህብረተ ሥራዎችን የሚመለከቱ ይገኙበታል ። በአንቀጽ አስራ አንድ ደግሞ በከፍተኛ ደረጃ የሚቋቋሙ የገበሬዎች ማህበር እንደሚኖር ያስረዳል ። እነዚህም በወረዳ ደረጃ ሲሆን በ20 ጋሻ መሬት ከለለ ውስጥ ከተቋቋሙት የገበሬ ማህበራት የተውጣጡ ይሆናሉ ።

የወል ስሬት ወይንም ቋርስት ሃገር መሬት ስሬት በሚገኝበት በሰሜኑ ክፍለ ሃገር የቀድሞውንም መሬት በተወላጁ የተያዘ የሚይዙት የሚይለወጥና እንደ ደቡብ ክፍለ ሃገር ጥሰኛ የሚይበዛበት በመሆኑ አሁን በመሬት ላይ የሚያርሱት አራሾቹም ሆኑ ጥሰኞች ይህ አዋጅ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የይዞታ መብት ይኖራቸዋል ። አንድ ነገር ቢኖር የወል እርስት በሚገኝበት ክፍለ ሃገር እንደ ቀደሞው በተወላጅነት ብቻ መሬት የሚያገኙ አንዳንድ መያዣዎች ተቀባይነት አለማግኘት እንደ አዋጁ አንቀጽ 23 መሠረት በወል እርስት የሚቋቋሙት የገበሬ ማህበራት ዋና ተግባር በገል ሃብትነት መሬት እንደተያዘ ባቸው እንደ ደቡብ ክፍለ ሃገር መሬት ለአራሹ ገበሬ ማከፋፈል ሳይሆን ፣ መሬት በህብረት እንዲታረስ ገበሬዎችን ማነሳሳትና ማደራጀት ይሆናል ።

የዘላን ሕዝቦችንም መሬት በሚመለከተውም የወል እርስት ሥሪት እንዳለበት ክፍለ ሃገር ዋናው የዘላን ህዝቦችን ለለማት በሚያስችል መንገድ ማህበር እንዲያቋቁሙ ማድረግ ነው ። አንቀጽ 26 እንደሚለው ፣ የህብረ ተግባር አዋጆች በግጦሽ አያያዝና በውሃ አጠቃቀም እንዲተባበሩ ማድረግ ይሆናል ።



መሬትን ለአራሹ ስለመስጠት በወጣው አዋጅ በምዕራፍ ስድስት ፣ ወቀሳሳ ድንጋጌዎች በሚለው አርእስት ስር ይህ አዋጅ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የገጠር መሬት የሚመለከቱ ክርክሮች በሙሉ ተከርዘዋል ፣ በተጨማሪም እንደሚለው ከሆነ ማንኛውም የመሬት ጉዳይ ለፍርድ ሸንጎ እንጂ ለፍርድ ቤት እንደማይቀርብ ይናገራል ።

የኢትዮጵያ ተማሪዎች አብዮታዊ ትግል መቀጠም የሆነው 'መሬት ላራሹ' ባለፉት 10 ዓመታት ይህንን መፈ ቃል በሰፊው አርሶ አደር ሕዝብ ውስጥ እንዲቀረጽና አርሶ አደሩ በአብዮታዊ ትግሉ ራሱ እንዲሰለፍ ጥሪውን ሲያስተጋቡት የኖሩት እውነተኛ ተራማጆች ሁሉ ዛሬ የዚህ አዋጅ መታወጅ የመጀመሪያው ድል እንደተገኘ መቁጠር ይችሉበታል ። ይህንን መፈ ቃል ሲያስተጋቡ በሰፊው ጭቁን ሕዝብ ለመብቱ ለነጻነቱ እንዲሰለፍ ለቀስቀስ አብዮታዊ ድምጻቸውን ከፍ አድርገው ሲያሰሙ ሕይወታቸውን ያሳለፉት ሁሉ ዛሬ ፣ በገና ተገደላችሁ እንጂ በከንቱ አልሞታችሁም ፣ ሊባላቸው የሚገባበት ቀን ነው ። ደግሞም ለመናገር የምንፈልገው የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበራት በዚህ አዋጅ ሊደሰቱ እንደሚገባና የ'መሬት ላራሹ' አዋጅ በፍጥነት ሥራ ላይ እንዲውል እንቅስቃሴያቸውን አጠንክረው እንዲታገሉ ነው ።

ዛሬ በወጣው የ'መሬት ላራሹ' አዋጅ የማይደሰቱ ፊውዳሎችና አምፒርያሊስቶችና ፍጹም ፀረ አብዮት የሆኑ ሃይሎች መሆናቸው አያጠራጥርም ። ስለዚህም ተራማጆች እውነተኛ አብዮታውያን ከምንጊዜውም የበለጠ ንቃታቸውንና ጥረታቸውን አስተባብረው ያለምንም ግደብና እንቅፋት አዋጁ ሥራ ላይ እንዲውልና አብዮታዊው ትግል ወደፊት እንዲገሰገስ ሃይላቸውን በፍጥነት ማቀረብ አለባቸው ። ይህ ማለት ሰፊው ሕዝብ እንዲደራጅ ፣ የፖለቲካ ንቃት ፍጹም አብዮታዊ እንዲሆንና ፊውዳሊዝምንና ኢምፔሪያሊዝምን ጨርሶ ለመምታት አስፈላጊው ዝግጅት እንዲደረግ በአሁኑ ተጨባጭ እርምጃዎች እንዲወሰዱ ወታደራዊውን ደርግ መገፋፋት አለብን ።

በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር የዚህን የ'መሬት ላራሹን' አዋጅ መውጣት ይደግፋል ። ይህ አዋጅ ሥራ ላይ እንዲውል ከሚታገሉ ሃይሎች ጋር ሁሉ ይተባበራል ። እንደሚታወቀው ሁሉ በጥር 7 1975 እኤአ ስለ ኢትዮጵያ ጉዳይ ሁኔታ በወጣው መግለጫ የ'ኢትዮጵያ ሶሻሊዝም' 'መሰረታዊ መመሪያዎች' የተባሉትን ለመቀበል ቀርበን ነበር ። መሬት ይዞታን በሚመለከተው በኩል ወደፊትነው የነበረው የተለያዩ የመሬት ስሪት በሚገኝበት ቦታዎች የገበሬ ማህበራት እንዲቋቋሙና ገበሬዎችም በመሬቱ ላይ የሚኖረውን ባለቤትነት በማህበሩ አማካይነት እንዲወስኑ የሚል ነበር ። ከዚህም ጋር አያይዞ ያቀረበው በሚቋቋሙት የገበሬ ማህበራት ውስጥ መደረግ የሚገባትን የፖለቲካ ቅስቀሳና ማደራጀትን ውስጥ

እንደነበር ይታወሳል ፡፡ የገበሬዎች ማህበር እንዲቋቋም የሚለውን አዋጅ እንደተለከተነው ከሆነ ለአራሹ ገበሬ የተወሰነለትን በራሱ ተከታታይነት በሚቋቋመው የገበሬዎች ማህበር እስኪታደል ድረስ በሚያርሰው መሬት የይዞታ መብት የሚኖረው መሆኑ በየክታውም እነዚሁ ማህበራቱ እንዲቋቋሙ መታወጁ ተጨማሪ ድል ነው እንላለን:: በሃገራችንም የሚካሄደው አብዮታዊ እንቅስቃሴ ወደ ህዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክና ቀጥሎም ወደ ሶሻሊዝም ለመሸጋገር የሚያስችለውን ዋናውን ሃይል ጨበጠ እንላለን:: ይህም አራሹ ገበሬ መሬቱን የራሱ የሚያደርገበት አዋጅ በሥራ ላይ በተሟላ ፍጻሜነት መዋል አለበት ፡፡ ይህም አብዮታዊ ትግል የሚከርበት በመሆኑ የገበረውን መደራጀትና መታጠቅን እንዲሁም የወዛደሩ መደብና የሌሎችንም ዲሞክራሲያዊ ሃይሎችና የህብረሰብ ክፍሎች የሚወከሉበት የፖለቲካ ድርጅቶች በነጻ የማቋቋም መብታቸው እንደከበር በአስቸኳይ ይጠይቃል ፡፡ ስለድርጅት አንገብጋቢነት የምንችለውን ያህል እስከምንጠለለበት ድረስ በ25 የካቲት '67 በወጣው አዋጅ ዘመን የወታደራዊውን መንግስት መግለጫዎች በመጠቀስ ስለ ሰፊው ሕዝብ መደራጀት ምን እንደሚታሰብ ለማየት እንሞሳለን ፡፡

• የገጠርን መሬት የሕዝብ ለማድረግ የወጣ አዋጅ መግለጫ • በሚለው አርእስቱ ሥር አዋጁ በሚገባ ሥራ ላይ እንዲውል መወሰድ የሚያስፈልጋቸው እርምጃዎች ለሚለው የሚከተለውን ያስፍራል ፡፡

• እንደዚሁ አዲስነትን መሰረታዊ የኢኮኖሚና የህብረተሰብ ለውጥ በሥራ ላይ ያዋሉ ሃገሮች ታሪክ እንደሚያሳየው ለውጡ ከመንግሥት በፊት ሕዝቡን አደራጅቶ ለለውጥ ንቁና ተከታታይና ተሰላፊ እንዲሆን የሚያደርግ የሕዝብ ድርጅት ማቋቋም ነበረባቸው ፡፡ ድርጅቱን ሳያቋቁሙ ለውጡን ለማምጣት የሞከሩ ሃገሮች ፍሬ ታቸውን ከግቡ ለማድረስ ብዙ መሰናከል አየገጠማቸው ዕቅዳቸው የሚከሽፍ መሆኑን መገንዘብ ይገባል:: እንደዚሁም በኢትዮጵያ ለተበዘበዘው ሕዝብ መብትና ጥቅም ተቆርቋሪና ተዋጊ የሆኑ ኢትዮጵያውያን ሁሉ ራሳቸውን አደራጅተው ሰፊውን ሕዝብ ለማደራጀትና ለለውጡ ለማዘጋጀት የሚችሉበት ሁኔታ ሊፈጠርላቸው ይገባል ፡፡ ይህ ካልሆነ ከላይ እንደተገለፀው ሕዝቡ የለውጡን ዓላማ ባለመረዳት የለውጥ ደጋፊዎችን በማገዝ ፈንታ አፈንግጦ ከተቃዋሚዎች ሊሰለፍ ይችላል ፡፡ •

እዚህ የጠቀስነው የማደራጀትና የመደራጀት ተግባር ለብዙ ዓመታት ማህበራችን ሲታገልለት የኖረ መሪ ሃሳብ ነው ፡፡ ሰፊው ሕዝብ ያለ ድርጅት ምንም እያገኝ እያለን ደጋግመን በንግግር ኖረናል ፡፡ አሁንም በዚሁ ጥቅስ ላይ የምንጠምረው ነገር ቢኖር እነዚህ መብቶች በተጨባጭ እርምጃዎች እንዲረጋገጡ ያስፈልጋል የሚለውን



ነው ፡፡

መሬትን ለአራሹ ለማደላደል የፊውዳሎችን መንበራት ፍጻሜ ለመስበር በተለይም አሁን ባለንበት የዓለም ሁኔታ የሰፊው ሕዝብ አብዮታዊ ትግል በውስጥና በውጭ የሚነሱበትን ፀረ አብዮት ሃይሎች ለመቋቋም በሰፊው ህዝብ ያገኛቸው ድሎች በአድሃሪያች ተመልሰው እንዳይነጠቁ ከተፈለገ ወታደራዊው መንግስት ከዲሞክራሲያዊ ሃይሎች ጋር ያለውን ቅራኔ በግልፅ መፍታት ይኖርበታል ፡፡ እነዚህም በዲሞክራሲ ሃይሎችና በደርጉ ማህል ካሉት ቅራኔዎች የዲሞክራሲና የሰብዓዊ መብቶች በድርጊት ያለመዋል ነውና ፣ በተለይም የኤርትራ ጉዳይ ዲሞክራሲያዊ መፍትሄ ካለተገኘለት ከፍ በለን የዘረዘርናቸው አብዮታዊ ተግባሮች በሥራ ሊዉሉ አይችሉም ፡፡ አብዮታዊው ትግልም አሁን ከደረሰበት ከፍተኛ ደረጃ በብዙ ዓመታት ወደኋላ ይመለሳል::

በአሁኑ ተጨባጭ ሁኔታ አብዮታውያን የሆኑ ሁሉ የ"መሬት ላራሹ" ሥራ ላይ መዋል ሊያስከትል ለሚችለው ሁኔታሁሉ መዘጋጀት አለባቸው ፡፡ የ"መሬት ላራሹ" በተግባር መዋል የሲቪል ጦርነት ሁሉ ሊያደርስ እንደሚችል ወታደራዊው መንግስት ይገምታል:: የካቲት 25 ቀን 1967 ዓ.ም. የወጣውን አዋጅ ዘመን እንደገና በገመለከት • የዐድገት በሕብረት የዘመቻ መምሪያ ባዘጋጀው ሴሚናር ላይ ተገኝተው ለነበሩ የሴሚናሩ ተካፋዮችና የዘማቾች ተወካዮች የወታደራዊው መንግስት ተጠሪያቸ ቀዮለን ያስፈርነውን ይናገራሉ ፡፡

• ፦.......በዓለም የሶሻሊዝም ዐርምጃ ታሪክ ተደጋግሞ እንደታየው ሁሉ ድብቅና ገለጽ የሆነ የአድሃሪያን መከራዎች እንዳሉ በማገናዘም እጋጣሚ ከመጠቀም ወደኋላ እንደማይሉ፡መረዳትና ነቅተን መጠባበቅ ሕዝባዊ አብዮታችንን የማደናገርና ዘለቄታ ያለው እንዲሆን ያረጋግጥልናል ..... ስለሆነም ፣ ለብዙ ዘመናት የሰፊውን ሕዝብ በመጨቆንና በመበዝበዝ መሬቱን እንደ መሳሪያ የዘነተ ምንጭ የተጠቀሙበት ፊውዳል ከበርቴዎች ዛሬ መሬታቸው ሲወሰድባቸው ሰፊውን ሕዝብ ፊትለፊት ለመታገል እንደማይዘጋጁ መታወቅ አለበት ፡፡ ይህ ሁኔታ እራሱ አብዮታዊ ዘመቻችንን በበለተ መምራት እንደሚገባን ያስገነዝበናል ፡፡ በዚህን ወቅት እገሌ ደግ ነው እገሌ ግን አይደለም እያለን እራሳችንን ማታለልና መደለል የለበገም ጉዳዩ የመደብ ትግል በመሆኑ በመደብ ቋንቋ ዐረፍተ ይሉንታ የለም •

ማህበራችን ከላይ የተጠቀሰውን አንቀጽ ይደግፋል ፡፡ በአሁኑ ተጨባጭ ሁኔታም የምንለው ይኸው ቢሆን እርስ አደሩ ሕዝብ መሬት ባለቤት መብቱ የነፃነቱ ተከራካሪ ፍጻሜ አብዮታዊ እንዲሆን ከተፈለገ የዲሞክራሲ ሃይሎች አብዮታውያን

የወዘአደሩ ወደቡና የገበረው ወገኖች ተደራጅተው በሚቋቋሙት የገበሬ ማህበራት ውስጥ የፖለቲካ ሥራ የሚደምረበት ፣ የሚቋቋሙት የገበሬ ማህበራት በህብረሰብ ቾን የፖለቲካ የኢኮኖሚና የሶሺያል እንቅስቃሴያቸ በሙሉ ተከታታይነት እንዲኖራ ቸው ከሠራተኛው ከወታደሩም ከቀረው ተደራጅቶ ከሚቀርብ አብዮታዊ የህብረተሰብ ክፍሉሁሉ የሚይነጣጠል አብዮታዊ ድርሻ እንዲኖራቸው መደረግ አለበት ። አብ ዮታዊ ሃሳቦች እንዲስፋፉና እንዲዛመቱ በተለይም የቀበሌውና የማደራጀቱ ተግ ባር በበዙ ወቱ በሚቀጠሩ አብዮታውያን መሠረት ያለበት በመሆኑ እነሱን በቀ ሉ የሚረዋረ ለመፍጠር የሚችሉ የፖለቲካ ድርጅቶች በተሉ መመልያቸውንና ሰባና ቸውን ዘርገተውና ከፍተው ወቀረብ አሁንኑ ይኖርባቸዋል።

ወታደራዊው ደርግ አሁን በደብቅ ይምራቸውን የሚያበሙትን ነጻ ጋዜ ጦች እና ዲሞክራሲያዊ ፣ የሰፊው ህዝብ ድምጽና የመሰሉት ተመሳሳይው ሰፊውን ህዝብ ለአብዮቱ እንዲያዘጋጁ ቅ ወፍቀዱ ይኖርበታል። እናም በበኩላችን የሲቪል መርነት በአገሪቱ እንደሚመሰረት እንገምታለን ፣ የሲቪል መርነት ከተደረገ ደግሞ ሰፊው ጥቅን ህዝብ በፖለቲካ ፣ በድርጅትም በተጥቆ መገኘር መሳተፍ አለበት ። ይህ ከሆነ የሲቪል መርነት መምጣት አብዮታዊ ዱላን በለሚያስመር እንረቀዳለን። ነገር ግን ደርጉ ከላይ በመቀስነው አኳን ዘመን የሲቪል መርነት መምጣትን ብቻ ቢናገርና ሰፊው ሕዝብ አሁኑኑ ለመዘጋጀት እንዲችል ተጨባጭ እርምጃዎችን ካልወ ሰደ ፣ በተለይም አፋን አሳሳቡና በአሁኑ ጊዜ አሳሳቢ የሆነው የኤርትራ ጉዳይ ዲሞክራሲያዊ ምፍትሄ እንዲገኝለት ካላደረገ ደርጉ በየጊዜው የሚያነሳው "ያለ ፈው የጨለማ ዘመን" በባሰ ሁኔታ እንደሚመለስ መገመት ይኖርበታል ።

በአውሮፖ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር የሥራ አሥኪያጅ ኮሚቴ ገምቶ ደርጉ በኤርትራ ነጻ አወጪ ግንባሮች ውስጥ ለተሰማሩት የነፃነት ተዋጊዎች ቀ ጥተኛ ጥሪ ማድረግ አለበት ። ይህም ማለት ባለፉት 13 ዓመታት የተደረገው የኤርትራ ሕዝቦች ወረራ ተግል አብዮታዊ እንደሆነና የኤርትራም ሕዝቦች የራሳ ቸውን የወደፊት ዕድል በራሳቸው ለመወሰንና እስከመገንጠል ድረስ ያላቸውን መብ ት ማወቅ ይኖርበታል ። በነፃነት ተግሉ ውስጥ የተሰማሩትን የኤርትራ አብዮታ ውያን ድምፅ መስማት መጀመር ያስፈልጋል ።

ከአሁንም ወዲያ ያለው ዕድል ከእነሱ አብዮታውያን ጋር የሰላም ድ ርድር ለመጀመር የሚያስችለን መንገድ መፈለግ ብቻ ነው ።



ባለንበት ሁኔታ ለደርጉም ሆነ በደርጉ አካባቢ ላሉ ዲሞክራቶችም ሆነ ተራማጆች የሰፊው ህዝብ ወገን የመሆን ዕድል ገና አላከተመም በተለይ የኤርት ራ ጉዳይ ዲሞክራሲያዊ መፍትሄ እንዲገኝለት በአፋጣኝ አብዮታዊ ተግሉ በፊውዳሊ ዝምና በኢምፔሪያሊዝም ላይ ብቻ ለመታ የሚችለበት አቅጣጫ ከአብዮታውያን እንዲ ቀርብ ማድረግ አለባቸው ። ይህም የተደራጀና የታጠቀ የሕዝብ ትግል እንዲኖር ማለት ነውና ከላይ በመቀስነው ጊዜያ የሰረረትን እናም ያቀረብናቸውን ነጥቦች በተሉ በሥራ ላይ እንዲውሉ ደርጉን መጎተት ያስፈልጋል ማለት ነው ።

- መሬት ላራሹን አዋጅ እንደግፋለን!
- በሥራ ላይ እንዲውል እንጠይቃለን!
- ዲሞክራሲያዊ መብቶች በአስቸኳይ በሥራ ላይ እንዲውሉ!
- ፊውዳሊዝምና ኢምፔሪያሊዝም ይውደሙ!
- ሰፊው ሕዝብ ያሸንፋል!

## የማን እርስት ለማን?

የዛሬ አሥር ዓመት የመሬት ጥያቄ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ንቅናቄ የተከፈለበት፤ የተራማጅ ክንፍ የቀኙን ክንፍ አሸንፎ ሪፎርሚስቱን 'የመሬት ላራሹ' መሪ ቃል በትግሉ ሰንደቅ ላይ ያሰፈረበት ጊዜ ነበር::ከዚያን ወዲህ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ንቅናቄ በዚሁ አብዮታዊ መሪ ቃል ስር ባለመታከትና በቆራጥነት ሲታገል ቆይቷል::ታላቅ መስዋእትነት አሳይቷል::ለዚሁ የተቀደሰ ዓላማ ሲታገሉ ሕይወታቸውን ያጡ፤ይህ ነው የሚደገል ፋሺስታዊ ገፍ የተፈጸመባቸው እያሉ ናቸው::እነዚህ ወጣት ጀግኖች በኢትዮጵያ የነፃነት ትግል ታሪክ ውስጥ ሕያው ሆነው ይኖራሉ::በደማቸው የተነከረውን የሬፎርሚስን ባንዲራ ሪፎርሚስቱ የተማሪ ንቅናቄ ክንፍ አንግቦ እነዚህ ታጋዮች በጀግንነት ለወደቁለት ዓላማ እስከመጨረሻው ለመታገል ተነስቷል::ለዚህም የአወርጃ ማህበር ሪፎርሚስቱ ትግል ጥሩ ምስክር ነው::

ነገር ግን ምን ይሆናል፤የተማሪ ንቅናቄያችን ይህን መሪ ቃል ባነሳ ባሰር ዓመቱ ዛሬ በመሃላችን ያሉ የፀረ ሪፎርሚስ ኃይሎች የታሪክን ወደፊት እርምጃ ለመ .ለስ በሚያደርጉት ከንቱ ጥረት በመሬት ጥያቄ ላይ ያለንን አብዮታዊ አቋም ለመከለስ የሚደገለበጡት ጠብ የለም::የዛሬ አሥር ዓመት የነበረው የንቅናቄያችን የቀኝ ክንፍ መሬት ላራሹ የሚለውን መሪ ቃል የተቃወመው በገሃድ ነበር::የዛሬዎቹ ግን በተሸፈነ መንገድ ነው የተራማጅ ለምድ በመልበስ ያንኑ ግብ በማሳደድ ላይ ናቸው::እንደበፊቱ ሁሉ ዛሬም የነዚህ ሪፎርሚስቶች የንቅናቄያችን ክንፍ ይህን ፀረሪፎርሚስቱ ገበሬውን እንደሚያከሽፍባቸው ምንም ጥርጥር የለውም::

በዚህ ዓመት በመሬት ጥያቄ ላይ ያለንን አብዮታዊ አቋም ለማደናቀፍ የሚደረገው አድሃሪ ዘመቻ የተቀደሰው በኢሕአፓ መሪዎች ነው::እንደሚታወሰው የኢሕአፓ ማእከላዊ ኮሚቴ በዚሁ ዓመት የሀዳር ወር ባወጣው መጽሄቱ/ኮምባት/ ለአርሶ አደሩ መሬት ይሰጠው፤አይሰጠው ምንም ለውጥ አያመጣም በማለት ተራማጆችን ለመሸንገል ሞክሮ ነበር:: እንደጻፈተም:

"AS regards Land Reform,what Lenin called the 'Prussian-way' or 'the American way' of Land Reform might be proposed.IN either case the peasant will suffer."(Combat,p.24)

እዚህ ላይ 'ፕሩሺያን ዌይ'ና 'አሜሪካን ዌይ' የሚባሉት ሀረጎች ምን ማለት እንደሆኑ ማብራሪያ ሳይሰጥ አይቀርም::በነዚሁ ሀረጎች ተጠቅሞ የተለያዩ የመሬት ሥሪት ለውጦችን የገለፀው ሌኒን ነበር::'ፕሩሺያን ዌይ' የሚባለው ባለመሬቶች ሳይወረሱ



ጭሰኛው ከበርነት ሳይለቀቁ የሚደረግ አድሃሪ የመሬት ስሪት ለውጥ ነው::'አሜሪካን ዌይ' የሚባለው ደግሞ ባለመሬቶች በአፈና ገፊው አብዮታዊ እርምጃ ተደምስሰው መሬት ላራሹ የሚለው መሪ ቃል ሥራ ላይ የሚውልበት የመሬት ሥሪት ለውጥ ነው::እንግዲህ ከላይ የጠቀስነው የኢሕአፓ መሪዎች አባባል እንደገና ብንመለከት የመሬት ጥያቄ በአድሃሪ መንገድ ይፈታ/ፕሩሺያን ዌይ/፤ወይም በጭሰኛው ሪፎርሚስቱ ኃይል ይፈታ /አሜሪካን ዌይ/ ለነኢሕአፓ መሪዎች ያው ነው::ነገር ግን፤የአርሶአደሩን ነቀቶ ከገባተኞች መሬት መንጠቅ የሚደፈለግ ኃይሎች ያው ነው ይበሉ እንጂ፤በ'አሜሪካን ዌይ' ና 'በፕሩሺያን ዌይ' መሃል ያለው ልዩነት በጨለማና በብርሃን መሃል ያለውን ልዩነት ያህል ነው::በአብዮትና በፀረ አብዮት መሃል ያለ ልዩነት ነው::<u>አብዮታዊው መንገድ</u> ጭሰኛው ገበተኞችን ነቅቶ ተደራጅቶ መሬት በመንጠቅ ሲደመስሳቸው ነው/አሜሪካን ዌይ/: <u>የፀረ አብዮቱ ጉዳና</u> ደግሞ ጭሰኛው ከገበተኛው የጭቆና ቀንበር መላቀቅ ሲያቅተው የሚደረገው ለውጥ የገበተኛውንጥቅም ሲያስጠብቅ ነው/ፕሩሺያን ዌይ/::በመጀመሪያው መንገድ አርሶ አደሩ ነፃነትን ይቀዳጃል፤የኑሮው ሁኔታ በጣም ይሻሻላል፤የጠቀላላው ሕብረተሰብ እድገት ይፋጠናል::በሁለተኛው መንገድ ግን ጭሰኛው ከሥቃዩና ከረሃብ አይላቀቅም፤የጠቀላላው ሕብረተሰብ እድገትም የፊውዳሊስቶችን ጥቅም ለማስጠበቅ ሲባል ይታፈናል::ይህ ሁሉ ግን ለኢሕአፓ መሪዎች ያው ነው ታዲያ እስከናካቴው የአርሶአደሩ ትግል ስሜት እንደማይሰጣቸው፤'መሬት ላራሹ' የሚያምኑበትና የሚታገሉለት መሪ ቃል እንዳልሆነ ፍርጥርጥ አርገው መናገር ነዋ! ድብብቆሹ የት ለመድረስ ነው?

ለጭቁኑ አርሶ አደር ጉን የተሰለፈው ማህበራችን ግን የመሬት ሥሪት ለውጥ ሌኒን ባለው 'አሜሪካን ዌይ'/ማለት በአብዮታዊ ሪፎርሚስን ጉዳና/ እንዲፈጸም፤ አርሶ አደሩ በሪፎርሚስቱ አመጽ ባለቤቶችን መሬት እንዲነጥቅ ከማበረታታና በዚሁ ትግሉም አርሶ አደሩን ሙሉ በሙሉ ከመደገፍ ወደኋላ አይልም::አርሶ አደሩን ከባለመሬቶች መሬት መንጠቅህ ያው ነው መንሳትህ አይቀርም የሚሉት የኢሕአፓ መሪዎች ከማን ጋር እንደተሰለፉ መለየት አስቸጋሪ አይመስለኝም::

በቀርቡ በተደረገው የጀርመን ቀ/ማህበር ጉባዔ ላይ የፌዴሬሽን መሪዎች /ከየቦታው የመጡ ነበሩ/ የኢሕአፓን መሪዎች አድሃሪ አስተሳሰብ በበለጠ በመፍታ ያው በእጅ አዙር መሬት ላራሹ የሚለውን መሪ ቃል እንደማይቀበሉ አሳይተዋል::በቀጥታው በላቲን አዘጋጅ ቸርቦ በፀደቀላቸው ውሳኔ ላይ የሚከተለው ሰፍሯል::

'<u>ለዓም በገቢር ላይ ከዋለ</u> የገጠሩን ገጠር ከበርቴ መደብ እንደሚያስፋፋና የፋሺዝምን አገዛዝ መደብ የሆነውን ይህን የገጠር ከበርቴ መደብ ማስፋፋት ስለሆነ በዚህ በኩል ያለውን አደጋ ተራማጆችና ተማሪዎች ሕዝቡን እንዲያስጠነቅቁ ጥሪ ያደርጋል::'/ስርዝ፡ የተጨመረ/

ይህ በባበለ ፈጽሞ አይ[illegible] ም በላይ ከላይ አስቦታች ፀረ ሰይገበ
ነው:: ስለገጠር ከበርቴ ፊውዳ[illegible] ስርዓት ወደጎን ትተን ይህን ለማስረዳት እንሞክር
በመጀመሪያ ደረጃ መሬት ላራሹ የሚለው መሪ ቃል ሥራ ላይ በሚውልበት ጊዜ/
የደርጉ የመሬት አዋጅ መሬት ላራሹን የሚያፀድቅ ነው/ እያገኘን አራሹ^ገሉ^ መሬት አገ
ደሚያገኝና ከዚህም የተነሳ የኑሮ ሁኔታው በጣም እንደሚሻሻል ግልጽ ነገር ነው::
በዚሁ ሰበብም የአርባታ ኃይሎች ማደግ የጠቅላላውን ሕብረተሰብ እድገት ያስከትላል::
የመሬት ላራሹ መሪ ቃል ዋና ዓላማ የፊውዳሊዝም መደምሰስና የነፃ ገበሬ መደብ መፍ
ለቅ ነው:: ይህ ነፃ ገበሬ በአነስተኛ ከበርቴ አርባታ /ሲምፕል ኮሞዲቲ ፕሮ
ደክሽን/ የሚገተፈበና በኑሮው ጠባይ ገጠር ከበርቴ ይሆናል::እዚህ ላይ አርሶ አደሩ
ገጠር ከበርቴ ሊሆን ነው ይህ መሆን የለበትም እያሉ የሚጮሁ የመሬት ጥያቄን ፍቺ
ፈጽመው አለተረዱም ማለት ነው::የማናቸውም የመሬት ጥያቄን ይዞ የሚነሳ አብዮት ዋና
ይዘት በጉልተኞች እርስትነት ያለው መሬት ወደአርሶ አደሩ እጅ የማሸጋገር ጉዳይ
ነውና::ገበሬው አብዮቱ ውስጥ የሚገፈለው በጉልተኛ በዝበዛ ነፃ ለመውጣት፣መሬት ለማ
ግኘትና ኑሮውን ለማሻሻል ነው::ከታሪክ ለማየት እንደምንችለውም፣በሩሲያ፣በቻይና፣በቬ
የትናም ወዘተ.በባለመሬቶች መሬት ተነጥቆ ለአርሶ አደሩ ታድሏል::ከዚህም የተነሳ፣
ገበሬውን ገጠር ከበርቴ ያለማድረግ ተአምር በሌላ ወደገጠር ከበርቴነት መቀየሩ አለ
ቀረም::ገበሬው መሬት ሳያገኝ ይህ ሬጂሙን መደረግ አይቻልም::ስለዚህም ገበሬው ገጠር
ከበርቴ ይሆናል ብሎ መሬት ላራሹን መቃወም አስቂኝ ምክንያት ሰጥቶ የገበሬዎችን ነፃ
መውጣት መቃወም፣አገራዊ ሬጂሙን መቃወም^ነው^::ይህን "አደጋ" ፈርቶ ገበሬው ገጠር
ከበርቴ እንዳይሆን ማስጠንቀቂያችሁን የሚሰጧችሁ አርሶአደሩን በጭቆናነት ለማስቀረት
የሚፈልገው ባለመሬት ነው::የእነዚና መሪዎች በኢትዮጵያ ሕዝቦች ትግል ያው አገዛ ወጥ
ታችጊዜና^ነው^ አገዛ መሬት ከወሰደው የፋሽስት ዘዘጫ ትሆናለህ እያሉ የኢትዮጵያን ገበሬ
"ስታጠነቀቅ" ለማየት አገጋ ነበር::

ሁለተኛ ነገር፣የደርጉ የመሬት አዋጅ ፊውዳሊዝም ባይደመሰስ ሥራ ላይ ሊውል
አይችልም::ለአውነተኛ ተራማጆች በዚህ አዋጅ ሥራ ላይ መዋል የሚመጣው "አደጋ" ያ
የሚበቀትና የሚዘጋጅበት አዲሱ ዴሞክራቲክ ሬጂሙን ነው::ስለዚህም ይህን አዋጅ
ከሥራ ላይ ለማዋል የሚደረገውን ትግል እየደገፉ፣ከፖለቲካ ትግላቸው ጋር በማቀናጀ
በነዚሁ ትግሎች ውስጥ ገብተው ወዛደር አርሶአደር አንድነትን በመመስረት አዲሱን
ዴሞክራቲክ ሬጂሙን ለማምጣት ይታገላሉ::በሌላ አነጋገር አውነተኛ ተራማጆች የዚህን
አዋጅ ሥራ ላይ መዋልና አዲሱን ዴሞክራቲክ ሬጂሙን ነፃ ተለዉ ማየት የለባቸውም::



"አዋጁ ሥራ ላይ ከዋለ" ብሎ ጥያቄውን የሚያበቃ ዛሬ በኢትዮጵያ ካለው ፀረ
ፊውዳሊስት ትግል እራሱን ያገለለ መሆን አለበት::እዚህ ላይ ደርግ "ይህ አዋጅ
ሥራ ላይ ከዋለ አደጋ ይመጣል" ብሎ "የሚያስጠነቅቀን" ደግሞ፣ይህን 'አደጋ' ለመከ
ላከል አዋጁ ሥራ ላይ እንዳይውል ማድረግ እንዳለብን በተዘዋዋሪ ያገኘ መጋበዙ
ነውና፣ወደፊውዳሊዝም ጠቀለሉ የገባ ከሃዲ ነው::

ይህን የመሬት አዋጅ ሥራ ላይ መዋልና አዲሱን ዴሞክራቲክ ሬጂሙን ነፃ
ለን ማየት እንደሌለብን ከላይ ተናገርናል::ይህ የመሬት አዋጅ በአዲሱ ዴሞክራቲክ
ሬጂሙን ለማከይነት ሥራ ላይ ውሎ እንኳ አድርባዮች የሚሉት "የገበሬው ገጠር ከበ
ርቴ መሆን አደጋ" ፈጽሞ የሚቀር አይደለም::እርግጥ በወዛደር አርሶአደር አንድነት
ላይ የተመሰረተው መንግስት ከፊውዳሊስቶች ላይ በተነጠቀው መሬት ላይ ተሰብጣጥረው
በየገጠሩ የሚያደርሱት ገበሬዎች ማህበራት እያሉ በሕብረት እንዲያርሱና ይህም የሕብረት
እርሻ ቀስ በቀስ ወደሶሺያሊስት የሕብረት እርሻ እንዲዛወር ያደርጋል::ነገር ግን
ይህ ረዥም ያለ ጊዜ የሚወስድና በገበሬዎች ሙሉ ፈቃደኝነት ሥራ ላይ የሚውል በመሆኑ
በግል እርሻ ላይ የተሰማሩ ገበሬዎች ይኖራሉ_ ::ሶሺያሊስት ቻይና እንኳ ዓይነት
ገበሬዎች እስከዛሬ ድረስ ያሉትም ለዚሁ ነው::

ይህ አዋጅ፣የካፒታሊዝም አርባታ ኃይሎች እድገት ካፒታሊስት ስርዐተ ማህበር
ለማመንከር ሳይሆን ለሶሺያሊስት ስርዐተ ማህበር መሰረት መጣል እንዲሆን የሚቆጣጠረው
የወዛደሩ መደብ ሥልጣን ሳይይዝ ሥራ ላይ ሊውል ቻለ በለን በንነባ እንጂ፣ይህ አዋጅ
የሚያስፋፋው የገጠር ከበርቴውን መደብ አንዳልሆነ እናያለን::በአነስተኛ የከበርቴ አር
ባታ /ሲምፕል ስበል ፕሮደክሽን/ የሚመሰረተው የገበሬው እርሻ ከካፒታሊስት ውድድር/ኮም
ፒቲሽን/ የተነሳ መክሰሩ አይቀርም::ማለትም ትናንሽ እርሻዎች በትላልቅ የከበርቴ
እርሻዎች ይዋጣሉ፣እንዲሁም ይገደላሉ::በዚህም የካፒታሊስት አርባታ አስከ ሄደ በገዶ
በከፊል አና የሚይዙ የገጠር ከበርቴዎችን/ሌኒን ሩራል በርዦዋዚ ይላቸዋል::/በሌላ
በኩል ሰፊ የገጠር ወዛደር/ሩራል ፕሮሌታሪያት/ይፈጠራሉ::እንግዲህ የካፒታሊዝምን
እድገት የሚቆጣጠር በወዛደሩ የሚመራ መንግስት ሳይኖር ይህ መሬት ላራሹ ሥራ ላይ ቢ
ውል እንኳ "የፋሽስት ዘዘጫ" ገጠር ከበርቴ የሚያስፋፋ ሳይሆን የገጠረን ነዋሪ በቡ
ርዦዋና በፕሮሌታሪያት የሚከፋፍል ማለትም ፕሮሌታሪያትን የሚያስፋፋና ከበርቴዎች/ቡር
ዦዋ/ የሚፈጥር ሆኖ እናገኘዋለን::ይህ በመሬት ላራሹ ሥራ ላይ መዋል ለመጀመሪያ ጊ
የሚነሳው ገጠር ከበርቴ ጊዜያዊና በተገኘ ጊዜ ውስጥ በራሱ የሚጠፋ ነው::ወደሶሺያሊዝም
ያለመሸ አገራዊ ሬጂሙን በተደረገበት አገሮች ይህን ለማየት ይቻላል::

በሰበኛ ደረጃ ጉዑ ከበርቴው በኢትዮጵያ የፋሺዝም ተከካይ መደብ ነው የሚለውን ከአጼሱ ቅጥረቱ ሬጅሙን ጋር ተጣራሪ ሆነ ለዚያ የማንቀበለው በንሀ ገም የፋሺዝም አደጋ የሚለውን ከገዢ ወበደን በዚህም በኩል የሚያፍርሱት ተያዥ ያው እውነት ላይ የተ ረገዘ ባይሆን ወሬት ሳራኙን ለመያዝ የሚበጥ ሰበብ እንደሆነ ለመረዳት እንችላለን::በዓለም ታሪክ ውስጥ በመለከተ፤ፋሺዝም የተንበራራው እንግሬፅያን ሪፖሎችን ባለተደረገባቸው፤ማለት የደርጉ ወሬት አዋጅ ዓይነት ሥራ ላይ ባልዋለባቸው አገሮች ውስጥ ነው::ለምሳሌ ጀርመን፤ጣሊያን፤ጃፓን፤ስፓኝ፤ወዘተ::በሌላ በኩል ግን እንግሬፅያን ሪፖሎችን በተደረገባቸው አገሮች፤ወሬት ሳራኙ የሚለው ወሬ ያለ ሥራ ላይ ውሎ በዚሁ ባሉ የካበለፀ ገበሬ መደብ/ማለትም ጉዑ ከበርቴ/ የፈለቀባቸው እንደ አሜሪካና፤ፈረንሳይ እስካሁን ድረስ ፋሺዝም ነገሰ አያውቅም::እዚህ ላይ ለማ ባየት የምንፈልገው የፋሺዝምን መምጣት በሚያመቹት ነገሮች እንጂ በቀበሌ አበቶች ውስጥ የገጠር አበ ፀት /እንግሬፅያን ሪፖሎችን አለመደረግና በኪፒታሊስት ሕብረተሰብ ውስጥ የፊውዳሊዝም ርዝራዦች መገኘት መሆኑን ነው::ይህን ግንኙነት በሚገባ ያሳየው ለአያሌ ዓመታት ሪፖሎችን ሕብረት ተዋጊ ለኮሚኒስት የነበረው ገርጊ ዲ ሚትሮፍ ስለ ፋሺዝም በሚገለጸው መጽሀፍ ውስጥ ነው::

ይህ ስለሆነ ግን በፊርማዎችና በመግለጫ ውስጥ ፋሺዝም ለመጣ አይችልም ማለት አይደለም::የካፒታሊዝም እድገትና የወዛደሩ ትግል እስኪል ድረስ ይህ አደጋ አይወ ፋም::ሆኖም ደግሞ ኢትዮጵያ ውስጥ የፋሺዝም አደጋ ፈጽሞ አይኖርም ለማለት አይደለም::የምንለው በኢትዮጵያ ውስጥ የፋሺዝም አደጋ የሚኖረው <u>ይህ አዋጅ በሥራ ላይ የዋለ እንደሆነ ሳይሆን ሳይሠራ የሚቀር ሥራ ላይ ያልዋለ እንደሆነ ነው::</u>

የተማሪውን ንቅናቄ አደርባይ ክንፍ እንደ ባመቻሳይ በና ብረት አዋጁ ሥራ ላይ ከዋለ የፋሺዝም ቅጥጫ የሆነውን ጉዑ ከበርቴ የሚያበረታታ በሆነ አደጋ አለ የሚለው አነጋገር፤የተራማጆቹን ለምድ ለብሰውና፤ ገበሬዎቹ በመምሰል ወሬት ሳራኙን ለመያዝ የሚበጥ ሰበብ ነው::ለበፊው ግን በዚህ አስቂኝ ሰበብ ውስጥ የተደበቀውን መደብ ተቀምና ፀረ ሪፖሎችና ዊ እሳቤ በቀላሉ ለማየት ብዙ ጊዜ አይወስድብንም:: ነገር ግን በንቅናቄያችን ውስጥ ያሉ አድሃሪያን፤ፀረ ሕዝብ ሰዎች በሀገር ቤት በሚካሄደው እንቅስቃሴ ተቀምጠው የተመታባቸው ወገን/በገጠር እንደተጠቀው የኢትዮጵያ ገበሬ ወሬት የለሽ ሆኗል/ ይህን በፊበሽታው በሆነ መንገድ ወሬት ሳራኙን የሚያዝም መሰ መር በደገፉ አያበገርመንም::



ጊዜያዊው ወታደራዊ መንግስት ገጠሬት ሥሪት ማሻሻያ አዋጅ አውጥቷል:: የወሬትን ጥያቄ በመሰለ ከባድ ጉዳይ ላይ የወጣውን አዋጅ ተራማጆች እንዴት እንደሚመለከቱት በማያወላውል ሁኔታ ማመልከት ይገርባቸዋል::እና በበኩላችን እንዴት እንደ ምናየው በመጠኑም ቢሆን እንመለከተናለን::በመጀመሪያ ያህል፤ይህ አዋጅ በኢትዮጵያ ሕዝቦች የትግል ታሪክ ውስጥ አዲስ ምዕራፍ የከፈተና እንደበለፀው ሕዝብ ድል የሚቆጠር ነው:: የሕዝቡ ድል ነው ሊባል የሚችለውም ይህ አዋጅ ከደርጉ እንደምጽዋት ለሕዝቡ የተለገሰ ሳይሆን ባጠቃላይ የሰፊው ሕዝብና በተለይ የአርሶ አደሩ የረዥም ጊዜ መራራ ፀረባላባቶች ስርዐት ትግል ውጤት በመሆኑ ነው::ደርግም ይህን እርምጃ ለመውሰድ የበቃው በሕዝቡ ትግል ተገፋፍቶና ተገዶ እንደሆነ የሚያከራክር አይደለም::

ይህ አዋጅ የሰፊው ሕዝብ ድል ነው በምንልበት ጊዜ ሥራ ላይ የማዋሉ ጉዳይ ሌላ ጥያቄ መሆኑን ለማመልከት አንድ ምሳሌ እንስጥ::በ1973 የተፈረመው የቺሊ ተናም ድርድር በቬየትናም ሕዝብ ገናና የትግል ታሪክ ውስጥ ከፍተኛ ቦታ የሚይዘውና እንደታላቅ ድል የሚቆጠረው የአሜሪካን ኢምፔሪያሊስቶችና የሳይጎን አሻንጉሊቶች አነሡ የቬየትናምን ሕዝብ ትግል እንዲያውቁት ስለተገደዱ ነው:: የአሜሪካ ኢምፔሪያሊስቶችና የሳይጎን አሻንጉሊቶች አነሡ ውሉን ለመፈረም የደረሱት ሴራቸው ስለከሸፈባቸውና መወጊ መንገድ በማጣት በቬየትናም ሕዝብና በዓለም ተራማጅ ሃይሎች ትግል ተወጥረው ስለተያዙ ነበር::ምንም እንኳ የፓሪሱ ውል የተፈረመበት ቀለም ሳይደርቅ ኢምፔሪያሊስቶቹ በተ ሉያቸው ውሉን መጣስ በደምረም፤ውሉን ፈጽመው እንደማያከብሩትም ገለጸ ቢሆንም፤የፓሪሱ የሰላም ድርድር በሪፖሎችናቹያን ዘንድ እንደታላቅ ድል ይቆጠራል::ውሉን ለማስከበር የሚቻለው በቬየትናም ሕዝብ ጎታት ተጥቆና ትግል ብቻ እንደነበረ ጥያቄ ውስጥ አለገባም::

ኢትዮጵያ ውስጥ የታወጀው የወሬት አዋጅ በመለከት ደርጉ ስራ ላይ ያውለዋል አያውለውም የሚለው ከጥያቄ ውስጥ ሳይገባ እንደህዝብ ድል የምንቀበረው ለዚሁ ነው::እንደድል የሚቆጠረው በደረሰው የሕዝቡ ትግል ውጤት ስለሆነ ብቻ ሳይሆን <u>በይዘቱ</u> የኢትዮጵያ <u>በፊው አርሶ አደር ፀረ በለበት ትግል ተከበሮና ሲሆን በመቀበሉና የጌዶቹን መደብ</u> ... <u>ቁቀም የሚሰበር አዋጅ በመሆኑም ጭምር ነው</u>:ደር ፖርላማ ደቀ ርሱ ከነበረት አውሃሪ የወሬት ማሻሻያ ገበሬዎች ሆነ ከአንዳልካቸው ነዮ መጽሄዮ የሚለ የወም በዚህ መብረታዊ ይዘቱ ነው::

ይህ አዋጅ ሥራ ላይ በሚውልበት ጊዜ ፊውዳሊዝምን መንግር እንደሚ ቻል፤የፊውዳል መደቡንና የአከራዩ መብረቱን እንደሚደመስስ ምንም ጥርጥር የለውም::

እንዲያውም በቀርብ ለተመለከተው በ1917 በለሸቪኮች ሥልጣን ከወሰዱ በኋላ ከተደነገገው የመሬት ሥሪት ማሻሻያ ጋር በጣም ይመሳሰላል::በዚህ አኳያ ለአብዮታውያን ወሰረታዊ የሆኑት ጥያቄዎች ይህ አዋጅ በሥራ ላይ እንዴት ነው የሚውለው? ማንስ ነው ሥራ ላይ የሚያ ውለው? የሚሉት ናቸው::ለነዚሁ ጥያቄዎች ባጭር ባጭሩ መልስ ለመስጠት እንሞክራለን::

<u>የመሬት አዋጅ ሥራ ላይ የሚውለው እንዴት ነው?</u>

የመሬቱን አዋጅ ሥራ ላይ ለማዋል በሚፈለገበት ጊዜ በባላባታዊው ስርዐት ተጠቃሚ የሆኑ ሁሉ ጋር ግጭት እንደማይቀር ሳይታለም የተፈታ ነው::ገዢዎችና ነፍጠኞች ብቻ ሳይሆኑ የነዚሁ ቀኞ ተጋሪዎች እንደአገሬ ገዢዎች/ምስለኔዎች ወዘተ./ ደኞች፣ጠበቆች፣ጭቃ ሹሞች ወዘተ... የዚሁን አዋጅ ሥራ ላይ መዋል ከፋና መቃወማቸው አይቀርም::እንዲሁም ኢምፔሪያሊስቶች በር ከበርተው፣አብዮቱን የከፉ ሌሎች ከናሎችና በደርጉ ውስጥ ያሉ አድሃሪዎች ባላቸው ኃይል የዚሁን አዋጅ በረብሻና የመንገድ ሥራ ላይ መዋል ለማወናገና የማይመለሱ ናቸው::ስለዚህም ይህን አዋጅ በሚገባ ሥራ ላይ ለማዋል ከተፈለገ ሰፊው አርሶ አደር የገጠር አብዮቱን ጉዳና/አንገሬዎቹን ረብሻን/ መውሰድ አለበት::ገበሬው ታጥቆና ተደራጅቶ ጠላቶችን በአብዮታዊ እጁ አውልቆ ከባለመሬቶች መሬትን መንጠቅ አለበት::በሌላ ዓይነት መንገድ ይህ አዋጅ አሁን በያዘው ይዘት ሥራ ላይ ሊውል አይችልም::

እንግዲህ ይህ አዋጅ በሚገባ ሥራ ላይ ሊውል የሚችለው በገጠር አብዮት /አንገሬዎቹን ረብሻን/አማካይነት ብቻ ነው በሉናል::ከዚህም ላይ ተነስተን በፖለቲካና በኢኮኖሚ መሃል ያለውን ግንኙነት ስንመለከት፣የሕዝቡን ኢኮኖሚክ ኑሮ በመሠረቱ የሚቀይረው የገጠር አብዮት በፖለቲካ መድረክ ላይ ከሚደረገው አብዮታዊ ለውጥ ጋር የተያያዘ እንደሆነ እንረዳለን::መያያዝም አለበት::ማለትም፣በኢኮኖሚ ደረጃ የመሬት ሥሪት በአብዮታዊ መንገድ ሲቀየር፣እንበርትም በፖለቲካና አገዛዝ ሥርዐቱ በአብዮት መለወጥ አለበት::ይህን የበለጠ ለማብረዳት እንሞክር::ላይ እንደጠቀስነው አርሶ አደሩ የገጠር አብዮቱን ለማካሄድ የገዢዎች ስርዐት ተጠቃሚዎችን፣በተለይም ከገዢታዊው ስርዐት ጋር በሺህ ድሮች የተሳሰረውን የመንግስት ቢሮክራሲ መደምሰስ አለበት::ይህ ደግሞ የቀደሞውን አገዛዝ ሥርዐት መለወጥ ማለት ነው::በጠቅላይ ያለመሰረታዊ የፖለ ቲካ ለውጥ መሰረታዊ የሆነ የመሬት ሥሪት ለውጥ ሊኖር አይችልም::በተገላቢጦሽም፣እንዲሁ::ሁለቱም በቀርብ የተያያዙና አብረው የሚሄዱ የዲሞክራቲክ ረብሻን አካሎች ናቸው.



እንደኢትዮጵያ ባሉት አገሮች ከገጠር አብዮት ጋር የሚጣጣመው የፖለቲካ ሥርዐት አዲስ ዲሞክራሲ ነው::

ከላይ የዘረዘርነውን ከኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር ስናያይዘው፣ባሁኑ ጊዜ ገበሬው ተደራጅቶና ታጥቆ የገጠር አብዮትን ሲያካሂድ፣በፖለቲካ ደረጃም ለዲሞክራሲ የሚደረገው ትግል ይቀጥላል ማለት ነው::የገጠር አብዮቱ ወደፊት በሚገሰግስበት ጊዜ ከደርጉ ፀረ ዲሞክራቲክ አገዛዝ ጋር መጋጨቱ አይቀርም::ይህም አገዛዝ በሕዝቡ አብዮታዊ እጅ ተደምስሶ በእውነተኛ ሕዝባዊ መንግስት ሲተካ የገጠሩ አብዮት ድልን ተቀዳጅቶ ከፍጻሜ ይደርሳል::ለማጠቃለል ያህል፣የገጠር አብዮት የሚካሄደው በአዲስ ዲሞክራቲክ ረብሻን ጉዳና ላይ ነው::— የአዲሱ ዲሞክራቲክ ረብሻን አካል ነው:: የመሬቱን አዋጅ ሥራ ላይ ለማዋል መታገል፣አዲሱን ዲሞክራቲክ ረብሻን ለማምጣት መታገል ማለት ነው::

<u>አዋጁን ሥራ ላይ የሚያውለው —ለማዋል የሚችለው —ማን ነው</u>

የመሬት ሥሪት ማሻሻያ አዋጅ በሚገባ ሥራ ላይ ፣ ደርጉ እንዳሰበው ፣ በመንግሥት ቢሮክራሲ አማካኝነት ሊውል አይችልም :: እንዲያውም ያከሽፍዋል :: ፍጹም ሊሆን ፣ የአዋጁን መንፈስ የሚጻረር ፀረ አብዮታዊ አቅጣጫ ይሰጠዋል :: ይህ አካሄዱ አርሶ አደሩን ለመከፋፈልና መሬቱን ጥቂቶች ከአብዮታዊ ትግሉ ለመነጠል ብቻ ነው ሊበጅ የሚችለው :: ይህ መሬት አዋጅ በሚገባ በሥራ ላይ የሚውለው ፣ አርሶ አደሩ ተደራጅቶና በመሣሪያ ታጥቆ በሚደረገው ፀረ ገዢዎች አብዮታዊ ትግል ነው:— ይህንንም ለማከናወን የወዝአደሩ መሪነት ያስፈልገዋል :: ምክንያቱም ሌኒን እንደሚያስረዳው ገበሬው የሚያመርትበት ዘዴ አርሶ አደሩን በሚነጣጥለውና በሚበታትነው ፣ የአርሶ አደሩን ሀይል ለማስተባበርና ለማጠቃለል፣ እንዲሁም የትግል አቅጣጫውን ለማሳየት የወዝአደሩ መሪነት አስፈላጊ ነው :: ባጭሩ ፣ የመሬት አዋጅ ሥራ ላይ ሊውል የሚችለው አርሶ አደሩ በወዝ አደሩ መሪነት የሚያካሂደው የአዲሱ ዲሞክራቲክ አብዮት አካል በሆነው በገጠር አብዮት አማካኝነት ብቻ ነው ::

የገዢዎች መደብ ጥቅም ማስተጋባትን መረጡ የኢሠሰ መሪዎች ግን <u>የመሬቱን አዋጅ ታሪካዊ ፋይዳና ከኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ ተነስቶ ሊኖረው የሚችለውን ውጤቶች በመመርመርና ፣ በዚሁ ተጨባጭ ሁኔታ ላይ ተመርኩዞ አብዮታዊ ታክቲክን ከመጠቆም ይልቅ ፣</u> ይህን የተገኘውን ድል ፣ ማለት መሬቱን አዋጁ ፣ በማያለስ ባሁኑ ጊዜ የህዝቡን መታጠቅ በመቃወም የሚከተለውን ሲጽፉ እናገኛቸዋለን :—

"To stifle or diffuse the class struggle and mobilize the masses against national liberations wars, it was inevitable that the Junta will sooner or later attempt(??) the agrarian problem. Hence, on March 4/75 the nationalization of all rural lands was declared." (Emphasis and bracket ours)

ከዚህ አፈሣሪ አነጋገር ቢያንስ ሁለት መሠረታዊ ፀረ አብዮታዊ አስተሳሰቦችን ለማውጣት ይቻላል ::— 1ኛ/ የኢሕአፓ መሪዎች መሬት በራሱ ተነ አዋጁ እንደ ሕዝቡ መራራ ትግል ውጤት ሳይሆን ከላይ ማለት ከደርጉ እንደተሰነዘረ ስራ አድርገው ነው የሚመለከቱት :: በዚሁ አባባሉ ከገበሬዎች ጋር በመሰለፍ ደህን ታላቅ የህዝብ ድል ቢያወሩት አይገርመንም ፤ አፈሣሪነታቸውን የገቱትም ቢሆን በሌሎች ጥያቄዎች አይቶችና ፲ በበኩላችን ሰሞን እንደ ሕዝብ ድል እንደሚታይ ከፍ በለን ለማሳየት ሞክረናል ፲ በነገራችንላይ ፤ የራሱን ሃሳብ ከመደርደር ይልቅ የሃገር ቤት ጋዜጦች እንደሁ በለቀል እንዲያ በለቀል በማለት መከራከርን የሚመርጠው የኢሕአፓ ማእከላዊ ደርግ ፤ የሃገር ቤት ጋዜጦ ስለዚህ ጉዳይ ምን በለቀል በሉ ቢጠይቅ ፤ የሃገር ቤት ጋዜጦችና ተራማጅ ጋዜጠኞች እንደ 'ፍቅረ ራስያ' 'የበሬው ሕዝብ ድምፅ' 'አብዮትና 'ወዝ አደር' መሬት አዋጁን እንደ ሕዝብ ድል እንደቆጠረት በቀላሉ ለመረዳት በቻለ ነበር:: ገን ምን ይሆናል ፤ የኢሕአፓ መሪዎች የሀገር ቤት ጋዜጦች የሚሉትን በሙሉ እንደገፋለን ቢሉ እዚህም ላይ ያምኑ - ነው !

አርገጥ ሕዝቡ ነቀ ተ በተደረገ ትግል ደህን ድል እስኪያስከበረ ድረስ አፈሣሪ ሃይሎች ደህን አዋጁ የህዝቡን ትግል ለማሳከምና ለመስታተን እንደሚጠቀሙ ተ/በማና ቸውም የሕዝብ ድ ል ለመጠቀም እንደሚሞከሩት ሁሉ/ ሳይታለም የተፈታ ነው :: ነገር ገን ገና ለገና ሕዝቡ ካልተደራጀ አፈሣሪዎች በዚሁ መሬት አዋጁ መደብ ትግሉን ያዳፍናሉ በሉ መሬት አዋጁን መቃወም የገራ ካባ ለበሰ ለገበሬዎች መከራከር ነው ::

2ኛ/ የኢሕአፓ መሪዎች ባሁኑ ጊዜ የገበረውን መታጠቅ በመቃወም ፤ ደርጉ አርሶ አደሩን ካስታጠቀ በኋላ አንቀሳቃሴዎችን ለማጥፋት ማለት አርትራ ላይ ሕዝቡን ሊያዘምት ነው ይላሉ — ደህስ በገዘል የከደከር ነገበ የተም አያደርሳቸውም:: ባሁኑ ጊዜ ገበሬዎች በአምፐር ያለበቶች አርሳታ ሀይላቸውን በሚያደረጉበት ወቅት ፤ አርሶ አደሩን መሣሪያ ማስታጠቅ ከጊዜው ተቀዳሚ ተግባሮች አንዱ ነው :: በሌት ዕቶ ያ ተጨባጭ ሁኔታ የአርሶ አደሩ መታጠቅ በመደመራ ያ ደረጃ ላይ ሰው የሚችለው በአካባቢ ያለውንና ተቀዳሚ ጠላቱን ማለትም ገበሬውንና ነፍጠኛውን ለመቃምና ለመጣት



ነው እንጂ ጉዳ ያለውን ጥግ ጠላት ተቶ የራሱ ወገን በሆነ በኋላ አንቀሳቃሴዎች ላይ እንዲዘምት እንዳልሆነ ለማንም ግልጽ ነው : ሸፍታ በጥይቱ የሚቀልውን ገበሬ ሆነ በመቅለሉ ገበሬውን መደበ ለማጥፋት [illegible] አደሩ ፤ ከደርግም ሆነ ከደርጉ ውጭ ሊያገኝ የሚችለውን መሣሪያ አሹ ማስገባት አለበት!! ሆኖም ደርጉ የኤርትራ አንቀሳቃሴ ላይ በደበት ሚሊሻን ሕዝብ ለማዝመት እንደሚችል መገንዘብ አንለም :: ከዚህ ተነስተን የኢሕአፓ መሪዎች የሚሉትንም ማለት ደርጉ በመሬት አዋጁ አባቦ ሕዝቡን አርትራ ላይ ሊያዘምት ነው የሚለውን አባባል እንቢ በገ ቀጣሪቸው ፤ ተራማጆች ሕዝቡን፣ የሚሉት ደርጉ የሚሰጥህን መሣሪያ አትቀበል ሳይሆን ፤ ያገኘውን መሣሪያ አፈ ሙዝ ደርጉ ላይ እንዲያዞርበትና ከአርትራ ሕዝብ ጋር ያንዱነት ገንባር እንዲፈጥር ነው የሚቀስቀሱት:: የኢሕአፓ መሪዎች ገን በአርትራ አባቦ አርሶ አደሩ እንደይታጠቅ ነው የሚያገቱት :— ደህም ገበሬውን ለነፍጠኛው ለገበሬው አሳልፎ መስጠትና በጥይት ማስቀሳት እንደሆነ ይገነዘቡት !!— . ያለም በርዝቀ ለዉነት አየዘጋጀ ባለ ሕዝቡን ቢያስታጥቅ ፤ ሌኒን ስለጓጋይ ከርከር ከመሎ አፈሣሪዎች ጋር ሲከራከር እንዲህ በሉ ነበር ፤ —

"Today the imperialist bourgeoisie militarizes the youth as well as adults; tomorrow, it may begin militarising the women. Our attitude should be: All the better! Full speed ahead! For the faster we move, the nearer shall we be to the armed uprising against capitalism. How can Social-Democrats give way to fear of the militarisation of the youth, etc, if they have not forgotten the example of the Paris Commune?" (C.W.v23, p82)

የኢሕአፓ መሪዎች ሊሁኑ የሌሉ ዐዲያ ሁኔታ ይበቃል የሚሉ ያከታ ከዶ ሁኔታዎችንመረዳት እንደሚገለው የአበዮቱን ጉዳና የሚያ ነው ::በነገሩ አስተያየት መሠረታዊው የትግል ዘዴ የጀርሊያ ውጊያ ሳሆን /combat/ ባሁኑ ጊዜ የበሽለ ፀረ ነት የማስቀረስን ነገራቸውን እንደተቀዳሚ ተግባራቸው አድርገው ያቀርባሉ :: ሌቀላላ ፖለቲካቸው የበሬውን ሕዝብ ተቀቀ የሚፈራትና በነጻራዊ ደረጃ ለአፈሣሪዎች መጠናከር የርጊያ መንገድ የሚከፍት በሉሆነ መሬት አዋጁ ሆነ የበሬውን አርሶ አደር መታጠቅ ቢቃወሙ አዲስ ነገር አይደለም — ፈጽሞ አያስገርመንም ::

ከላይ እንደጠቀስነው ፤ መሬት አዋጁ ታላቅ ድል ቢሆን ፤ የሕዝቡ መታጠቅና መደራጀት ደህን ድል የሚያስከብር ዘዴ የበትናው ናቸው ::በሬው አርሶ

አደረ በየቦታው አብዮታዊ ድርጅቶችን በማቋቋም በነዚሁ አባባሉ መደራጀት አለበት :: አብዮታዊ ምሁራን በዚህ ለቀጣይ ተልዕኮ አስተዋፅዖ ማድረግ ይኖርባቸዋል ማለት ነው ፣ በዚሁ አኳያ በተለይ የገበሬዎችን መደራጀት በሚመለከተው በኩል ማህበራችን ፍጹም የማያወላውል አብዮታዊ አቋም አለው :: አንዳንዱ ተራማጆች ነን ባዮች እንደሚሉት የሠራተኛው መደራጀት ብቻ ሳይሆን ፣ የሁሉም ጭቁን መደቦች ለትግል መደራጀት በሙሉ ልቡና ሊደገፍ ይገባል :: የትግላችን ዜና ፣ የገበሬውን መደራጀት ጥያቄ ቢያነሳ ፣ የሚከተለውን የዛሬ አምስት ወር ጽፎ ነበር :-

"In Ethiopia,we find the peasantry being engaged in a bitter struggle against feudal overlords.Our attitude towards the peasants' struggle could not be condescending,we would not ignore it nor tell the peasantry to wait until it is organized by a future Marxist party.On the contrary,we will encourage the peasantry in its struggle,call upon it to get organized as to carry out the struggle more effectively and see it as our task to help promote the peasants' struggle in every way possible."(Tiglachin Zena No.2,Vol.2 p-34-5)

በተረፈ በዚሁ ጽሁፍ ውስጥ አርሶ አደሩ <u>በአብዮታዊ ቡድኖችና ማህበራት ውስጥ መደራጀት</u> እንደሚኖርበት ገልጸን ነበር :: በ14ኛው የኢ.ሕ.ተ.ፓ. የተላለፈውን አብዮታዊ ውሳኔ የተቃረነውን ይህ የድርጅት ጥሪ ፣ የተማሪ ገበሬዎችን ቀኝ ክንፍ ሲያራውጡዋቸው ኋላ ሲያስመዘግቡ ቆይቷል :: ገበሬው እንዴት ለብቻው መደራጀት አለበት ተላላቾሁ እያሉ በመደገፋት የኢዘና መሪዎችበአብዮታው ያለርጅ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር ላይ የቀኝ ዘመቻ ያካሄደው ነበር :- በነሱ አባባል :-

"The program of the working class will be comprehensive and for all oppressed people,based on the foundation of worker-peasant alliance.The peasant party has a programme whose principal provision is the agrarian problem.<u>How can the foundation of the revolutionbe constructed when revolutionaries organize both parties?</u>Would not this be self-contradictory?The peasantry cannot solve the agrarian problem without the leading role of the proletariat.The proletariat cannot make the revolution without the peasantry,the foundation of the revolution.<u>So how come revolutionaries are made to agitate for a contradictory aim which is mutually self-defeating?</u> Would one imagine Lenin agitating for both the Bolsheviks and the peasant party the socialist revolutionaries?"(Combat,79)



እንዲሁም ከላይ እንዳየነው የኢዘና መሪዎች እንደሚሉት ከሆነ ሀ/ አርሶ አደሩ ለብቻው መደራጀት የለበትም ለ/ እና ሌኒን ወዛደሩንና አርሶ አደሩን ለየብቻቸው እንዲደራጁ አላደረገም ነው :: አርሶ አደሩና ወዛደሩ ለየብቻቸው ለምን መደራጀት እንዳለባቸው ከዚህ በፊት በትግላችን ዜና ጥራዝ 2 ቁጥር 2 በዝርዝር ስላተደረደረ አንመለስበትም ፣ እና ሌኒን አርሶ አደሩና ወዛደሩ ለየብቻቸው እንዲደራጁ አላደረገም የሚለው ደግሞ ቀላል ያለ ሃሰትና አሳሳቢ የሆነ የታሪክ ቅለበጣ ነው :: ለምሳሌ በ1907 ገደማ በሩሲያ ቦልሼቪኮች አርሶ አደሩና ሌበራሉ ከቦርቱ በተከፋፈለበት ወቅት በሰርቪሰች ቦልሼቪኮች አርሶ አደር /ትሩዶቪኪ በሚባለው ቡድን የቀረቡት/ ከሊበራሉ ከቦርቱ ተለይቶ /ከግራ ከተባሉት/ ለብቻው እንዲደራጅ በሙሉ ሃይላቸው ወርዳት እንዳለባቸው ሌኒን በተደጋጋሚ አስገንዝቦ ነበር:: በተረፈ ሌኒን ባጠቃላይ በለአርሶ አደር መደራጀት ሲናገር ፣ የወዛደሩና የአርሶ አደሩ ጥቅም በመደብ ደረጃ የተለያየ በመሆኑ አርሶ አደር ለብቻው በቦልሼቪኮች መገሪብ መደራጀት እንዳለበት ከመግለጽ ቦዝኖ አያውቅም ::

በዚህ ጽሁፍ ለማየት እንደሚቻለው የኢዘና/ፌዴሬሽን መሪዎች በሌሎች ጥያቄዎች ላይ ያሳዩት አድሃሪነት እንዲቾው በመሬት ጥያቄ ላይም በነባራዊ ደረጃ ሆኖቸውን ቁርጠው የገለፁትን መደብ አፈ ቀላል ሆነው ተገኝተዋል ::"በተማሪ ገቅናቄ ውስጥ ባለው የሃይል አሰላለፍም ኢትዮጵያ ውስጥ በሚካሄደው አብዮት እንቅስቃሴ <u>ጥቅማቸው የተጠቃቸው ቀኝ አድሃሪዎች</u> /ርስት ያላ ቁጥር በፍር የለውም ፣ በተለይ ውጭ ባሉት ተማሪዎች መሃል/ በሙሉ በፌዴሬሽኑ ጥላስር መጠጊያ ቢያገኙም አይደገኑም :: ይህ ማህበራችን ውስጥ የሚካሄደው የጥራት ፕሮሰስ የገፋ ከኋላን ያጠነከረዋል እንጂ አያደከመውም ::

አውሮፓ የሚገኙ የፌዴሬሽን መሪዎች በበዛት በተገኙበት በቅርቡ በደርሶን በተደረገው የቀርንጪና ማህበር ስብሰባ ላይ አንዳንዱ የፌዴሬሽን ደጋፊዎች የነመስፍን ብሩ ፣ የደጂች ብር ሃይ መስቀል ደስታ ፣ ነጋ ተገኘ ወዘተ የትግል ስነዱን የሬሳቸው በማድረግ " የማን መሬት ለማን! " በማለት መፈክራቸው ይታወስና ፣ የነ ያውም የተማሪ ገቅናቄዎችን ክንፍ " መሬትስ አርም ናት ፣ አፈር ገፊው አይ ከገባች አትመለስም! " በማለት በማን ወገን እንደሆነ በማሳየት መለሱን ሰጥቷል :: እነዚህ ሁለት ስናጋዎች የኢትዮጵያ ተማሪዎች ገቅናቄ ውስጥ ያሉትን የሁለት መስመሮች ደዘት ቁልጭ አድርገው በሚያገለግሉ ፣ እዚህ ላይ መተቸት ትርፍ ነገር ይመስለናል — ይሁ የጭቁኑ በፊው ሕዝብ ነው

* መሬትስ አርም ናት፣ አፈር ገፊው አይ ከገባች አትመለስም

## የጦር ኃይሎች ደርግና የተራማጆች አቋም

ያለፈው የየካቲት ሬቮሉሽናዊ እንቅስቃሴ የቀድሞ ገዥ መደቦችን ከመንግስት ሥልጣን ሲየለ፣ሰፊው ሕዝብ ይህን ሥልጣን በቅ ለማስገባት ያልተዘጋጀና ያልተደራጀ ስለነበረ፣የኢትዮጵያ ወታደር በሕብረተሰቡ ውስጥ ባለው ቦታ ምክንያት በጦር ኃይሎች ደርግ መሪነት ሥልጣን ለመያዝ ችሏል፡፡ የጦር ኃይሎች ደርግ በነዚህ 11 ወራት የሥልጣን ዘመኑ ብዙ ተራምዷል፡፡ በየካቲት የፈነዳው የኢትዮጵያ ሕዝቦች ትግልም እንዲሁ፡፡

ያሁኑ የጦር ኃይሎች ደርግ የመንግስት ሥልጣን በቅ ያስገባው በ1 22 አንጋፋ ካቸው ከጠ/ሚኒስትር ነት እንዲወገዱ አድርጎ የቀድሞ ባለሥልጣኖችን ማሰር እንደ ቀጠለ ነው ለማለት ይቻላል፡፡ ያኔ ለነገሩ 'ታማኝነትን' መግለጫ ይህን እውነት አይቀይረውም፡፡ ለማገናዘብም በዚያኑ ሰሞን ሁሉ ከተቋረጠ የኢትዮጵያ ዲሞክራቲክ ኃይሎች ጋር ሆና ዲሞክራቲክ መብቶች ከሥራ ላይ እንዲውሉ ይጠይቅ ነበር፡፡ መስከረም ሁለት ንጉሡን ገለበጠ ሥልጣን በገሃዱ እንደያዘ፣እራሱ ከጥቂት ሳምንታት በፊት ያቀርባቸው የነበረትን ዲሞክራሲያዊ መብቶች የሚከለክል አዋጅ አወጣ፡፡ 'ኢትዮጵያ ትቅደም' በሚለው ጥፍን መፈክሩ ሥር ግን ስለእኩልነት፣ስለነፃነት ስለሰብአዊ መብት መለፈፉን አላቆመም ነበር፡፡ የቀሩ ከቀድሞዎቹ የገዥ መደብ አባሎች ከሁሉም በላዩን በሞት ቀጣ፡፡ ትንሽ ቆየት ብሎም 'ኢትዮጵያ ትቅደም' ለሚለው መመሪያው 'ኢትዮጵያን ሶሺያሊዝም' የሚል ስያሜ ሰጠ፡፡ ይህናውም እንደበፊቱ 'ኢትዮጵያ ትቅደም' ተራማጅ ይዘቶች ፀረ-ዲሞክራቲክ አንቀጾች ይገኙበታል፡፡ በኤርትራ ጥያቄ ከመጀመሪያውም ዲሞክራቲካዊ መፍትሄ ለመፈለግ ምንም ፍላጎት ካለማሳየቱ ሌላ የኃይለ ሥላሴን የሚፍጨሩ ፖሊሲ ቀጠለ፡፡ በቅርቡ ደግሞ 'መሬት ላራሹን' የሚያፀድቅ አዋጅ አወጣ፣የዘውድ አገዛዝ መደምሰሱንም አስታወቀ፡፡

የኢትዮጵያ ተራማጆች በዛሬይቱ ኢትዮጵያ ሁኔታ ደርጉን በሚመለከቱ በኩል ትክክለኛ አቋም ካልተከተሉ ፊውዳሊዝምንና ኢምፔሪያሊዝምን ለመደምሰስ በሚደረገው ትግል ላይ ከፍተኛ ጉዳት ያስከትላል፡፡ ከላይ ባጭሩ የዘረዘርናቸውን የደርጉን ድርጊቶች እንደ በገመለከት አንዴ ፍጹም አድሃሪ አንዴ ፍጹም ተራማጅ እርምጃዎች እየወሰደ እዚህ ደርሷል፡፡ አሁን ከመሬት ሕግ ወዲህ እንኳ በዚሁ በመለዋወጥነት ምክንያት የደርጉ የሚወስደው እርምጃ ምን እንደሚሆን ለመገመት አይቻልም፡፡ በቅርብ ጊዜ ውስጥ ኢትዮጵያ ወዴት እንደምትጓዝም እንዲሁ በእርግጠኝነት ለመተንበይ አይቻልም፡፡ ወይ በደርጉ በኢምፔሪያሊዝም መካከል ያለው ቅራኔ ይባባስና በደርጉ ውስጥና ውጭ ያሉ የሲቪል ሰዎች በሁኔታ ያሁኑን ደርግ ሊገለብጡ ይችላሉ፡፡ ወይ በደርጉ በራሱ ውስጥ የግራና የቀኝ ክንፍል ይነሳና ቀኙ አይሉ እንደም አቅደት የነበረውን መንገድ



ይቀጥሉ ይሆናል፡፡ ወይንም የኢትዮጵያ ተራማጆች ይህንን ታሪካዊ የሽግግር ወቅት ተጠቀመውበት ባስቸኳይ ለመደራጀትና ለማደራጀት ይባካላቸውና የኢትዮጵያ ሕዝቦች የቀርብ ጊዜ እድል በ120 የደርግ አባሎች የሚወሰን ባይሆን በራሱ በሕዝቡ እጅ እንዲገባ ያስችሉ ይሆናል፡፡ የምንመኘውና የምንታገለው ለዚህ ለመጨረሻው ቢሆንም ያገሪቷን የቀርብ ጊዜ እረማመድ ከላይ እንዳልነው እርግጠኛ ሆኖ ለመተንበይ አይቻልም፡፡

ነገር ግን እርግጠኛ ሆኖ የወደፊቱን መተንበይ አይቻልም ስለተባለ፣ለዛሬው ትግል የሚያቀጣ ለነገው ትግል መሰረት የሚሆን መስመር ዛሬ መያዝ አይቻልም ማለት አይደለም፡፡ ለነገው መሰረት የሚሆን ፖሊሲ ለመቀየስ ግን ዛሬ ካለው ተጨባጭ ሁኔታ መነሳት አለብን፡፡ ሌኒን እንደሚያስተምረን የተራማጅ ትክክለኛ አካሄድ ይኸው ነው፡፡

"In assesing a given situation,a Marxist must proceed NOT from what is possible but from what is real."(C.W.vol.24)

ከዚህ ጥቅስ በግልጽ እንደሚታየው ለዛሬው ሥራ ከዛሬው ተጨባጭ ሁኔታ መነሳት አለብን ለማለት እንጂ ስለወደፊቱ ማሰብ የለብንም ለማለት አይደለም፡፡ እንዲያውም ወደፊት ለሚመጣው ለመዘጋጀት ዛሬ ከሚሆነው መነሳት አለብን ለማለት ነው፡፡ የኢትዮጵያን ሁኔታ በሚመለከቱ በኩል ብቻ ሳይሆን ደርጉንም በሚመለከቱ በኩል አካሄዳችን እንዲሁ መሆን አለበት፡፡ ስለዚህም በዚህ ጽሑፍ ስለደርጉ ስናወራ ዛሬ ስላለው ደርግ እንጂ ወደፊት ሊኖር ስለሚችለው ደርግ አይደለም፡፡

የጦር ኃይሎች ደርግ ሥልጣን ከያዘ ጀምሮ በወሰዳቸው እርምጃዎች በኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበራት ዘንድ የተለያዩ አቋሞች ተወስደዋል፡፡ ባጠቃላይ ስለደርጉም እንዲሁ ልዩነቶች አሉ፡፡ የደርጉን እርምጃዎች በሙሉ እየተቃወሙ መጪውን በቀድሞ ገዥ መደቦችና በደርጉ መካከል ልዩነት የማያዩትን ወገን የዓለም ዐቀፍ ፌዴሬሽን/ኢዜአ/መሪዎችና ደጋፊዎቻቸው ይወክሏሉ፡፡ ደርጉንም እንዳለ በመደገፍ መግለጫዎች ያወጡ ማህበራትና የተማሪ ገሮች አሉ፡፡ ደርጉ በሕዝብ ትግል ተገዶ የወሰዳቸውን ተራማጅ እርምጃዎች እየደገፈ አድሃሪ እርምጃዎቹንና ፀረ-ዲሞክራቲክ አገዛዙን እያጋለጠና እያወገዘ መጪውን ወገን በአውሮፓ ማህበር ይወከላል፡፡ በተለይ በሁለተኛውና በሶስተኛው ወገን የሚዋልሉ ቡድኖች እነዚህን ሶስት አቋሞች እንደምሳሌ ወስደን መጀመሪያዎቹ ሁለቱ ስህተቶች እንደሆኑ የመጨረሻው የኢትዮጵያ ተራማጆች ሊኖራቸው የሚገባ ትክክለኛ አቋም መሆኑን በዚህ ጽሑፍ ለማሳየት እንሞክራለን፡፡ የተያያው ወሰበሰብነት፣የ'ባንዳ በኩል — በሌላ በኩል' መስዘት የአገባበን በጥንቃቄ ነገሩን መከታተል ይጠይቃል፡፡

1. ያለፉ ዐቶች ፌዴሬሽን/ኢዜፍ/መሪዎችና ደጋፊዎቻቸው አቋም

የዚህ መስመር ደጋፊዎችና መሪዎች ስለደርግ አርምጃዎች የወሰዷቸው አቋሞች፣ ስለደርግ የሰጡዋቸው ግምቶች ባጠቃላይ ለማወቅ ፌዴሬሽኑ ያወጣቸውን ስምንት ያህል ወገ ለጧዎች፣ከሀገር ከምባት፣ከአለፎሬያ ከወጡት ጽሁፎች፣ከሀላጉ 'ሳበአደር'፣በርሊን ካሉት የፌዴሬሽን ሰዎች የተበተኑ ጽሁፎችን ማገበብ የበለጠ ይጠቅማል::

ስለደርግ ባጠቃላይ የተጨበጠ አቋም ከነዚህ ጽሁፎች ማየት አይቻልም::አንዴ ደርግ ከቀድሞ የገዥ መደቦች ጋር በጥቅም ሊተባበር ነው ይሉናል::ለምሳሌ ከምባት ገጽ 24 ላይ::አንዴ ገዐስ ከበርቴ ነው ይሉናል::አንዴ ከምንፊደር በርዥሬቱ በርዥዋ ነው ይሉናል::ባጥሩ የተምታታ ስያሜ አገጁ፣ደርግ ፋሽስት ነው የሚለው አያቸው አገጁ ስለመደብ ይዘቱ የአጡት ብይነገቢ ተገቶ፣የደርግን ቦታ ከኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ ተነስተው ያቀረቡት ጥናት የለም::የሚያውቃቸው አገባቢ፣ይህን የሚከረትን መብደቢቸው መች አነበ ቡ" ማለት አይቻልም::ደርግ ስለወሰዳቸው ተራማጅ አርምጃዎች የወሰዷቸው አቋሞችም አን ዱሁ የማይያዙ የማይጨበጡ ናቸው::አንዳንዴ የሚያስቁ አንዳንዴም ፍጹም አይዛሩ ናቸው::

ደርግ ከሥምበ በላይ የሚሆኑ የቀድሞ ባለሥልጣኖችን በሞት አገደቀ ፌዴሬሽኑ ባወጣው መግለጫ ይህ የተደረገው በዚያኑ እለት የተገደሉትን ተራማጆች መገደል ለመሸፈን ሲባል ነው ይል ነበር::ከበርሊን የፌዴሬሽኑ ደጋፊዎች ቡድን አንዱ የተበተነ ጽሁፍ ላይ በኢትዮጵያ ያሉትን ፋብሪካዎች ወዘተ. መንገበት ሀብት የተደረገው ወዘደሬ የነ ናቸው ብሉ በተራደበ አንዳያደርግ ነው ብሏል::መሬትን አዋጅም በተያዘው አለፈውታል:: ፌዴሬሽኑ በዚሁ ባበያ ባወጣው መግለጫ ላይ 'ይህ አዋጅ የወጣው መደብ ትግሉን ለማ ቀዘ ቀዘ/ለማዉናገፍ/ና ብ ዜሬ ነፃ አውጭ ገቦና ፅያችን ለመደምሰስ ነው ብሏል:: በቀርቡ በደርጉን ማህበር ጠቅላላ ጉባዔ ላይ የለምናው የፌዴሬሽን ቡለቲን አዘጋጅ አማካይነት ቁርበ የዐደቀው ውሳኔም ይህ አዋጅ ወረቀት ላይ ከዋለ በገጠር የፋሽዝም ተሸካሚ የሆነውን መደብ ስለሚያስፋፋ 'አንጭንጠነቀቅ' ያስጠነቅ::ይኸው ሰው በዚህ ጉባዔ ላይ ኃይለ ሥላሴ ከደርግ መቶ ጊዜ አገደሚሻል ገለጸ ነበር::

እነዚህን የፌዴሬሽን መሪዎችና መሰሎቻቸውን አቋሞች ለምሳሌ ያህል ጠቀ ስናል::በዙዎቹ አቋሞች ለራባቸው በሰሜናገሪ እነሱን በመተቸት ብዙ ያላት ማጥፋትም አያስፈልግ::አንዳንዶቹን ብቻ በመተቸት አገወስናለን::

ደርግ ወይ ገዐስ ከበርቴ ነው ወይም 'ፊውዳል ከምንፊደር በርዥዋ' ነው ብሉ ቁርጥ ያለ አቋም መውሰድ ይገባቸው ነበር::ለመያዝ ሴሉ ብቻ የሚያዝም ሰው ካልሆነ በቁር ለገዐስ ከበርቴ መንገበት የሚደረግ ተያዞቁና 'ለፊውዳል ከምንፊደር



በርዥዋ'/የፈለገውን ማለት ይሁንና/ የሚደረግ ተያዞቁ አንድ ሊሆን አይችሉምና ከሁለቱ አንዱን መያዝ ነበረባቸው::ከተባደሉ መቻላቸው ነባቸውና!ይህን አላረጉም::

ደርግ ከቀድሞ ባለሥልጣኖች ጋር እየተባበረ የሚሄድ ከሆነ የነሥራት ቢባ መገ ደል ምን ለናገር ይሆን?ቀሩ ሰዎች ቢሳ ገቦተው ለምን አለቁ?እነዚር ሃነ መስቀል ደበታበ ቢሳ ለቢሳ ምን አገበሩተታቸው?ለዚህ መልስ በናገኘ ከኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ ተነስተው የተገለ መስመራቸውን የሚቀይሩ'ሬቮሉሽናውያን' መሆናቸውን ባለ ተጠራጠርገም ነበር!!የደርግን ፊውዳለነት በማመለከተው በኩል እንዳሉት ቢሆን ኖሮ፣ከቀድሞ ገዢዎች ጋር በጥቅም የሚተባበረው ደርግ 'መሬት ላራሹን' የሚያፀድቅ አዋጅ ሲያወጣ በራሱ ላይ የሞት ፍርድ የፈረደ የመደመሪያው የፊውዳሊዝም ጥቅም ጠባቂ ያረገዋል::በሌላ በኩል ግን የአዋጁ ሥራ ላይ መዋል ፋሽዝምን በገጠር ያስፋፋል በሚል ሰበብ መሬትን አዋጅ የሚያወጣ ደገፍ የፊውዳሉ መደብ መሬትን ተነጥቀ ገበሬውን ፋሽስት አንዳያደርገበገ ደርግን ተከተው ተቀመን የሚጠብቁት እኚህ ዓይነት 'ተራማጆች' ሆነዋል!!!.

በደርግ የቢሮክራሲዝም አዋጅ ላይ የወሰዱት አቋም እንዲሁ ቀጥ ያለ ነው:: የለደናው የሀላጉ ላብ አደር ባይገባቼ ቢሮክራሲዝም ባለመሆኑ ሊያስቀን ፈልጉ 'እን ደኔ እንደኔ'መዝ' ሉሉት ይችሉ ነበር ይሉናል::የደርግ ቢሮክራሲዝም በዴገባቼ እንዳል ሆነ እንዲያውም የሚያረሩት ሀሳቦች እንዳሉት የማርክሲዝምን ሀሁ ያወቀ ሰው በቀላሉ ሊረዳ ይችላል::የደርግ ቢሮክራሲዝም ለምን ባይገባቼ አለሆነም ብሉ ለመተቸት የሚነሳ ካለ ራሱ ስለ ባይገባቼ ቢሮክራሲዝም አያውቅም ማለት ነው::አንደኛ ነገር ደርግ በሳ ይገባቼ ርእዮተ ዓለም የሚመራን መደብ የሚወክል ባለመሆኑ አይጠበቅበትም::ሁለተኛ ነገር የደርግ አባሎች አብዛኛዎቹ ቢሮክራሲቶች በሆኑ ኖሮ እንኳ ባይገባቼ ቢሮክራሲ ዝም አያውቁም ነበር::ስለዚህም ባይገባቼ ቢሮክራሲዝም እንዳልሆነ ማስየትና ማጋለጥ ተገቢ ነገር ነው፣ለምን ባይገባቼ አለሆነም ብሉ መያዝም ግን ቂልነት ነው::

የፌዴሬሽን ሰዎች የደርግ ቢሮክራሲዝም ባይገባቼ ባለመሆኑ ከወጋገዙ በኋላ /እነሱም በለባይገባቼ ቢሮክራሲዝም የሚያውቁት እነበተኛ ቢሆንም/ ለደርግ ፋሺስትነት አንደአንዱ ማረጋገጫ ይወስዱታል::በበላቢ ዓመታት በፊት እነቆበሉኒ እነሂትለር ባይ ገባቼ ያልሆነ ቢሮክራሲዝም አውጀው ነበር::ፋሽስቶች ነበሩ::በ1975 ደርግ ባይገባቼ ገባቼ ያልሆነ ቢሮክራሲዝም አወጀ::ከቆበሉኒ አበራክ የወጣ/የደርጉን ጉባዔ ውሳኔ ፩ገ፩/ ያልሆነ ቢሮክራሲዝም አወጀ::ከቆበሉኒ አበራክ የወጣ/የደርጉን ጉባዔ ውሳኔ ያልሆኑ ቢሮክራሲዝም

ለመሆኑ አንዱ ማረጋገጫ ነው::አዘር ለማያዩ መች እነሰ?!

በለማረጋገጫነቱ ከማገባታችን በፊት ባይገባቼ በሳለሆኑ ቢሮክራሲዝሞች በመደቡ እናውቃ::ከመደመሪያው ቢሮክራሲዝም የባይገባቼ ርእዮተ ዓለም መገለገልያ ያለ፣

የወዛደሩ መደብ ወገኖች መጠሪያ ብቻ መሆኑን ከ በጣም የዴ ቷል::ከሙኒስት ማኒፌስቶ ይህ በኋላ ይዞ የወጣው ያኸ ቶተኾ፣ የከበርቴውን ሥርዐት አደጋ ላይ የሚጥል ለው፤ ገን ጥፍ በዘበዛ ይጥፋ ባቅ ሁሉ ራሱን 'ሶሺያሊስት' ብሎ ይጠራ ስለነበረ ነው ይላል እንገልስ::/የ1888ቱ የኮሙኒስ ማኒፌስቶ የእንግሊዝና እትም መግቢያ/ ከዚያም ወዲህ ከወዛደሩ ይልቅ ለቀ ለቀ የንዑስ ከበርቴ ክፍሎች ይህንኑ መጠሪያ ይገለገሉበታል::ለምሳሌ በደቡብ ቪየትናም የነፃ አውጭ ግንባር ውስጥ የወዛደሩ ፓርቲ 'ሬቮሉሽናዊ የሕዝብ ፓርቲ' ተብሎ ሲጠራ የንዑስ ከበርቴው ፓርቲ ግን 'ራዲካል ሶሺያሊስት ፓርቲ' የሚል ስያሜ አለው::

በሩሲያ ከሬቮሉሽኑ በፊት የነበረው ሁኔታ የበለጠ ጥሩ ምሳሌ ነው::በዚያን ጊዜ ሩሲያ ሳይንሳዊ ያልሆነ ርእዮተ ዓለማቸው ሶሺያሊዝም የሚል ስያሜ የሰጡ እራሳቸውም ሶሺያሊስት ብለው የሚጠሩ እነ ሶሺያሊስት ሬቮሉሽናሪስ፣ፖፑላር ሶሺያሊስትስ የሚባሉ ነበሩ::እነሌኒን የነዚህን ሶሺያሊዝም ፀረሳይንሳዊነት እያጋለጡ፣በሶሺያሊዝም ስር የሚሸፍኑት መደብ ይዘታቸውን እያሳዩ በዙ ታግለዋቸዋል::/በነገራችን ላይ እነ ሌኒን ካጋለጡት የነዚህ ገሪፖች ፀረ ሳይንስ ገምት እንዱ ካፒታሊዝም ሊያድግ አይችልም የሚለው ነበር:: የሩ.ን አጥር ዝዞች ሊገርም ይችላል፤ ለሶሺያሊዝም የሚታገሉት እነሌኒን ካፒታሊዝም ሊያድግ ይችላል ሲሉ፣ለካፒታሊዝም መምጣት በለው ፊውዳሊዝምን ይታገሉ የነበሩት ንዑስ ከበርቴዎች ግን ካፒታሊዝም ሊያድግ አይችልም ይሉ ነበር::/እነሌኒን ይህን ሳይንሳዊ ያልሆነ ሶሺያሊዝም እያጋለጡ የተከታዮቹን የመደብ ይዘት መርምረው በዚህ ሶሺያሊዝም ስር የሚገለፀውን አስተሳሰብ ከአቀራቢያቹ መደብ ፍላጎት ጋር ያለውን ዝምድና ይገልጡት ነበር እንጂ ርእዮተ ዓለማቸው ለምን ፀረ ሳይንሳዊ ሆነ በለው፤ ወይንም ይህንን እንደአድሃሪነቱ ምልክት/በተለይ የትግል ደረጃ/አይተውት አያውቁም ነበር::ከብዙዎቹ ጋርም በትግል ተባብረዋል::

ከላይ ከበጩ ናቸው ምሳሌዎች ለማየት እንደሚቻለው ሳይንሳዊ ያልሆነ ሶሺያሊዝም የነጂተለር ረዐፍ ባይሆን የደቀም የነበረ፣ከርሶም ጋር የሚመጡ አድሃሪ ገዳቶች/ሳይንሳዊ እስካልሆነ ድረስ ከአድሃሪ ገዳቶች ሊለዩ አይችሉም::/የሩሽሰትነት ይቀርና በተለይ የታሪክ ወቅት የዚህን መደብ አድሃሪነት እንኳ ሊያስብ እንደሚያቸሉ ለመረዳት ይቻላል::

ወደደርጉ ሶሺያሊዝም እንመለስና፣ሳይንሳዊ አለመሆኑ ፋሽስታዊ አያደርገውም::እንዲያውም የኢትዮጵያ ሕብረተሰብ በሚገኝበት ደረጃ ተራማጅነት አለው/ፀረሳይንሳዊ ይዘቶች አያሉትም::/አሁን ባለንበት ወቅት ከፊውዳሉ አይደለም ወይንዑስ ከበርቴ አይደለም የተደረገ እንጂ የወደፊት እርምጃ ነው::ይህን የሚክዱ የንዑስ ከበርቴ ርእዮተ አለም ከፊውዳሉ የበለጠ ተራማጅ እንደሆነ የማያውቅ ነው::ይህ ደግሞ ሳይንሳዊ እንደ



ማይሆን የታወቀ ነው::ሆኖም ሳሎት የሰደሮች ከመዝ አይለይ እንጂ መታወቅ እራሱ ታሪካዊ ትርጉም አለው::ይህ አጭሩ ሳይታወቁ ኖር ይቀር እንደነበር ቢያጠራቅርም፣ አርግጥ የኢትዮጵያ እውነተኛ ሶሺያሊስቶች የዚህን 'የአጭሩ ሶሺያሊዝም' ሳይንሳዊ አለመሆን ለማጋለጥ ስለሚገደቱ በመታወቅ 'ትርፍ' ሥራ የተሟነባቸው ይመስላል:: ሳይንሳዊ ሶሺያሊዝም ከተወለደ ጊዜ ጀምሮ ሳይንሳዊ ካልሆኑ ተራማጅ አስተሳሰቦችና ዓማጉጊዎች ጋር እየታገለ እዚህ የደረሰ መሆኑን የሚያውቀ ግን ሳይንሳዊ ባለመሆኑ ብቻ ወይይ አይሉትም::በደርጉ ጋዜጦች ላይ አሉፍ አሉፍ የሚወጡትን ትክክለኛና ሳይንሳዊ ትንተናዎች ወደጉን ትተን፣በኃይለ ሥላሴ ዘመን የሚወጣውን አዲስ ዘመንና የዛሬውን በማስተያየት ብቻ እንኳ የዚህን አጭሩ ስታ ለማየት እንችላለን::በኃይለ ሥላሴ መለኮታዊ ሥልጣን ወዘተ. አየፃፈ ሕዝቡን ለማደደብ ተልቀ አስተዋጽኦ ያረጉ የነበሩ ጋዜጦች ዛሬ በለአከለቶት፣ሁሉ መሥራት አለበት፣መሬት ላራሹ ይሁን፣ወዘተ. እያሉ ሲጽፉ በርእዮተ ዓለም ደረጃ ከፊውዳሊዝም ለመላቀቅ በሚደረገ ትግል ያላቸውን አስተዋጽኦ ፈጽሞ መናቅ አይቻልም::እንግዲውን ከፊውዳሊስት አይደሉም እሊቸው ወደ ሳይንሳዊ ሶሺያሊዝም አያመጡትም::ግን ከፊውዳል አይደሉም ማለቱ ቀያቸው ራሱ ትርጉም አለው:: የሚቀጥለው የኢትዮጵያ ሬቮሉሽን ሶሺያሊስት እንዳልሆነ የሚያውቀን ሰው ይህ የሚያስገርመው አይመስለንም::ሌኒን በርእዮተ ዓለም ደረጃ በጣም የታገሏቸውን የናሮዶኒኮችን ርእዮተ ዓለም እንበተ እንዲህ ብሎ ነበር::

"In sofar as the Narodikshold the opinion that eqauality may be maintained on a basis of commodity production...,their views are erroneous and their socialism reactionary.That is something every Marxist should know and remember.The Marxist,however,would be unfaithful to his historical analysis of the specific tasks of the bourgeois-democratic revolution if he were to forget that this very idea of equality and the many different equalitarian plans are the fullest possible expression of the tasks of the bourgeois revolution,NOT the socialist, and that they express the tasks,not of the struggle against capitalism,but of the struggle agianst the rule of the landrods and bureaucracy"

(Lenin.C.W.Vol.12.p.355-6)

ከላይ ለማሳየት የሞከርነው የደርግ ባይገባቹ ያለሁኑ ሶሺያሊዝም አገዟን የፋሺስትነቱ ምልክት ሊሆን ኢትዮጵያ ባለችበት የእድገት ደረጃ የተወሰነ ተራማጅነት እንዳለው ነው።የፌዴሬሽን ባለሟሎች አገዟን የዚሁን ባይገባቹ ያለሁኑ ሶሺያሊዝም የተወሰነ ተራማጅነት ሊያቆ ይቀርና ደርግ የሚሰራቸው ነገሮች ሁሉ ለነሱ የፋሺስትነቱ ምልክት ነው።ፌዴሬሽኑ ስለመሬት አዋጁ በወጣው መገለጫ ላይ የሚከተለውን አንዴ፦

"To stifle or diffuse the class struggle and mobilize the masses against national liberation wars,it was inevitable that the Junta will sooner or later attempt the agrarian problem.Hence,on March 4/75 the nationalization of all rural lands was declared."

ስለዚህ መገለጫ በዚሁ እትም ሌላ ጽሁፍ በለማመለስት አንባብ እንደገረመው ብቻ ጠቀስነው እናልፋለን።ብቻ ዛሬ ባገራችን ባር ቀጠሉ የፋሺዝም ምልክት ነው። የሀላንዱ ቅርንጫፍ ማህበር 1ኛው ዝግጅትን እንዲያመናለት የሚለገው 'ገበ ከበርቴና ፋሺዝም' መሆኑ ይሆን የሌለ ጠላት /ፋሺዝምን/ ለመዋጋት ምን ያህል ቀንና ሌሊት እንደሚያስቡ ያስያል።በቀርቡ በደርመን ዝግጅ ላይ እንዳቀየነው፣ደርግ ፀረ ዲሞክራቲክ ነው፣አንዳንዱ ድርጊቶቹ ፋሺስታዊ ናቸው ግን ይከ በኢትዮጵያ ፋሺዝም ነገሠ ለማለት አያስችልም የሚለውትክክለኛ አቋም ደርግን ከመደገፍ ይቆጠራል።የዛሬው ተራማጅነት በኢትዮጵያ ፋሺስታዊ አገዛዝ አለ ማለት ሆኗል።ምናልባት ፋሺስታዊ ድርጊትና ፋሺስታዊ አገዛዝ ተቀላቅለው ነው በለን ነበር።ስለፋሺዝም ያላቸውን እውቀት በምሳሌ ቢያስረዱን የሚለው ከሽ ትንታ ፋሺስታዊ አይደለም፣ደርግ ግን ነው ብለውናል።

ባሁኑ ጊዜ የቀደመው እሱን ወራሽ ከለንደን የሚያወጣው መገለጫና የሀላንዱ ማህበር በደርግ ላይ የሚሰጠው መገለጫ የሚለያየው በመጠኑ ነው።ሀላንዱ ያለው ያ ናው በለቴን አዘጋጅ ኃይለ ሥላሴ በደርግ ወቅ ጊዜ እንደሚገሸ ገለፀልን ነበር። ኃይለ ሥላሴ እንደወደቀ ደስ ብሎት የነበረው አስፋ ወሰን አሁን ግን አባቱ ይሻለኝ ነበር ባይል አለቀረም።ሁለቱም ሰብአዊ ፍቅር ያላቸው የዓለም ሕዝቦች ኢትዮጵያ ከወደቀችበት ፋሺስታዊ ስርዐት ለማዳን የእርዳታ እጃቸውን መዘርጋት ያለባቸው አሁን መሆኑን አስታውቀዋል።/የእሱን ወራሽን መገለጫና የሀላንዱ ቅ/ማህበርን መገለጫ ተመልከት/ ባገራችን የታወጀውን መሬት ላራሹ መሬታቸውን ስለሚያስወስዱባቸው ደርግን የሚያወሩ በርከት ያሉ ባለመሬቶች አሉ።የፌዴሬሽን ስያቸው ገበሬው መሬት ወስዶ 'ፋሺስት' እንዳይሆንባቸው ይፈልጋሉ።ከዋናነት የፌዴሬሽን ቅርንጫፍ የሚወጣ አንድ



'ሰሳነ አበዩት' የሚባል ቀባጣሪ ጋዜጣ በዜና አምድ ላይ 'ጭሰኞች' ተገላቸውን አፋና መው እንዴ ሄሊኮፕተር ከማያጠለቸውም በላይ በዙ ወታደሮች ማሰራቸውን ለጋዜኞቹ አበሰር ነበር።ይህ ገበሬን 'ፋሺስት' የሚያደርግ አዋጅ ሥራ ላይ እንዳይውል ከሚታገሉ ኃይሎች ጋር እንደሚተዛዘኑ ጥሩ ምልክት ሰጥቷል።በርግጥም ፋሺዝም በኢትዮጵያ ካለ ከማገናውም ኃይል ጋር ሆኖ እርሱን መዋጋት ይገባል።በሁለተኛው የአለም ጦርነት ጊዜ ኮሙኒስቶች ከኢምፔሪያሊስቶች ጋር የተገለ ግንባር ፈጥረው ፋሺዝምን ተዋግተዋል። የቻይና ኮሙኒስቶች ከቻይና ፊውዳሊስቶች ጋር ሆነው የጃፓንን ፋሺዝም ተዋግተዋል። የቀርብ ምሳሌ ለመጥራት፣በከምቦዲያ ነፃነት ተዋጊዎች ሲአይኤ ባገራቸው ፋሺስታዊ የወታደር አገዛዝ በመሰረተ ጊዜ ከዚያ በፊት ለአመታት ጠቅ ሆነው ይታገሉት የነበረውን ሲሃኖክ/ሰዐለ/ እንዲተባበራቸው አርገዋል።ፋሺዝም ዋና ጠላት የሆነባቸው የኛዎቹ 'ተራማጆቸም' ይህን የኢትዮጵያ ፋሺዝም ለመደምሰስ —መሬቱን ለማግኘት በመታገል ላይ ካለው የኢትዮጵያ ገበሬ፣ይህን አዋጅ በደስታ ከተቀበለው የኢትዮጵያ ወዛደር፣ከአብዛኛው የከተማ ነዋሪና ተራማጅ ምሁሩን በስተቀር —'በሬ' የተገለ ግንባር ለመከፈት አመቺ ሁኔታ አለላቸው።እናም፣ይህ በኢትዮጵያ ፋሺዝም አለ የሚለው ሰበብ ከፀረ ሕዝብ ኃይሎች ጋር ለሚደረግ የወደፊት ትብብር ርእዮተዓለማዊ ዝግጅት መሆን አለመሆኑን የምንገመራመረው ለተቂት ጊዜ ይሆናል።

## ደርግን የሚደገፉ

የዚህ መስመር ደጋፊዎች የደርግን ተራማጅ እርምጃዎች በማወደስ፣ለአድሃሪ እርምጃዎቹ በገኩሩ ምክንያቶችን በመስጠት ትልቅ ውዥንብር ይነዛሉ።በጣም ግልጽ በሆነው የኤርትራ ፍጅት ላይ እንኳ ይህን የደርግን ፀረሕዝብ እርምጃ የደገፉ አሉበት።ስለዚህም ጥያቄውን ባጭሩ እንመልከተው።

የኢትዮጵያን ሕዝቦችና የኤርትራን ሕዝብ አንድነት የማይፈልግ ተራማጅ አይኖርም።ጥያቄው ግን ይህ አንድነት እንዴት ይገኛል?እንዴትስ እውነተኛ አንድነት ይሆናል?የሚለው ነው።እውነተኛ አንድነት ለመሰረት የሚችለው በእኩልነት ላይ ብቻ ነው።እውነኛ አንድነት ለመሰረት የሚችለው በመፈቃቀርና በመፈቃቀድ ብቻ ነው።ከዚህ ውጭ አንድነት ሊኖር አይችልም።የተለያዩ ሕዝቦችን በጉልበት አንድ ላይ ለማኖር መሞከር የሚያስከትለው መቀራረብን ሳይሆን መራራቅንና መቃቃርን ነው።ስለዚህ እውነተኛ አንድነትን የሚፈልግ ሁሉ በመጀመሪያ የተለያዩ ብሄረሰቦች ያላቸውን መብትና እኩልነት ማወቅ ይኖርበታል።ከዚሁ ጋር ተያይዞ የብሄር ጥያቄ መሰረት የሆኑትን አስተሳሰቦች

ፖለቲካዊ ምክንያቶች ለመደምሰስ መታገል አለባቸው።ማለትም፣በኢትዮጵያ እውነተኛ የሕዝቦች አንድነት እንዲኖር የፈለገ፣ እስካሁን የተጨቆኑ ብሄረሰቦችን እኩልነት፣የራሳቸውን እድል በራሳቸው ለመወሰን ያላቸውን መብት ማወቅ ይኖርበታል።ከዚሁ ጋር አያይዞ የብሄርና የሌሎችም ጭቆናዎች መሰረት የሆኑትን ፊውዳሊዝምንና ኢምፔሪያሊዝምን ለመደምሰስ መታገል አለበት።የብሄሮች የእኩልነት መብት በታወቀበት ኢትዮጵያ፣ፊውዳሊዝምና ኢምፔሪያሊዝም በተደመሰሱበት ኢትዮጵያ የብሄር ጭቆና አይኖርም፣በመፈላለግና በመፈቃቀር ላይ የተመሰረተ እውነተኛ አንድነት ይኖራል።

ኢትዮጵያ ብዙ ብሄረሰቦች በጉልበት ተገደው የሚኖሩባት "የብሄረሰቦች እሥር ቤት" ሆና ቆይታለች።አሁንም የብሄረሰቦች መብት ያልታወቀባት፣የዚህ ጭቆና መሰረቶች ያልተደመሰሱባት አገር በለሆነች በመፈላለግ ላይ የተመሰረተ አንድነት የለም።የጦር ኃይሎች ደርግ ሥልጣን ከያዘ ጀምሮ በዚህ ጥያቄ ላይ የተከተለው ፖለቲካ ይህንኑ "የብሄረሰቦች እሥር ቤትነቷን" የሚያፀና ነው።የኤርትራ ሕዝብ ከ13 ዓመታት በላይ የብሄር ጭቆናንና የዚሁ ጭቆና መሠረታዊ ምክንያቶችን ሲታገል ቆይቷል።የሌለውን "የኢትዮጵያ አንድነት" ለመጠበቅ ተፈጠርኩ የሚለው የጦር ኃይሎች ደርግ ይህ የኤርትራ ሕዝብ ትግል ለነፃነት መሆኑን እንደማወቅ፣ሕዝቡ የፈለገውን ለመወሰን መብት እንዳለው እንደማመን፣በያለትም ሁነ በጀርገት የቀደምቶችን የኢትዮጵያ ገዥዎች ፖለቲካ ለመከተል መርጧል።የሰፊው ኤርትራ ሕዝብ ባይሆን የጥቂት "ሽፍቶች" ትግል ነው ይለናል። የኤርትራ ሕዝብ የራሱን እድል በራሱ የመወሰን መብት እንዳለው አውቆ ለጥያቄው ሰላማዊ መፍትሄ እንደመፈለግ በጦር ኃይል መጨፍጨፍን መርጧል።በአንድነት ስም ኤርትራ በቦንብና በጥይት ተደበደባለች፣በ"አንድነት"ስም ሰፊ ፀረኤርትራ ፕሮፓጋንዳ በኢትዮጵያ ውስጥ ይካሄዳል።ይህ ሁሉ በኤርትራና በኢትዮጵያ ሕዝቦች አንድነት ላይ የተፈጸመ ወንጀል ነው።በአንድነት ሥም የተሰራው ይህ ወንጀል ያስከተለው መቀራረብንና መፈቃቀድን ባይሆን መራራቅንና መቃቃርን ነው።ስለዚህ ነው ለኤርትራና ለኢትዮጵያ ሕዝቦች እውነተኛ አንድነት የምንታገል ተራማጆች ይህን የአንድነት ፀር የሆነውን የደርግን ፀረ ሕዝብ ፖለቲካ አገቧን ለንደገና ማውገዝና ማጋለጥ ያለብን።

የኤርትራ ጥያቄ በዚህ ደብያገና፣የተቀረውን የደርግን የእስካሁን ፖለቲካ ስንመለከት በመሰረቱ ፀረፊውዳሊስት፣ከኢምፔሪያሊዝም ጋርም ግዝያዊ ቅራኔ ውስጥ የከተተው መሆኑን እናያለን።እነዚሁ ደግሞ የኢትዮጵያ ሕዝቦች መሰረታዊ ጠላቶች ናቸው። ከዚህ ተነስቶ ግን በደርግና በኢትዮጵያ ሕዝቦች መሃል ቅራኔ የለም ማለት የኢትዮጵያን ሬቮሉሽን የሚያሰናክል አቋም ነው።



የጦር ኃይሎች ደርግ የቀደምቶችን የኢምፔሪያሊስት አሽከሮች መገደሉ፣የውጭ ካፒታሊስቶችን ሀብት መውረሱ፣በመጨረሻም አገሪቷን ፍጹም አብዮታዊ ማእበል ውስጥ የሚከት የመሬት አዋጅ መደንገጉ፣እነዚሁ ሁሉ ከኢምፔሪያሊዝም ጋር ግዝያዊ ቅራኔ ውስጥ ከተውታል።ይህን ቅራኔ መካድ ከኢምፔሪያሊዝም ጋር እስከመጣበል ድረስ ሊያስኬድ ይችላል።ይህን ቅራኔ እንደመሰረታዊ ወይንም እንደዘላቂ መውሰድ ደግሞ በኢትዮጵያ ለፀረኢምፔሪያሊስት ትግል መደረግ ያለበትን ዝግጅት የሚያደናቅፍ ፖለቲካ ነው።ይህን ቅራኔ ግዝያዊነቷን ሽረው መሰረታዊ ሊያስመስሉት የሚችሉ ምልክቶች እንኳ የሉም።ደርጉ በመግለጫዎቹ አስፍሮአቸው የነበሩት ፀረ ኢምፔሪያሊስት ዓላማዎች እስካሁን በተግባር አልተተረጎሙም።ሰሞኑን ከዋሺንግተን የሚመጡት "እርዳታዎች" የቅራኔውን እየጠበበ መሄድ ነው የሚያሳዩት።

እንግዲህ በደርግና በኢምፔሪያሊዝም መሃል ያሉትን ግዝያዊ ቅራኔዎች ተጠቅሞ መታገል ያስፈልጋል።ደርጉ ከኢምፔሪያሊዝም ጋር የሚያደርገውን መቀራረብ እያጋለጡ ዘላቂ ፀረ ኢምፔሪያሊስቶችን ለትግሉ ማዘጋጀት ግን ዋናው ተግባር ነው።በደርጉና በኢምፔሪያሊዝም መሃል ያለውን ቅራኔ እንደመሰረታዊ መውሰድና በርሱም ላይ እምነት መጣል ደግሞ እውነተኛ የኢትዮጵያ ፀረ ኢምፔሪያሊስቶችን ከተግባራቸው ማዘናጋት፣ትግላቸውን ማጨናገፍ ይሆናል።

የደርጉ የመሬት ላራሹ አዋጅ ፍጹም ሬቮሉሽናዊ ነው።ይህ ሁሉ ሆኖ ግን ዲሞክራሲያዊ መብቶች አሁንም እንደተከለከሉ ነው።በተለይ የመሬት አዋጅ ወጥቶ ዲሞክራሲያዊ መብቶችን መከልከል "የሰፊው ሕዝብ ድምጽ" በትክክል እንዳስቀመጠው "ሥጋ ሰጥቶ ቢላዋ እንደመከልከል" ነው።ስለዚህም በመሬት ጥያቄ ባቢያ በደርግና በሰፊው ሕዝብ መሃል ለጊዜው ቅራኔ ባይኖርም፣በዲሞክራሲ ጥያቄ ላይ በደርግና በኢትዮጵያ ሕዝቦች መሃል ያለው ቅራኔ የበለጠ ከሯል።

ሁላችንም ለንስማማበት የምንችለው አንድ ነገር አለ።ይኸውም ፊውዳሊዝምንና ኢምፔሪያሊዝምን መደምሰስ የሚችለው ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ ነው።ደርጉ ሆነ ሌላ ቡድን ሰፊውን ሕዝብ ተክቶ ይህን ሊያደርግ አይችልም።ደርጉ ግን "መሬት ላራሹም" ብሎ ኢምፔሪያሊዝምንም ተንኮኘ እነዚሁን ጥንድ ጠላቶች ሊደመስስ የሚችለው የሕዝብ ኃይል በዲሞክራቲክ መብቶች እየተጠቀመ እንዳይደራጅ እየከለከለ ነው።የሕዝብ ጠላቶችም ፋታ አገኝተው እየተደራጁ ናቸው።ሰፊው ሕዝብ እንዳይደራጅ መከልከል የጠላቶችን መደምሰስ ማገድ ነው።ሬቮሉሽኑ ወደፊት እንዳይገፋ መግታት ነው።ስለዚህም የጦር ኃይሎች ደርግ ፊውዳሊዝምን ለማጥፋት የፈለገውን ያህል ፍላጎት በኖረው እንኳ፣ለሰፊው

ሕዝብ እንደሕይወት እስትንፋስ የሚያስፈልጉትን ዲሞክራቲክ መብቶች እስከነፈገ ድረስ በገበር የፊውዳሊዝምንና የኢምፔሪያሊዝም አደጋ እንዲራዘም ማድረጉ ነው።

ለነዚህ ዲሞክራቲክ መብቶች መነፈግ በደርጉ ሆነ በደጋፊዎቹ የሚሰጡት ምክንያቶች እንዳንዶቹ ናቸው ፀረ ሕዝብ ናቸው።ሕዝቡ እስከሚያድግ ድረስ ዲሞክራሲ አያስፈልገውም ይላሉ።ይህ ቅኝ ገዥዎች የተጨቆኑ ሕዝቦችን በአገዛዛቸው ሥር ለማቆየት ለረዥም ጊዜ የተጠቀሙበት ፀረ ሕዝብ ምክንያት ነው።ፍጹም ቦታ የለውም።ሁለተኛ ነገር የኢትዮጵያ ሕዝቦች/የዛሬን አያርገውና ደርጉ ጭምር/ ከእጦት በፊት ደምረው ዲሞክራሲያዊ መብቶች ሲጠይቁ ዛሬ ለዲሞክራሲ አልበቃችሁም የሚሉት፣ለታጋዩ ሕዝብ ስድብ እንጂ ቦታ የሌለው ምክንያት ነው።ለሰፊው ሕዝብ መብት ከተከበረ የሕዝቡ ጠላቶች ይጠቀሙበታል የሚለውም ሰበብ እንዲሁ ነው።ከሆዴ ካለጡ እምቢ አይገድም እንደሚባለው ነው።ደርጉ የሕዝቡን መደራጀት የሚከለክለው በርግጥ ይህን ፈርቶ በሆነ ኖሮ፣ለሰፊው ሕዝብ መብት ሰጥቶ የሕዝብ ጠላቶችን የማይከለክልበት ምክንያት የለም ነበር።ሰፊውን ሕዝብ እንዳይደራጅ የሚከለክል መንግስት ተቃዋሚ ሆኖ የሕዝብ ጠላቶችን መከላከልና መቋቋም አያቅተውም።

በቅርቡ የገበሬዎች ማህበራት በየቦታው እንዲደራጁ መደረጉ ይህን የመደራጀት መብት ተያቄ አላሟላም።አንደኛ ነገር እነዚህ ማህበራት የሚደራጁትበመንግስት ቢሮክራሲ አማካይነት ነው።የኢትዮጵያ ጭሰኞች ከዚህ ከኃይለ ሥላሴ ከተወረሰ ቢሮክራሲ ወሳኞቹን እንጂ ፍርሱን መከታነት ወይም ተገኝነት አይፈልጉም።ማለት አሁንም በሆነ ገበሬዎች ከቢሮክራሲው ውጭ በነፃ ለመደራጀት አልተፈቀደላቸውም።እዚህ ላይ ስለገበሬው መደራጀት የተሰጠው መብት ሙሉ እንዳልሆነ ለማሳየት እንጂ እነዚህ እየተደራጁ ያሉት የገበሬ ማህበራት ፊውዳሊዝምን ለማጥፋት በሚደረገው ትግል ያላቸውን ትርጉም ለመካድ እንዳልሆነ ገለጽ መሆን አለበት።ተራማጆች ለነዚህ ማህበራት ከወዛደሩ ቀጥሎ ማህበር ያለተለየ ግምት ሊሰጡ ይገባል ባዮች ነን።

ለገበሬዎች የተሰጠው መብት ያልተሟላ መሆኑን አየን፤የኢትዮጵያ አብዮታውያን፣የወዛደሩ መደብ፣የተቀረትም ፀረ ፊውዳልና ፀረ ኢምፔሪያሊስት ኃይሎች ለመደራጀትና የፖለቲካ ማህበር ለማቋቋም አሁንም መብታቸው እንደተነፈገ ነው።

ለማጠቃለል፣በማንኛውም የሕዝብ ትግል ውስጥ መደራጀት መቻልና አለመቻል የትግሉን ወደፊት መቀጠል አለመቀጠል የሚወስን ከፍተኛ ጉዳይ ነው።ከኢትዮጵያ ሕዝቦች ትግል የወደፊት እድገት ተነስተንም የዲሞክራሲ ጥያቄ በደርጉ በኢትዮጵያ ሕዝቦች መሃል ያለው መሰረታዊ ቅራኔ ነው ያልነውም ስለዚህ ነው።ደርጉ በፈለገውና



በሚኘው አገባ ፊውዳሊዝምንና ኢምፔሪያሊዝምን ሊደመስስ አይችልም።ይህን ሊያደርግ የሚችለው የሰፊው ሕዝብ የተደራጀ ኃይል ነው።ደርጉ የነዚህን ኃይሎች ለዚህ ሬቮሉሽናዊ አላማ መደራጀት እስከከለከለ ድረስ፣በገበር ፀረ ሬቮሉሽናዊ ሚና ይጫወታል።ለደርጉ ፀረ ዲሞክራቲክ አገዛዝ ሰበብ እየሰጡ ለዲሞክራቲክ መብቶች ዛሬ መደረግ ያለበትን ትግል መካድ ቢሊት የኢትዮጵያ ሕዝቦች ትግል እራስን ማግለል ነው።እንዲያውም ሰፊውን ሕዝብ ትግል የወደፊት እድገት የሚያደናቅፍ፣እስካሁን የተደረጉትን ተራማጅ እርምጃዎች መቀልበስ ለሚሹ ኃይሎች ሕዝቡ ሳይዘጋጅ እጅን እንዲሰጥ የሚያደርግ ፖለቲካ ነው።

## 3. ተከበለናው የአውሮፓ ማህበር አዋጅ

የአውሮፓ ማህበር እስካሁን ስለደርጉ የየጊዜው ድርጊቶች የወሰዳቸውን አቋሞች ከሥ/አ/ኮ መግለጫዎች ማየት ይጠቀማል።በተለይም ስለደርጉ ባህሪያይና ስለ እንዳንዱ እርምጃዎች የተደረጉትን በፋፋ ትንተናዎች ከታጠቀ ቁ.1 1967፣ትግላችን ዜና ቁ.3 1967፣ትግላችን ጥር 3 1967 ማገበቡ የበለጠ ይረዳል።ከላይ ሁለቱን በሁተኛ አቋሞች በነቶች ተከበለናውን አዋጅ ማየት እንዲቻለም ጥምር ስለ ነበረ በዚህ የጽሁፋችን ክፍል ብዙ አንመለስበትም።

የአውሮፓ ማህበር የደርጉን ፀረ ዲሞክራቲክ አገዛዝና የኤርትራ ፖለቲካውን ሲያወግዝና ሲያጋልጥ ቆይቷል።እዚህ ጽሁፍ ውስጥ ዋና ትኩረቱ እነዚህ ላይ ሳይሆን ተራማጅ እርምጃዎች ላይ ነው።

ኃይለ ሥላሴ ከሥልጣን ሲወገድ ማህበራችን ድጋፉን እሰጠ።እዚሁ ድጋፉ ላይ ዲሞክራቲክ መብቶች እንዲከበሩ፣የዘውድ አገዛዝ ፈጽሞ እንዲጠፋ ጠይቋል።ደርጉ የቀድሞ ባለሥልጣኖችን በሞት ቀጣ።ኢምፔሪያሊስቶችና አድሃሪዎች ደርጉን በዚህ ሲያጥቡ ማህበራችን ይህን ቅጣት ደግፎ የነዚህን ጨለማ ዝብነት አወገዘ።በዚሁ የድጋፍ መግለጫው ውስጥም ይህ ቅጣት ቢገራችን ፊውዳሊዝምን መደምሰስ እንዳልሆነ፣ደርጉ የቀድሞ የሕዝብ ጠላቶችን መግደሉ ለሰፊው ሕዝብ ዲሞክራሲን እስከነፈገና በኤርትራ ላይ ያለውን አድሃሪ ፖለቲካ እስካላተወ ድረስ ይህ የሕዝብ ውሳኔ እንደማያደርገው ገልጿል ነበር።የወጭ ባለሀብቶች ንብረት መንግስት ሀብት ሲደረግ ይህ በደርጉ በኢምፔሪያሊስቶች መካከል ያለውን ቅራኔ ስለሚያባብስ ደገፈ።በዚሁ ድጋፍ ውስጥም ይህ እርምጃ ደርጉን ከገዐ ከበር ተነስቶ ተወደከበር ተነስቶ ለመሸጋገር ይረዳዋል እንጂ እውነተኛ ሕዝባዊ መንግስት ባገራችን እስካልተመሰረተ ድረስ ለሰፊው ሕዝብ [illegible] [illegible] መሆኑን አሳየ።በመጨረሻም ማህበራችን ፊት ለ10 ዓመታት ሲታገልለት የኖረውን 'መሬት ላራሹ' ደርጉ ሲያውጅ ይህን እንደሰፊው ሕዝብ

ድስ በመቆጠር ይገፋ፡፡በዚሁ ድጋፍ ውስጥ ለዚህ የመሬት አዋጅ ያለገደብ ሥራ ላይ
መዋል የሚያስፈልገው ሁኔታ አሁንም እንዳልተሟላና የዲሞክራቲክ መብቶች ጥያቄ እንደበሰለ
በደርግ በሰፊው ሕዝብ መሃል ቀራኒ ሆኖ እንደሚቆይ አመለከተ፡፡

እንግዲህ ማህበራችን ደርግ በሰፊው ሕዝብ ትግል ተገዶ የወሰዳቸውን ተራ
ማጅ እርምጃዎች፣ከሕዝቡ ጠላቶች ጋር የሚያደርጋቸውን ድርጊቶችን እየደገፈ፣የነዚህን
ተራማጅ ድርጊቶች ውስንነት እያሳየ፣ከነዚህ ድርጊቶች በኋላ የሚቀጥለው ትግል ምን
መሆን እንዳለበት፣እነዚህን ድርጊቶች ተጠቅሞ ትግሉ ወደፊት መገፋት እንዳለበት እያ
መለከተ ትክክለኛ አቋም በመውሰድ እስከአሁን ቆየ፡፡ከኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ
የሚነሳ፣በሪፎርምና በሪቮሉሽን መሃል ያለውን ግንኙነት ያወቀ፣ከሌሎች አብዮታዊ ትግ
ሎች ትምህርትን የቀሰመ ተራማጅ የነዚህን አቋሞች ትክክለኛነት በቀላሉ ሊያይ ይችላል፡፡

እነዚህ በነጠላ ስለተወሰዱት የደርግ እርምጃዎች ላይ የነበረን አቋሞች
ናቸው፡፡እነዚህን ነጠላ ድርጊቶች፣የደርግን አድሃሪ እርምጃዎች በማጣጋና የኢትዮጵያን
ተጨባጭ ሁኔታ በመመርመር ስለደርግ አጠቃላይ ገፅታ በማህበራችን ተጠቅተዋል፡፡የጦር
ኃይሎች ደርግ ፀረ ፊውዳል እንደሆነና ከፊውዳሉ መደብ ጋር ተፋፋሪ ደረጃ የደረሰ
ቅራኔ እንዳለው ማህበራችን ተናገር ነበር፡፡ከኢምፔሪያሊዝም ጋር ግልጽ ቅራኔ ውስጥ
የገባ መሆኑንም እንደዚሁ፡፡ይህንን ሀቅ አለመቀበል ቢያንስ ሁለት መሰረታዊ ስህተቶች
ያስከትላል፡፡<u>አንደኛ ነገር</u> ዛሬ በኢትዮጵያ ያለውን የመደብ አሰላለፍ አለመረዳትን
ያስከትላል፡፡የጦር ኃይሎች ደርግ በወሰዳቸው ተራማጅ እርምጃዎች ሳቢያ ከፊውዳሎቹና
በፊውዳሊዝም ላይ ጥቅም ካላቸው ወገኖች ጋር ቅራኔ ውስጥ ገብቷል፡፡/ባለመሬቶች፣የቀድ
ሞው ቢሮክራሲ አባሎች፣ጠበቆች ወዘተ./ንብረቶች ወርሶ የመንግስት ሀብት ማድረግ ከስ
ቀባይ ከበርቴውና ከብሄራዊ ከበርቴው የተወሰነ ክፍል ጋር የሚያደርገው ነው፡፡የሶሺ
ያሊዝም መታወጅ ራሱ እንኳ ከተላለቁ ሃይማኖት መሪዎች ጋር የሚያደርገው ነው፡፡ይህን
ካልተገነዘብን ኃይለ ሥላሴን የተቃወመውን ሁሉ እንደገና እንደነበረው ዛሬም ደርግን
የተቃወመውን ሁሉ የሚያስደግፍ ፖለቲካ ልንከተል እንችላለን፡፡ባጭሩ ደርግን የሚቃወሙት
የሬአክሽናሪ ኃይሎች ብቻ ሳይሆኑ ፀረ ሕዝብ ኃይሎችም ጭምር እንደሆኑ መረዳት አስፈ
ላጊ ነው፡፡<u>ሁለተኛ ነገር</u>፣ከላይ ያለነውን አለመቀበል በቅስቀሳና በፕሮፓጋንዳ ደረጃ
ከተጨባጭ ሁኔታ አስወጥቶ ቅዠት ውስጥ ይከታል፡፡ለምሳሌ የሬአክሽን ሰዎች ደርግ
ከቀድሞ ገዥ መደቦች ጋር እየተባበረ የሚሄድ ነው ሲሉ ቆይተዋል፡፡የኢትዮጵያ ገበሬ
ይህን በለማቸው ፍርድ ምንና ስለቀባቸው!!/መሬት ከወሰዱበ የፊውዳል ተገዢ ተሆናለሁ
የምትለዋን ግን ቢሰማ በሳቅ ያልፋቸዋል ለማለት ያስቸግራል/፡፡ባጭሩ ደርግ ከላይ የጠ
ቀስናቸው ቅራኔዎች ውስጥ እንደሆነ ሳንቀበል በእውነት ላይ የተመረኮዘ ቅስቀሳ ለማድ



ረግ አይቻልም፡፡ደርግ ፀረ ፊውዳሊስት ነው ብሎ እዚያው መቆም አይደርቢይነት ነው፡፡ይ
ህን ተቀብሎ ፊውዳሊዝምን ለመደምሰስ የሚችል ኃይል አለመሆኑን ማሳየት ግን ትክክለኛ
ው አቋም ነው፡፡የአብዮቱ ማህበር ደርግን የሚያየው፣ያጋለጠውና የሚያጋልጠውም ከዚሁ
ተጨባጭ ሁኔታ በመነሳት ነው፡፡ይህንንም በቅስቀሳና በፕሮፓጋንዳ ደረጃ ከፍለን እንደ
ሚከተለው ለማጠቃለል እንሞክራለን፡፡

<u>በቅስቀሳ ደረጃ</u>፡ የደርግ ተራማጅ እርምጃዎች የኢትዮጵያ የመደብ ትግል የሚያፋፍሙትን
ያህል፣ፀረ ዲሞክራቲክ አገዛዙ ደግሞ የኢትዮጵያ ሕዝቦች ትግል የወደፊት እድገትና
ግስጋሴ የሚያፍን ነው፡፡በገቢርም የፊውዳሊዝምንና የኢምፔሪያሊዝምን እድሜ የሚያራዝም
ነው፡፡ለፀረ ሬቮሉሽን ኃይሎች ማደራጀት ፋታ የሚሰጥ ነው፡፡ፀረ ሬቮሉሽናዊ ዎላሽ ቢ
ደረግ የሕዝቡን እጅ እስር የሚያስረክብ ነው፡፡ባጭሩ፣የደርግ ፀረ ዲሞክራቲክ አገዛዝ
የሬቮሉሽኑን ኃይሎች የሚጎዳ የሬቮሉሽኑን ጠላቶች የሚጠቅም ነው፡፡ስለዚህም የደርግን
ፀረ ዲሞክራቲክ አገዛዝ ማጋለጥ፣ምንነቱንና በትግሉ ላይ የሚያመጣውን ጉዳት ማሳየት
የተራማጆች ቅስቀሳ ዋና ይዘት መሆን አለበት፡፡በዚሁ አንፃር ደርግን እያጋለጡ፣ለዲሞ
ክራቲክ መብቶች የሚደረገው ትግል እንዲፋፋም መቀስቀስና የሚነሳውንም ትግል እያገዙ
ማደራጀት የተራማጆች አጣዳፊ ተግባር ነው፡፡

በተጨማሪም፣የጦር ኃይሎች ደርግ በየጊዜውና በየሰበቡ ተራማጆችን ማሰሩና እንዳንዶቹ
ንም መግደሉ የታወቀ ነገር ነው፡፡በአሁኑ ጊዜም ደርግ እውነተኛ ተራማጆችን እያሳደደ
በማሰር ላይ ይገኛል፡፡በገጠር ያሉት ብዙ ተራማጅ "ዘማቾችም" እንደዚሁ፡፡
ስለዚህም የታሰሩ የፖለቲካ እስረኞች በፍጥነት እንዲፈቱ መታገል፣የደርግ "የኢትዮጵያ
ትቅደም በደፍ" የተዘዘው በቀዳሚዎች ገዢዎች ላይ ብቻ ሳይሆን በእውነተኛ ተራማጆችና
አገር ወዳዶችም ላይ እንደሆነ ማጋለጥ እንዲሁ አጣዳፊ ተግባር ነው፡፡

የመሬቱን አዋጅ በማስከተሉ በኩል፣ተራማጆች ይህን አዋጅ ሙሉ በሙሉ እንደ
ሚደገፉና ያለምንም ገደብ ሥራ ላይ እንዲውል የሚታገሉ መሆናቸውን ማስታወቅ አለባቸው፡፡
አዋጁንና ደርግን በማስከተሉ በኩል፣የዚህን አዋጅ ያለገደብ ሥራ ላይ መዋል የሚያደናቅፉ
ቀሬታን ነገሮች ሁሉ ማሳየት ያስፈልጋል፡፡የመደራጀት፣የሃሳብ መግለጽ...ነፃነቶችን
የሚገፈው የደርግ አዋጅ የፀረ ፊውዳሊዝም ትግል እንቅፋት እንደሆነ ማሳየት ተገቢ ነው፡፡
ደርግ እየተጠቀመበት ያለው ቢሮክራሲ፣ይህ ከኃይለ ሥላሴ ፊውዳላዊ መንግስት፣የተወረሰ፣
ገበሬውን ለመበዝበዝና ለመጨቆን የቆመ ቢሮክራሲ፣ዛሬ ፊውዳሊዝምን ለመደምሰስ፣ገበሬውን
ነፃ ለማውጣት ለማገልገል እንደማይችልና የአዋጁን አሁን ባለው ሬቮሉሽናዊ መንፈስ
ሥራ ላይ መዋል የሚያደናቅፍ መሆን በሰፊው መገለጽ አለበት፡፡ስለዚህም ገበሬዎች ባለ
መሬቶችን ለመንጠቅ፣የተገኘውን ድል ለማስከበር፣ባጭሩ ፊውዳሊዝምን በሚያዳግም ሁኔታ
ለመደምሰስ በዚህ መደምሰስ ባለበት ቢሮክራሲ ላይ ሳይሆን በራሳቸው ኃይል ላይ ብቻ
መመርኮዝ እንደሚያስፈልጋቸው ማሳወቅ አንዱ ሃላፊነት ነው፡፡ከዚሁ ጋር ተያይዞ አርሶአደ
ሮች የፊውዳሎቹን ፀረ ሬቮሉሽን ለመመከትም ሆነ የራሳቸውን ኃይል ለማጠናከር መታጠቅ
እንዳለባቸው ማስረዳትና ገበሬውን መታጠቅ እንደ ጊዜያዊ የሬቮሉሽኑ ጥያቄ ማስጨበጥ
ሊታለፍ የማይችል የተራማጆች ተግባር ነው፡፡

ደርጉንና ኢምፔሪያሊዝምን በሚመለከተው በኩል፣ተራማጆች ባንድ በኩል ይህ በደርግና በኢምፔሪያሊዝም መሃል ያለው ቅራኔ መሰረታዊ እንዳልሆነ ማሳየት አለባቸው:: በሌላ በኩል ደግሞ በደርግና በኢምፔሪያሊዝም መሃል ያለውን ቅራኔ ለማባባስ ደርጉ በየንግግሮቹ ላይ ያሰፈራቸውን ፀረ-ኢምፔሪያሊስት ዓላማዎች በሥራ ላይ እንዲያውል እየጠየቁ ግፊት ያደርጋሉ::ከዚሁ ጋር ተያይዞ የነዚህን ሥራ ላይ አለመዋል እያጋለጡ፣ደርግና ኢምፔሪያሊዝም መሃል የሚደረገውን ማንኛውንም መቀራረብ እያመለከቱ ፀረ-ኢምፔሪያሊስት ትግሉ እንዲፋፋም ማገዝ ይኖርባቸዋል::

<u>በፕሮፓጋንዳ ደረጃ;</u> የኢትዮጵያን ሕዝቦች ከፊውዳሊዝምና ከኢምፔሪያሊዝም ብዝበዛና ጭቆና ለዘለቄታ የሚያላቅቀው፣ፍትህ ዲሞክራሲና እኩልነት የሰፈነበትን ኢትዮጵያ ለመሰርት የሚችለው አዲሱ ዲሞክራቲክ ሪፐብሊክ ነው::ስለዚህ ሪፐብሊክን መሰረታዊ ለውጥ ሊደረግ አይችልም፣የምንመኘው ያገሪቱን እድገትና ብልጽግና ምኞት ብቻ ሆኖ ይቀራል:: የዛሬው ያገራችን ሁኔታ ለዚህ ሪፐብሊክ ምቹ ሁኔታዎችን እየፈጠረ ነው::በየከተማ የፈነዳው የሰፊው ሕዝብ ሪፐብሊክና ዊ እንቅስቃሴ ገና አላከተመም፣በገጠር የሚካሄደውን የመደብ ትግል የሚያፋፍም የመሬት አዋጅ ወጥቷል::የሪፐብሊኩ ተሸካሚ የሆነው አርሶ አደር በተለይ ትግል ውስጥ ይገኛል:: ታሪካዊ ሃላፊነታቸውን የተገነዘቡ አብዮታዊ ምሁራን ለመደራጀትና ለማደራጀት የሚያደርጉትን ትግል ቀጥለዋል::ስለዚህም፣ይህ ሪፐብሊክን ምን እንደሆነ፣አስፈላጊነቱና ያለርሱ ነፃነትና እውነተኛ ዘላቂ ሰላም ሊገኝ እንደማይችል ማሳየት የተራማጆች ፕሮፓጋንዳ ዋና ይዘት ይሆናል::

ደርጉንና አዲሱን ዲሞክራቲክ ሪፐብሊክን በሚመለከተው በኩል ሰፊው ሕዝብ በደርጉ ላይ እምነት እንዳይጥል መታገል አስፈላጊ ነው::ይህም ማለት ደርጉ በወሳ ኞነቱ ጠቅላላ የሕዝብ ጠላቶች ጋር ሊያብር እንደሚችል ማሳየት ብቻ ሳይሆን፣ደርጉ የዚህን ሪፐብሊክን ጠላቶች ለመደምሰስ የማይችል ኃይል መሆኑንም ማሳየት ጭምር ነው:: ፊውዳሊዝምንና ኢምፔሪያሊዝምን ለመደምሰስ የሚችለው ሰፊው ሕዝብ ራሱ እንደሆነ፣እራሱ ተደራጅቶ እነዚህን ሁለት ጠላቶች በመደምሰስ በወዛደሩ መደብ የሚመራውን እውነተኛ ሕዝባዊ መንግስት እስካላመሰረተ ድረስ የሚፈለገውን መሰረታዊ ለውጦችን ማግኘት ይቅርና እስካሁን የተገኙትን ድሎች እንኳ ዋስትና እንደሌላቸው ማሳየት ሪፐብሊካዊ ሃላፊነት ነው፡አሁን ፊውዳሊዝምን አጥፍቻለሁ ብሎ ደርጉ የሚገለገልበት ቢሮክራሲና የጦር ኃይል ተደምስሰው በሰፊው ሕዝብ የጦር ኃይልና በሰፊው ሕዝብ መንግስት እስካልተተኩ ድረስ፣ተለበሰው ሰፊውን ሕዝብ ለመጨቆን የሚውሉ መሳሪያዎች መሆናቸውን ሰፊው ሕዝብ እንዲያውቀው ማድረግም እንዲሁ አንደኛው ሃላፊነት ነው:



ከዚሁ ጋር ተያይዞ ኢምፔሪያሊዝም በዓለም ዙሪያ ባጠቃላይና በኢትዮጵያ በተለይ ያለውን ጥቅም፣የኢትዮጵያ ሕዝቦች ትግል የዓለም አቀፉ ፀረ-ኢምፔሪያሊስት ትግሎች አካል እንደሆነና በነሱም እንደሚደገፍ፣በመጨረሻም፣ይህ ጠላታችን እንደፊውዳሊዝም ሁሉ በሰፊው ሕዝብ የተደራጀ የረዥም ጊዜ ትግል እንጂ በደርጉ ሊወገድልን የማይችል መሆኑን ለሰፊው ሕዝብ ማሳየት ያበቁ ተግባሮች አካል ነው::

በዚህ ጽሁፍ ባጠቃላይ ደረጃ የደርጉን ድርጊቶችና ጠባይ ከኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ ተነስተን በማጤን አርሱንና የኢትዮጵያን ሕዝቦች ትግል በሚመለከተው በኩል የቅስቀሳችንና የፕሮፓጋንዳችን ይዘት ምን መሆን እንዳለበት ለማሳየት ሞክረናል::አጠቃላይ በመሆኑም ለሚነሱ ጥያቄዎች ሁሉ መልስ ሰጠን አንልም::እያንዳንዱን መደብና የሕብረተሰብ ክፍል/ፀረ-ፊውዳልና ፀረ-ኢምፔሪያሊስ የሆኑትን ማለታችን ነው/ ለይቶ ወስዶ እነሱን በነጠላ የሚመለከተው ቅስቀሳ ምን መሆን እንዳለበት ለምሳሌ አለመረመርንም::ከዚህም በላይ ደርጉን የሚቃወሙ ፀረ-ሕዝብ ኃይሎች ላይ የምናደርገን አምሳይ ስምምነት ሊኖር እንደማይችል በመገመት ታልፏል::ግን እነዚህን በመጪው የሚደረገ ቅስቀሳ ከሁኔታው ጋር መያያዝና የጠንቃቃ ጥናት ያስፈልጋቸዋል::/ለምሳሌ ጠበንጃን ጥያቄ ይዘው ለመነሳት የሚሞክሩ ፊውዳሊስቶችን ለማጋለጥ/::

ለማንኛውም፣ደርጉ ባጠቃላይ ፀረ-ፊውዳሊስት እንደሆነና ከኢምፔሪያሊዝም ጋር ጊዜያዊ ቅራኔ እንዳለው በመገንዘብ፣ተራማጆች ደርጉን በመቃወም የሚያደርጉት ትግል ምን ለመሆን እንደሚችል ለማሳየት ሞክረናል::ደርጉ 'ፋሽስት ነው' በሚል ስያሜ የሚረካው ያደርግ ባይ ወገን ገና ከመጀመሪያው 'የደርግ ደጋፊዎች' ብሎ ማንገብ እንደሚያየን ለመገመት እንችላለን::የኢትዮጵያ ሕዝቦች ትግል ተፋፍሞ፣አዲሱ ዲሞክራቲክ ሪፐብሊክ ተደርጎ፣ የኢትዮጵያ ሕዝቦች በደርጉ ሬሳ ላይ ሕዝባዊ መንግስታቸውን ለማቋቋም የሚችሉበትን የትግል መንገድ ለማስያዝ እውነተኛ ተራማጆች የዛሬው ቅስቀሳና ፕሮፓጋንዳቸው ይዘት ከላይ ለማጠቃለል በሞከርነው መስመር ላይ የተመሰረተ እንደሚሆን እናምናለን::

ከቅስቀሳና ከፕሮፓጋንዳ ጋር የተያያዘውን ዋና ተግባር በሚመለከተው በኩል፣ ከዚህ በፊት ደጋግመን እንዳሳሰብነው ሁሉ፣የተከለው ሪፐብሊክን እንዲደረግ፣የደርጉ ፀረ-ዲሞክራቲክ አገዛዝ ወድቆ ሥልጣን የሰፊው ሕዝብ እጅ እንዲገባ ዛሬ መደረግ ያለበት ተራማጆች እየተደራጁ የወዛደሩን መደብና ሌሎችንም ሪፐብሊክና ዊ ኃይሎች ማደራጀት ነው::ሪፐብሊክናውያን ለመደራጀት የፀረ-ዲሞክራሲ ኃይሎችን ፈቃድ አይጠብቁም፣የፀረ-ዲሞክራሲ ኃይሎች መደራጀትን መከልከል ደግሞ የሪፐብሊክና ዊ ኃይሎችን መደራጀት አስፋጋሪ ያደርገዋል እንጂ የማይቻል ሊያደርጉት አይችሉም::መንግስት ሥልጣን ይዘን፣ቅስቀሳ ከሰበረ እንጂ

እንደራጂለን ስለዚህ .... የሚሉን የአፍ ረቭሉሽናውያን ከትግሉ ዳር ሆነው ወገባ ቸውን እንደያዙ ሊቀሩ ይችላሉ።እውነተኛ ተራማጆች ግን ሕዝቡ ያለ ድርጅት ምንም እንደማያገኝ በመገንዘብ ድርጅት ፈቀደ አለፈቀደ በጽናት ተደራጅተው እያደራጁ የኢት ዮጵያ ሕዝቦች ትግል ወደአዲሱ ዲሞክራቲክ ረቭሉሽን እንዲያመራ መታገል በምንም ዓይ ነት ሰበብ ሊያመልጡት የማይገባ ታሪክ የጣለባቸው ሃላፊነት መሆኑን መገንዘብ አለ ብን።ይህን ታሪካዊ ሃላፊነት በተግባር ላይ ማዋል የጊዜው ዋና ተግባር ነው።

ድሉ የሰፊው ሕዝብ ነው።የአድር ባዮች እድሜ አጭር ነው።



"While we say to the workers:you have to undergo fifteen, twenty,fifty years of civil wars and popular struggles not only to change the relations but to change yourselves and prepare yourselves for political mastery,they tell them on the contrary,'We must come to power immediately, or we can forget about it.' While we make a special point of emphasizing to the German worker the underdeveloped state of the German proletariat,they flatter his national feeling and the craft prejudice of the German artisan, which to be sure is more popular."(Marx in M.E.Werke v.8)

## እንደገና ስለጊዜያዊ መንግሥት

የአውርጃ ማህበር መጽሄቶች በዚህ ዓመት በዙ ጊዜ ተመላለሰው ስለዚህ ጥያቄ ጽፈዋል።ይህ መንግሥት ሊቋቋም ይችላል፣ስለዚህም አስቸኳይ ጥያቄ ነው የሚል አቋም ነት ናርን ሳይሆን፣በዚህ ወሬ ያለ ሰቢያ የተነሱትን ስህተቶች ለማጋለጥ፣ይህ ፍጹም ቦታ የሌለው ወሬ ያለ የሚያፍናቸውን አጭበርና ቀውሚያ ያላቸውን ወሬ ያሉት ለማጋለጥ ብቻ ነው።አሁንም በዚህ ጥያቄ ላይ ስንመለስ ከዚሁ ከቀየ ገባችን ተነስተን እንደሆነ አርእስቱ ራሱ የሰላቸው አንባቢ ሊረዳን ይገባል።

ይህ ወሬ ያለ እንደተነሳ፣"ፈረስ ከጋሪ አይቀድምም፣ሰፊው ጭቁን ሕዝብ መንግሥት ሥልጣን የሚያስጨብጠው ድርጅት ሳይኖረው መንግሥት ሥልጣን ለመያዝ ስለማይችል ለዚሁ ታገል ማለት አይቻልም።መንግሥት ሥልጣን ለመጨበጥም ሆነ ዲሞክራቲክ መብቶችን ለማስከበር መጀመሪያ ድርጅት ስለሚቀድም የዛሬው ትግል ዋና ግብ መደራጀትና ማደራጀት ነው።" ብለን ነበር።ነገር ግን አስከምናውቀው ድረስ ከኢትዮጵያ ተራማጅ ድርጅቶች በዙዎቹ ይህን ወሬ ያለ ማንበታቸው አለቀረም።ማህበራችን አስከዛሬም በዚሁ አቋሙ ላይ ጸንቶ ቀይቷል።አሁን ግን ከጥቂት ወራት ወዲህ ከአገር ቤት ይህ ወሬ ያለ አይሰማም። እና አባምናቸው ለማለት ሳይሆን፣እውነተኛ ተራማጆች ካለፉት አሥራአንድ ወራት የራባቸው ትግል ይህ የጊዜያዊ መንግሥት ወሬ ያለ ኪንዴማጊካው ፍጹም ጊዜያዊ አንዳል ሆነና ጊዜያዊውን ትግል እንደሚያደናቅፍ ለረቁ በቻሉ አያስገርመንም።ኢትዮጵያን የሚገ ዛው ወታደራዊ ደርግ ይህን የተባባተ ወሬ ያለ ይዘው በተነሱ ገን ሀቀኛ የሕዝብ ወገን በሆኑ አንዳንድ ግለሰቦች ላይ የወሰደው ኢሰብአዊ እርምጃ ራሱ እንደሚያሳየው ያለፖለቲካ ድርጅት ለመንግሥት ሥልጣን ለመታገል መነሳት "ምን ይዞ ገዞ" እንደሚሆን ሳይረዱት የ ሚቀር አይመስለንም።የተራማጆች ትግል በአንድ አቅጣጫ ኃይሉን አጠናክሮ መቀጠል ባለበት ሰዓት ብሁኑ ጊዜ፣አገር ቤት ያሉ ተራማጆች ይህን ፍጹም ጊዜያዊ ያልሆነ ግን ጊዜያዊ

አጫጭሬ ተግባር የሚሸፍን ወሬ ያለ ፕለውጥ ወጃወሬያ የመንግስት ሥልጣን መጨበጫ መሳሪያ የሆነውን ድርጅት ለመፍጠር፣ተደራጅተው ለማደራጀት በሚያደርጉት ትግል ላይ በመቸውም የ በለጠ እንደሚያተኩሩ ተስፋችንም እምነታችንም ነው።።

በእዚና ወሬያች አካባቢ ያሉት አድርባዮች ግን ይህን ፍጹም ጊዜያዊ ያለ ሆነ ግን ጊዜያዊ ተግባርቸን የሚሸፍን ወሬ ያለ ይዘው ለሰው ሁሉ እየተወ ሲሄዱ ውየኝ በሉበት ምንም አይገርመንም።።ወደኋላ ዞር ብለን ከቀድሞው የነበሩትውን ፖለቲካ በንመለከት አድኅሚውንና ሃይ ሃይ የሌለበትን የረበሹትን ተግባር መዘለል ለማቸው እን ይሆን እንረዳለን።።ጊዜያዊ ያለሆኑ ወሬ ያሉቸ አያነሱ በሬቮሉሽናዊ ቀጸሎች እያስመወራ ባደ ቦታ ሆይ ሆይ ማለት የተዋሀዳቸው ነገር መሆኑን እንገነዘባለን።።

ከየፔት ዓመታት በፊት ፍጹም'ገሬ ቀደም በመሆን ኢትዮጵያ ውስጥ 'ሕዝባዊ' ጦርነት ለመጀመር በጣም አመቺ ጊዜ ነው።። sieze the time sieze the gun ይሉ ነበር።።ያኔ ማህበራችን 'የኢትዮጵያን ሕዝብ ነፃ ማውጣት የራሱ የሕዝቡ ሥራ መሆን አለበት።።በለዚህ የኛ ተግባር ሕዝቡን ተከተን አርሱኑ ነፃ ለማውጣት ጠመንጃ ለመንከስ መሽቀዳደም ሳይሆን የሰፊውን ሕዝብ የፖለቲካ ንቃት ከፍ ለማድረግ፣መደራጀቱንም ለማገዝ በሬ ቀስቀሳ በማድረግ ለራሱ ጦርነት ብቁ እንዲሆን መታገል ነው በሉትም ነበር።።ምንም እንጂ እነሱም ከመሃላቸን ሳይጠፉ፣በጦር ትግል የሚያምኑ የወንበር ሬቮሉሽናውያን፣ወዘተ. በሚሉ ስድቦች ተወስነው 'አያጋልጡን' 'በትሬበትነት' /የትሉ ቋንቋ/ ቀዩ።።ዛሬ ደግሞ የኢትዮጵያ ሁኔታ ፍጹም አብዮታዊ በመሆኑ፣የሰፊው ሕዝብ ትግል ከፍተኛ ቦታ በመድረሱ፣በዚህም ትግሉ በርከት ያሉ ድሎች በማግኘቱ፣ትግሉን ከፍጻሜ ለማድረስ ለሕዝባዊ ጦርነት መዘጋጀት ማዘጋጀቱ በዓት በርግጥ ሲደርስ ሲሸሉ ጦርነት የሚያስቀር ጊዜያዊ መንግስት ይምጣ ይሉ ገቡ።።ጦር ጦር ባሉበት አፋቸው ጦርነቱ በመጣ ሰላም ሰላም ይሉ ጀምረዋል።።

የየካቲት እንቅስቃሴ ከተነሳ በኋላ እንጬ የተጨበጠ አቋምና ፖለቲካ መከተል አቀቷቸው እንደነበረ ባለፈው ዓመት የወጣው ቡለቲን በዘመኑ አትሞቹ ዘመን ለቀ ለቀ አጅዎች ይዞ መውጣቱ ምስክር ነው።።ጊዜያዊ መንግስት የሚለ ወሬ ያለ በማግኘታቸውና በተ ለይም በአገር ቤት መስፋፋቱ ደስ ሲያሰኛቸው አልቀረም።።አድኅሚውንና ትእግስት የራቀነት የሚጠይቀውን የመደራጀትና የማደራጀት ተግባር የሚያስዘለል ወሬ ያለ በመሆኑ ማለታቸን ነው።።እንደማገናዝበው ሬቮሉሽነን ወከዓት ሲፈልገ አይደራጅ አለ ባይ አድሃሪ ሁሉ፣ ያኔ ሕዝቡን ነፃ ለማውጣት ጦር እናንሳ ባዮች ዛሬ ደግሞ 'የለም ጦርነቱ ይቅር፣ሕዝቡን ነፃ ለማውጣት ወጃወሬያ የመንግስት ሥልጣን እንያዝ' ማለታቸው ያው የቀድሞው ፖለቲካቸው ተቀ ጥያ በለሆኑ እኳሉ ወሬ ያለ ከነማምታቸዋል።።



ከአድር ባዮች ጋር 'ሕዝብ'በለሚለው እንኳ በምምነት ሊኖር አይቻልም።። ቀደሞ 'ሕዝባዊ' ጦርነት ያሉት የነሱኑ ጦር ይዞ ውር ውር ማለት እንጂ የሰፊውን ሕዝብ የተደራጀ የጦር ትግል አልነበረም።።ዛሬም 'ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግስት' የሚሉን የነሱንና የመሰሎቻቸውን መንግስት እንጂ ሰፊው ሕዝብ ተደራጅቶ አራሱ ታግሎ የሚመሰርተውን አይደለም።።ባጥሩ እንደ 'ሕዝባዊ' የሚየጥሩት ራሳቸውንና መሰሎቻቸውን ነው።።በነሱ ገጸት ሰፊው ሕዝብ እነሱ 'ነፃ' የሚያወጡት የሚገውለት <u>ሕዝብ</u> እንጂ፣መንግስት ሥልጣን ይዞ መብቱን ከበሬን የሚያስጠብቅለት <u>ሕዝብ</u> እንጂ አራሱን በራሱ ነፃ የሚያወጣ፣አራሱ በጎዛ እጁ የወደፊት እድሉን ለመወሰን የሚነሳ <u>ሕዝብ</u> አይታያቸውም።።ከሰፊው ሕዝብጋርና ከሰፊው ሕዝብ ጋር የሚደረገው ትግል ሳይሆን <u>ሕዝቡን ተክቶ</u> የሚደረገው ትግል የሚታያቸው ለዚሁ ነው።።ለመጃወሬያው ተአገበተ፣የራቀነትና እውቀት ያስፈልገዋል።።ለሁለተኛው ግን ዥራና እለሁ እለሁ ባይነት ይበቃዋል።። የውጭው ንቅናቄ አድርባዮች በሰደድና በጐራ አገደና፣ ወገ ባለው የቀስቀሳ ሥራና ባይገባዊ ተንተና ግን ሁሉ የሚሆኑት ም ለዚሁ ነው።።

ወደ ጊዜያዊ መንግስት ጥያቄ እንምጣ።።ይህ ወሬ ያለ የሰፊው ሕዝብ ጥያቄ ሳይሆን አርግጥ በሰፊው ሕዝብ ስም በለቀ ለቀ የንዑስ ከበርቴ ከፍሎች /የቀህርሲቲ አስተማሪያችና ተማሪያች፣የሊሆስግ ወሬያች/ የቀረበ ጥያቄ መሆኑን ደጋገ ወገ ከማሳየታችንም በላይ ሁሉም የሚያውቀው ነገር ነው።።የእዚና ወሬያችና መሰሎቻቸው እንደሰፊው ሕዝብ ጥያቄ ለማቅረብ በቀከረም ሕዝብ ሲሉ ይከው ከአጠገባቸው ያለውን የንዑስ ከበርቴ ክፍል እንደሆነ ገለጸ ነው።።በሌሎች ጸሁፎቻችን ይህን ከወታደሩ ጋር ተሻክረው ሥልጣን ለመያዝ ከቸኩሉ ንዑስ ከበርቴዎች የረለቀ ወሬ ያለ ከታላቁ ሌኒን ሬቮሉሽናዊ ቲዎሪ ያገኙት ለማስመሰል የሚያደርጉትን ሙከራ አጋልጠናል።።ለምሳሌ ባለፈው ተገላቸን ዜና ሌኒን በጦር ትግል የሚደገፍ ጊዜያዊ መንግስት አላለም፣የወዛደሩና የገበሬው ዲክታተርነት መንግስት ነው ያለው ወዘተ. ያሉትን ከራሱ ከሌኒን ጸሁፍች በሰፊው እየጠቀስን ውሸታቸውን አጋልጠን ነበር።።

ይህን ሙከራቸውን አልተውትም።።ለምሳሌም በለጊዜያዊ መንግስት በተፃፈ ቀጥር ሳይጠቀሷት የማያልፏት እንድ የሌኒን ጥቅስ አለች።።ይዘቷን እንገቢ በዝንብ እንዲያለን በሰፊው እንጠቀሳታለን።።

Replying to the anarchists' objection that we are putting off the socialist revolution,we say:we are not putting it off,but are taking the first step towards it in the only possible way,

along the only correct path,namely,the path of a democratic republic.Whoever wants to reach socialism by any other path than that of political democracy,will inevitably arrive at conclusions that are absurd and reactionary both in the economic and political sense.(Lenin,C.W. Vol.9 p.29)

ይህ ጥቅስ የተወሰደበትን ጽሁፍ ሁሉ ሳይሆን ጥቂቱን ብቻ በመመልከት ለናስተውል የምንችለው ሁለት ነገር አለ፡፡አንደኛ፤ይህ የሌኒን ጽሁፍ በተጻፈበት ጊዜ በሩሲያ ይካሄድ የነበረው ሶሺያሊስት ሳይሆን ዲሞክራቲክ ሬቮሉሽን እንደነበረ፤ሁለተኛ፤ከለዚህ ዲሞክራቲክ ሬቮሉሽን ወደሶሺያሊስት ሬቮሉሽን ማለፍ እንደማይቻል፡፡የተሟላት አናርኪስቶች ወዛደሩ ለሶሺያሊስት ሬቮሉሽን ቃገሉ የራሱን ዲክታተርሺፕ ይመሰርታል እንጂ በዚህ ሬቮሉሽን በፊት የመንግስት ሥልጣን መጨበጥ የለበትም ይሉ ነበር፡፡በዚህ ጽሁፍ ሌኒን ለነሱ በመልስ፤እርገጥ ወዛደሩ የራሱን ሬቮሉሽን አርጎ የራሱን ዲክታተርሺፕ የሚመሰርትበት ሬቮሉሽን ሳይሆን፤ከሌሎች ጋር ሥልጣን ተጋርቶ በዚህ ሬቮሉሽን ካለፈ ወደ ሶሺያሊስት ሬቮሉሽን ማለፍ አይችልም ይላቸዋል፡፡በሌላ አነጋገር ይህ መንግስት የሩሲያ ሬቮሉሽን የዲሞክራሲያዊ ደረጃ ሬቮሉሽን /ዲሞክራቲክ ሬቮሉሽን/በኋላ እንጂ የሶሺያሊስት ሬቮሉሽን እንዳልሆነ ይናገራል፡፡ይህን በዚህ ጽሁፍ ውስጥ በብዙ ቦታዎች ልቅስታል፡፡ከላይ ያየነው ጥቅስ በሌኒን ጽሁፍ ከመምጣቱ ሁለት መስመር ከፍ ብሎ እንዲ "ሶሺያሊስት ሬቮሉሽን ከጥያቄ ውጭ ነው" ይላል፡፡ጥቂቶች ለምሳሌ ያህል ለመስጠት፡፡

"Moreover,we must outline for such a government a programme of action that will conform with the objective conditions of the present period and with the aims of proletarian democracy,This programme is the <u>entire</u> minimum programme of our party"..."
(ibid.p.27 Lenin's emphasis)
"...a <u>victorious</u> popular insurrection and the <u>establishment</u> of a provisional government would signify the victory of the revolution <u>in actual fact</u>..."(ibid. p.33 Lenin's empasis)

ለመደምደም፤ለሌኒን ይህ መንግስት የጦር ትግል ተከታዩ፤ዲሞክራቲክ ሬቮሉሽን ተከታዩ፤የወዛደሩን ጋር ቱ <u>ዝቅተኛ/ሚኒሞም/ፕሮግራም</u> ከሥራ ላይ የሚያውል መንግስት ነው፡፡



ይህ ሌኒን ያለው ጊዜያዊ መንግስትና የነሌዘና ጊዜያዊ መንግስት የሚመሳሰሉት "ጊዜያዊ" በምትለየ ቃል ብቻ ነው፡፡በአመጣጥ፣በተግባር፣በሬቮሉሽን ደረጃዎች ላይ በተሰጣቸው ቦታ ፍጹም አይመሳሰሉም፡፡ የኢትዮጵያ ወዛደር ዝቅተኛ/ሚኒሞም/ፕሮግራምና ከፍተኛ/ማክሲሞም/ ፕሮግራም ከነሌኒን ጋር በመሰረቱ የሚለይ አይሆንም፡፡ የኢትዮጵያ ወዛደርም በቀጥታ ሶሺያሊስት ሬቮሉሽን ማድረግ ስለማይችል በዲሞክራሲያዊ ዲሞክራቲክ ሬቮሉሽን ያልፋል፡፡<u>ስለእነሱ ዲሞክራቲክ ሬቮሉሽን ወደሶሺያሊስት ሬቮሉሽን መሸጋገር አይችልም፡፡</u>ይህ እነሱ ዲሞክራቲክ ሬቮሉሽን የወዛደሩን <u>ዝቅተኛ ፕሮግራም</u> ከሥራ ላይ የሚያውል ነው፡፡ ከዚህ ሬቮሉሽን በኋላ የሚመሰረተው መንግስትም የወዛደሩ ብቻ ዲክታተርነት ሳይሆን ከሌሎች የዚህ ሬቮሉሽን ተካፋዮች ጋር ሥልጣን የሚጋራበት መንግስት ይሆናል፡፡ሶሺያሊዝምን ለማምጣትና የወዛደሩን ብቻ ዲክታተርነት ለመመስረት የሚደረገው ትግል ከዚህ ሬቮሉሽን በኋላ ይቀጥላል፡፡በኢትዮጵያ ጊዜያዊ መንግስት የሚለው መፈክር ቢነሳ ሶሺያሊስት ሬቮሉሽን ነው መደረግ ያለበት በሚል የተያዘ አናርኪስት የለም፡፡ይህን መፈክር የተያዘም ነው እንዲ ምክንያት፤በእኛ ዲሞክራቲክ ሬቮሉሽንና ባሁኑ ጊዜ መሃል እንዱ የጊዜ ክፍል ስርዐት ዘመን መንግስት ለናር የሚችል በማስመሰል፣ የኢትዮጵያ ሬቮሉሽን ደረጃዎች ሁለት/እኛ ዲሞክራቲክ ሬቮሉሽንና ሶሺያሊስት/ሆነው ሳሉ ሶስት በማስመሰል .ትክክለኛውን የሬቮሉሽን አካሄድ ስለሚያዛባ፤በለዚህም በኢትዮጵያ አሁን መደረግ ያለበትን ዲሞክራቲክ ሬቮሉሽን ስለሚያደናቅፍ ነው፡፡ከላይ የጠቀስነው የሌኒን አባባል ዛሬ በኢትዮጵያ ጊዜያዊ መንግስት ለሚያውጁ ሊስነዘር የማይችለውም ለዚህ ነው፡፡ይህ በጣም ግልጽ ስለሆነ አጽርጣቶች ይጋገሙ የሚጠቅሷት ወይ አለገባቸው ወይም አውቀው ለማደናገር ነው፡፡

ለመጨረስ ላይም እንዲሁ ልዩነት እንዳለ ደጋግመን አሳይተናል፡፡ የሌኒን ጊዜያዊ መንግስት በጦር ትግል የሚመጣ ነው፡፡ የነሌዘና ጊዜያዊ መንግስት ግን ደግሞ የሲቪል ጦር ነት ለማስቀረት በሕዝባዊ ድርጅቶች የተ ወጣጣ፡ በምርጫ የሚመጣ ነው፡፡ሌኒንማ እንዲህ ይላል፡፡

"But what you(Menshevics) speak of is not called a"provisinal revolutionary gowernment": tnat (provisional revolutionary government) is the name givento the government of a revolutionary epoch, one that immediately replaces the overthrown government <u>and rests on the people's insurrection and not on some kind of representative institution coming from the people.</u>"( ibid.p.42-43. Emphasis and words in brackets ours)

ይህ በዚህ ይበቃና ወደሌሎች የዚህ መፈክር መደገፊያ ስንገባ ምክንያቶች እንለፍ፡፡

አንደኛው የመከራከሪያ ዛሬ የደርግን ፀረ ዴሞክራቲክ አገዛዝ የሚመለከት ነው፡፡ ወይ ይህን ወሬ ቃል ያነሱ በነቶች እየተገደሉ እየታሰሩ እንዴት ተያውማሳቸውእያ እንደ ወንገል ስበክ የፖለቲካውን ጥያቄ የመሬል ጥያቄ ያረጉታል፡፡አለዚያ ያሉት አድርባዮች ይህን ወሬ ቃል ተቻተን እንዳንገድፍ ሲገዙትን እንዲህ ይላሉ፡፡

Every word you write against this basic demand of the masses gives more ammunition(...)to the oppressors."(Algeria,Our stand etc.p10)

ወይም ደግሞ የደርግ አገዛዝ ዴሞክራቲክ አይደለም፤ከሱ የሚሻል ሌላ የገዐ ከበርቴ መንግስት ምን ይገኛል? ስለዚህም የእዚና ወሬያች እንደሚሉት ውሉ ከዚህ ፀረዴሞክራቲክ ገዐ ከበርቴ ሻለ ያለውን ገዐ ከበርቴ ምረጡ ይላሉ፡፡ይህም ሌኒን እንዳለ በተጨባጭ ሁኔታ ላይ ሆኖ ያለውን ተዘ ያበናል፡፡

" !We must choose'- thisis the argument the opportunists have always used to justify themselves,and they are using it now....We must not be utopians and strive after big things.We must be practical politicians;we must join in the demand for small things,and these small things will facilitate the fight for the big ones.We regard these small things as the surest stage in the struggle for big ones. That is how all the opportunists,all the reformists argue;unlike revolutionaries."(Lenin C.W. Vol.11 p.69)

ከምናት ዓለም ሆነን ካየነው ከፀረዴሞክራቲክ አገዛዝ ዴሞክራቲክ አገዛዝ ይሻላናል፡፡ከአት ዓለምያ ጊዜያዊ ተጨባጭ ሁኔታ ተነስተን ነገሩን በገመለከት ግን ዛሬ እንዲህ ዓይነት ምርጫ አይቀርብልንም፡፡ለዴሞክራቲክ አገዛዝና ዴሞክራቲክ ስርዐት አስፈላጊ የሆኑት ሁኔታዎች ገና አልተሟሉም፡፡በሬው ሕዝብ ወደመንግስት ሥልጣን የሚወጣበት መሰላል የለም፡፡ማለት ሕዝቡን የመንግስት ሥልጣን የሚያስይዘው፤ዴሞክራቲክ ወይ ዞ ለማስከበር የሚያታገለው የፖለቲካ ድርጅት የለም፡፡ሕዝብ ያለውን የመንግስት ወኪና የሚያስከብርበት፤የተገኙ ድሎችን የሚያስከብርበት የተደራጀ ሕዝባዊ የጦር ኃይል የለም፡፡ዴሞክራሲያዊ አገዛዝ፤ዴሞክራሲያዊ ስርዐት ሊኖር የሚችለው እነዚሁ ሁሉ ሲሟሉ ነው፡፡እነዚህ ሳይሟሉ ዴሞክራሲ ስርዐት ወይም አገዛዝ ይኖራል ማለት አራስም ተታሉ ሌሎችንም ማታለል ነው፡፡

በ1905 በሩሲያ ስሬ አብዮታዊ እንቅስቃሴ እየጠነከረ ሲሄድ ባለ በዚሁ በዴሞክራሲ ጥያቄ ላይ በነሌኒንና በአድርባዮች መካከል ልዩነት ነበር፡፡ልዩነቶችን በግልጽ ለማስቀመጥ ሌኒን በጥያቄ መልክ መልክ ካስቀመጣቸው 11 ነጥቦች መሃል አንደኛው፤



**10.Shold we call upon the people immediately to elect,on the basis of universal suffrage,bodies of revolutionary self-government and through these a constituent assembly?(V.9,p264)**

የአድርባዮች መልስ "አዎ" ነበር፡፡የነሌኒን መልስ የሚያወላውል "የለም" ነበር፡፡ታዲያ ሌኒን የፈለገው ቀጥ አገዛዝ ደጋፊ ሆኖ ነው? ዴሞክራሲን ጠላት ነው? ይህ ለእዚና ወሬያችም የሚመስል አይደለም፡፡የሚመኘውንና የመደብ ትግሉ ያለበትን ደረጃ ስለማያሟሉ ነው፡፡በዚያን ጊዜ ሩሲያ ሁኔታ፤ለዴሞክራሲ አስፈላጊው ሁኔታ ባልተሟላበት ደረጃ፤ከረፍርሚስቶች ጋር ለይስሙላ ዴሞክራሲ ወምጫት እየታገሉ ሕዝቡም ከማታለል ይልቅ፤ለእውነተኛ ዴሞክራሲ ትግሉን መቀጠል እንዳለበት፤በመጀመሪያ ለእውነተኛ ዴሞክራሲ መኖር አስፈላጊ የሆኑ ሁኔታዎች እንዲሟሉ ማድረግ እንዳለበት ስለተገነዘበ ነው፡፡ከሁሉም በላይ ለዴሞክራሲ የሚያስፈልገውን ሁኔታ ማሟላት ማለት ደግሞ የዴሞክራሲን ጠላቶች በሚገባ መደምሰስ ማለት ነው፡፡በዚያን ጊዜ ሩሲያ ፈላጭ ቆራጭ አገዛዝንና የመንግስት መኪናውን፤የፊውዳሊዝምን ርዝራዥ መደምሰስ ማለት ነበር፡፡በአገራችንም በአሁኑ ጊዜ ዴሞክራሲን ጠላቶች መደምሰስ ማለት፤ለዴሞክራሲ አስፈላጊ የሆኑትን ሁኔታዎች ማሟላት ማለት፤ከሁሉም በላይ ፊውዳሊዝምንና ኢምፔሪያሊዝምን መደምሰስ ማለት ነው፡፡እነዚህ ሁለቱ ጠላቶቻችንና ዴሞክራሲ በፍጹም በአንድ ጣራ ስር ሊኖሩ አይችሉም፡፡ስለዚህ እነዚህ ጠላቶቻችን ሳይደመሰሱ በአገራችን ከፀረዴሞክራቲክ አገዛዝና ከዴሞክራቲክ አገዛዝ ምረጡ የሚል ጥያቄ ለእውነተኛ ተራማጆች ሊነሳ አይችልም፡፡ለይስሙላ ዴሞክራሲ ወይስ ለእውነተኛ ዴሞክራሲ እንታገል፤የሚል ሁለት የተገለ መንገድ ግምር/አንድ የአድርባይ አንድ ሬቮሉሽናሪ/አለ እንጂ ከፊውዳሊዝምና ከኢምፔሪያሊዝም መደምሰስ በፊት አገራችን ጠብቅ ዴሞክራሲያዊ ስርዐት ሊሰፍን ስለማይችል፤ ከዴሞክራሲና ከፀረ ዴሞክራሲ ምርጫ አልቀረበልንም፡፡ የይስሙላ ዴሞክራሲ የፈለገ፤አሁኑኑ ምርጫ ይደረግ፤ፊውዳሊዝምና ኢምፔሪያሊዝም ሳይደመሰሱም የመንግስት ሥልጣን እንያዝ ሊል ይችላል፡፡ለእውነተኛ ዴሞክራሲ የሚታገለው ወገን ግን ፊውዳሊዝምንና ኢምፔሪያሊዝምን ለመደምሰስ የሚችለውን የሕዝብ ኃይል እንደራጅና ትግሉን እንቀጥል፤በሬው ሕዝብ ተደራጅቶ፤ገዢዎቹንና ተቀጽላ ከና አድርጉ ጠላቶችን ካልደመሰሰ ከዚህ የዱሮ ዴሞክራሲ አይኖርም ይላል፡፡በሌላ አነጋገር ልዩነቱ የሚነሳው ዴሞክራሲን በመፈለግና ባለመፈለግ ወሃል ሳይሆን ለእውነተኛ ዴሞክራሲ ወይም ለይስሙላ ዴሞክራሲ በመታገል ላይ ነው፡፡

ሌላኛው የመከራከሪያ ነጥብ፣ደርጉ በአንፃራዊነት ሥልጣን ላይ ወጣ፣ከዚያም
ወዲህ ፀረ-ዲሞክራቲክ በሆነ መንገድ ይገዛል::ስለዚህ አሁኑኑ ወርዶ በ"ሕዝባዊ" መን
ግሥት እንዲተካ ካልጠየቃችሁ ደርጉ ሥልጣን ላይ እንዲቆይ መደገፋችሁ ነው የሚለው ነው::

የየካቲቱ ሰፊ ሕዝባዊ እንቅስቃሴ የቀደሞ ገዥ መደቦችን ገፍቶ የመንግስት ሥል
ጣን በሰፊው ሕዝብ እጅ ያልገባው ሰፊው ሕዝብ የመንግስት ሥልጣን ለመያዝ ያልተዘጋጀና
ያልተደራጀ በመሆኑ ነው::ዛሬም ቢሆን የፈለግነውን ያህል ደርጉ እንዲወድቅልን ብን
መኝ ሰፊው ሕዝብ የመንግስት ሥልጣን ለመያዝ እስካልተደራጀና እስካልተዘጋጀ ድረስ ደር
ጉን ከመንግስት ስልጣን ሊጥል አይችልም::ደርጉ እንደቀደሞ የገዥ መደቦች በሰፊው ህዝብ
ተገፍቶ ቢቢያ በወደቀ እንኳ የኢትዮጵያ ሕዝቦች ለመንግስት ሥልጣን እስካልተዘጋጁና እስ
ካልተደራጁ ድረስ የመንግስት ሥልጣን እንዲሁ በወታደሩ የተደገፈ አንዱ አምባገነን ቡድን
እጅ እንጂ በሰፊው ሕዝብ እጅ ሊገባ አይችልም::ባጭሩ ረዥም ጊዜ ላይ ያለመሰላል መው
ጣት የማይቻለውን ያህል ያለፖለቲካ ድርጅትም ሰፊው ሕዝብ የመንግስት ሥልጣን ላይ ለመ
ጣ አይችልም::

አንዱን ገበሬ እንደምሳሌ እንውሰድ::እህል ለማፍራትና ከችግሩ መውጣት
ይፈልጋል::መሬት አገኘ እንበልና ማረሻ ግን የለውም::በዚህ ሁኔታ በተቀዳሚ ማረሻውን
ያዘጋጅና አርሻውን መጀመር ይችላል::ማረሻውን ሳያዘጋጅ ግን "አርሻዬ ይፉር" ብሎ ቢጸ
ፍኮር አያረግም::በዚህ ምሳሌ ማረሻው ለገበሬው ያለውን ተርጉም ያህል የፖለቲካ ድር
ጅትም ለሰፊው ሕዝብ አስፈላጊ ነው::የፖለቲካ ድርጅት የሰፊው ሕዝብ የመንግስት ሥልጣን
መያዣ መሳሪያው ነው::ካለዚህ መሳሪያው የመንግስት ሥልጣን አጠገብ ድርሽ ሊል አይችልም::
ካለዚሁም ወደድንም ጠላንም ይህ የፖለቲካ ድርጅት ተፈጥሮ ሕዝቡን ለመንግስት ሥልጣን
እስካላዘጋጀ ድረስ ደርጉ ይገዛናል::የመንግስት ሥልጣን በሰፊው ሕዝብ እጅ እንዲገባ
የሚፈልግ ዛሬ ማድረግ የሚችለውና ማድረግ ያለበትም ይህን የመንግስት ሥልጣን መጨበጫ
መሳሪያ መስራት መጀመር ነው::ማለትም አሁን የኢትዮጵያ ተራማጆች አጣዳፊ ተግባር
መደራጀትና ማደራጀት ነው::"ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግስት" እያሉ የሚጮሁትም ደርጉንም
ፋሺስት እያሉ እናገም የደርግ ደጋፊዎች እያሉ በመሳደብ ለመርካት ነው እንጂ ደርጉን
ሊያስወግድ በመጨረሻም ሊጥል የሚችለው የተደራጀ ሕዝባዊ ኃይል ብቻ ሊሆን እንደሚችል
መረዳት ይህን ያህል የሚከብዳቸው አይመስለንም::."ደርጉ እንዴት ይወድቃል" የሚል ጥያቄ
ለራስ አቅርቦ መልሱን በተጨባጭ መንገድ መፈለግ ይበቃዋል::

እዚህ ላይ አንድ የታሪክ ምሳሌ በመጥቀስ ነገሩን የበለጠ ያብራራል::
በየካቲት 1917 የሩሲያ ሰፊ ሕዝብ ባደረገው ታላቅ ትግል ቢቢያ ፈላጭ ቆራጭ



የነጋሢ መንግስት ይወድቃል::ሌኒን እንዳለው የወዛደሩ ፓርቲ ሕዝቡን በሚገባ ስላላ
ደራጀውና ስላላዘጋጀው፣የፊውዳሊስቱ ኃይሎች በሚገባ ስላልተመናከሩ፣የመንግስት ሥልጣን
በሰፊው ሕዝብ እጅ/ ማለትም በወዛደሩና በደሃ ገበሬው እጅ / ሳይሆን በከበርቴው እጅ
ይወድቃል::ከበርቴውም "ጊዜያዊ መንግስት" ይመሰርታል::ይህ የከበርቴው ጊዜያዊ መን
ግስት ፍጹም ፀረ አብዮታዊ ነበር::እነሌኒንን ሊገድል ወይም ሊያስር ያሳድድ ነበር::
/አድርባዮች ልብ ብላችሁ ስሙ፣ቁራሉና የፖለቲካ ጥያቄ እንደሚለይ ለማሳየት ነው
ይህን የሌኒንን ለመግደል መፈለግ ያነሳነው::/

ሌኒን በሩሲያ ወዛደር ፓርቲ ማእከላዊ ኮሚቴ ክሜካፍነት የሚከተ
ለው በሰፊው የምንጠቅሰው ውሳኔ እንዲያልፍ ያደርጋል::

"The slogan 'Down with the Provisional Government'is an inco-
rrect one at the present moment beacause,in the absence of a
solid (i.e.,a class-consciuus and organized) majority of the
people on the side of therevolutionary proletariat,such a slo-
gan is either an empty phrase,or,objectively,amounts to attem-
pts of adventurist character.
"We shall favour the transfer of power to the proletarians and
semi-proletarians only when the Soviets of workers' and Soldie-
rs' Deputies adopt our policy...(Lenin,C.W.Vol 24 p.21o-11.
Our Emphasis).

ሌኒን የዚህን ፀረአብዮት መንግስት መውደቅ ባይፈልግ ኖሮ እንዳለሁ፣
ወይንም ይህን መንግስት ስለሚደግፍ እንዳለሁ፣ ሰው ያለውን እንደሚፈልግ ለማመን ያለ
አስበረይ ለማይቻለው ለአስደራጊያ አድርባዮች እንኳ ገለጽ ይመስለናል::ሥልጣን በሰፊው
ሕዝብ እጅ የሚገባበት ሁኔታ ሳይሟሏ፣ሌኒን "ሥልጣን ለሰፊው ሕዝብ አሁን" ብሎ ቢጽ
ጫፍ የማይወሀ ሬቮሉሽናዊ ስለነበረ ነው::ስለዚህም የጊዜው ዋና ተግባር "ሥልጣን ለሰ
ፊው ሕዝብ አሁኑኑ" እያሉ መጮህ ሳይሆን ይህ ሁኔታ እንዲሟላ ማለት ሥልጣን በሰፊው
ሕዝብ እጅ የሚገባበት ሁኔታ እንዲፈጠር ትግሉን መቀጠል እንደሆነ ሲያስረዳ እንዲህ
ይላል::

የጊዜው ዋና ስሎጋኖች ብሎ በጠቀሳቸው አራት ነጥቦች ሁለቱ የከበርቴውን
ጊዜያዊ መንግስትና ሬቮሉሽኑን የከዱትን አድርባዮች ማጋለጥ መሆኑን ከሳዩ. በኋላ:-

"...(3)To carry out propaganda and agitation from group to group in every regiment, in every factory, ...(4) To organize, organize and once more organize the proletariat, in every factory, in every district and in every city quarter." (ibid. Lenin's emphasis)

ይህ የጊዜው ተቀዳሚ ተግባር እንደሆነ ካለየ በኋላ፣ የነሌኒን ፓርቲ ተግባራቸውን በሚገባ በመፈጸም ይሆን መንግስት ቶሎ ሥልጣን ወደሰፊው ሕዝብ ሊተላለፍ የሚችልበት ሁኔታ እንዲፈጠር ካደረጉ በኋላ፣ ማለትም የወዛደሩና የወታደሩ ሶቪየቶች አብዛኞቹ የቦልሼቪክ ፓርቲ ወገን ከሆኑ በኋላ፣ አስፈላጊው የፖለቲካና የተግባር ዝግጅት ከተደረገ በኋላ፣ እነሌኒን 'ጊዜያችን የከበርቴ መንግስት እናውድም፣ ሥልጣን ለሰፊው ሕዝብ' ብለው ተነሱና በርግጥም ደምስሰው የመጀመሪያውን የወዛደር መንግስት መሰረቱ።

በዛሬው የኢትዮጵያ ሁኔታም ዲሞክራሲያዊ አብዮት ባገራችን እንዲሳካን ለማስቻል እስካሁን መደረግ የሚገባውና የሚቻለውም ሪፎርሚዝምንና ኦፖርቹኒዝምን ለመደምሰስ መዘጋጀት ማለትም መደራጀትና ማደራጀት ነው። የደርጉን ፀረ ዲሞክራቲክ አገዛዝ ቶሎ ሥልጣን በሰፊው ሕዝብ እጅ የሚገባበትን እውነተኛ ሕዝባዊ መንግስት ለመመስረት ዛሬ ሊደረግ የሚቻለውና መደረግም ያለበት እየተደራጁ ማደራጀት ነው። ወደድንም ጠላንም ጹሳ እንደራጭ ዛሬ ለምርጫ አልቀረበልንም። በሌላ አነጋገር ከእኒሁ ዲሞክራቲክ ሬቮሉሽን በፊት ባገራችን ዲሞክራሲያዊ ሥርዐት ሊኖር አይችልም። <u>ከዚህ ሬቮሉሽን በፊት ሥልጣን በሰፊው ሕዝብ እጅ ሊገባ አይችልም</u>። በስም ብቻ 'ሕዝባዊ' የሆነ መንግስት ይኖር እንደ ሆነ እንጂ እውነተኛ 'ሕዝባዊነት' ያለው መንግስት አይኖርም።

በዛሬው የኢትዮጵያ ሁኔታ ወደ ዲሞክራሲና ወደእውነተኛ ሕዝባዊ መንግስት የሚያደርገው እውነተኛና ትክክለኛ የወደፊት እርምጃ ለእኒሁ ዲሞክራቲክ ሬቮሉሽን መዘጋጀት ብቻ ነው። ዛሬ ለዚሁ ሬቮሉሽን መዘጋጀት ማለት ደግሞ መደራጀትና እያደራጁ በሰፊው ሕዝብ መሃል ስለዚሁ ሬቮሉሽን አስፈላጊነት ከፍተኛ ቅስቀሳና ፕሮፓጋንዳ ማድረግ ማለት ነው። ሌላው ሁሉ ባዶ ወሬ ነው። ሌላው ሁሉ ይህን አስፈላጊ ዝግጅት የሚያደናቅፍ ፀረ አብዮታዊ ቅዠት ነው። ያልደራጀት ለመንግስት ሥልጣን ለመታገል መነሳት 'ምን ይዞ ጉዞ' ነው። ያልደራጀት ሰፊው ሕዝብ ምንም አያገኝም። የኢትዮጵያ ሕዝቦች የዘመናት ትግል ዛሬ በደረሰበት ደረጃ ያቀረበልን አብዮታዊ ጥሪ ለእኒሁ ዲሞክራቲክ ሬቮሉሽን ተዘጋጁ፣ እዘጋጁ፣ ተደራጁ አደራጁ የሚለው ነው። ከዚህ የተለየ ጥሪ እለ የሚሉን መለስም ፀረ ሬቮሉሽናሪ ጉ ዞ እያሉን እውነተኛ ተራማጆች ይሆን ታሪካዊ ጥሪ በተግባር ለመተርጎም እንታገል።

ገ.ዓ.

በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር
መጽሔት አዘጋጅ ቦርድ
The Ethiopian Students' Union
in Europe
Editorial Board



27/4/75

## ግንቦት 1 /ሜይ/ የዓለም ዓቀፍ ወዛደር የትግል ቀን

ከ1890 ጀምር እስካለንበት ጊዜ ድረስ ግንቦት አንድ እንደዓለም አቀፋዊ የወዛደሩ የትግል ቀን ከቀላ ጉደለ በመላው ዓለም እየተከበረ መጥቷል። የወዛደሩ መደብ በነዚሁ ዓመታት ውስጥ የሥራ ሰዓቶችን ለማስቀነስ፣ የኑሮ ሁኔታውን ለማሻሻል ከሚያደርገው ትግል አልፍ፣ የፖለቲካ ሥልጣን በመጨበጥ የሰውን ልጅ በማያዳግም ሁኔታ ከበዝባዥና ከጭቆና ነጻ ለማውጣት የሚታገልበት ደረጃ ከደረሰ ቆይቷል። በመጀመሪያው የዓለም ጦርነት ወቅት የብዙ አገር ወዛደሮች ባደረጉት ትግል ድል ለመቀዳጀት ባይችሉም፣ የሩሲያው ወዛደር የተካሄ ሶሺያሊስት ሬቮሉሽን በማድረግ ለዓለም ዓቀፍ ወዛደርና ጭቁን ሕዝቦች አዲስ መንገድ ከፈተ። ከዚያን ጊዜ ወዲህም በብዙ የአውሮፓ አገሮች፣ በቻይና፣ በኩሬያ፣ በቬትናም በወዛደሩ የተመሩ ሬቮሉሽኖች ድል ተቀዳጁ። ዛሬ የሶሺያሊስት ሬቮሉሽን፣ የኢምፔሪያሊዝም መውደቂያ ዘመን መሆኑ የማያጠራጥር እውነት ሆኗል።

አሁን ባለንበት ዘመን፣ የተጨቆኑ ሕዝቦች፣ የተበዘበዙ አገሮች ለዲሞክራሲ፣ ለናፃ ሀና ለነፃነት ከዓለም አቀፍ ኢምፔሪያሊዝም ጋር የሚያደርጉት ትግል ከፍተኛ ደረጃ ላይ በመድረሱ ኢምፔሪያሊዝምን በያለበት ሲያንበረክኩት እናያለን። ኢምፔሪያሊዝም በአገሩ ባሉት የወዛደሩ መደብ ትግሎችና በሌሎችም የውስጥ ችግሮች ተወጥሮ በውጭም በያለበት በሕዝቦች የመርና የፖለቲካ ትግል እየተመታ ነው።

ለብዙ ዘመናት የኮሎኒያሊዝምን የኢምፔሪያሊዝምን ጭቆናና ወረራ ሲታገል የኖረው ጀግናው የቬትናም ሕዝብ በደቡብ ቬትናም በጀግና ነፃ አውጭ ግንባር መሪነት ዛሬ ትግሉን ከፍጻሜ ለማድረስ በከፍተኛ ቆራጥነት እየታገለ ነው። የደቡብ ቬትናም የነፃነት ተዋጊዎች በጥቂት ሳምንታት ውስጥ አብዛኞቹን የደቡብ ቬትናም መቀመጫ ግዛቶች ከነጭ ከቀሪዎቹ ኢምፔሪያሊዝምና ሎሌዎቹን ድል በማድረግ ነፃ አውጥተዋል። ጀግናው የቬትናም ሕዝብ በታላቅ መስዋእትነት የሚያካሂደው ይህ ትግሉ፣ ኢምፔሪያሊስቶችና ሎሌዎቻቸው የተዋረዱበት፣ ለነፃነታቸው በመታገል ላይ ያሉ ሕዝቦች በአርአያነትና በታላቅ እምነት የሚመለከቱት ትግል የወረሪውን ድል ሊጎናጸፍ የሚቀረው ጊዜ በጣም ጥቂት ነው። ለእንደሌሎች ዘመናት በነፃነት ተዋጊዎች ደም የተነከረው፣ በሁዌ፣ በዳናንግና በመጨረሻም በቅርቡ ነፃ በወጡ የደቡብ ቬትናም ከተሞች የሚውለበለበው የነፃነት ባንዲራ በጥቂት ቀናት ውስጥ በሳይጎንም እንደሚውለበለብ ጥርጥር የለውም።

ኢምፔሪያሊዝም በደቡብ ምሥራቅ እስያ ጠረገና ያጧጧፈውን የማስፋፋት በሲአይኤ ሴራ ሕጋዊውን የካምቦዲያ መንግስት ከገለበጠበት ጊዜ ጀምሮ በሕዝብ ትግል እየፈራ ያለበት ጊዜ የለም::በበኩሉም የነፃ አውጭ የአንድነት ግንባር መሪነት የካምቦዲያ ሕዝብ ባደረገው ታላቅ ተጋድሎ ኢምፔሪያሊዝምንና ሎሌዎቹን ድል በማድረግ ያገሬቷን ነፃነት አስመለሰ::ይህ የካምቦዲያ ሕዝብ ብቻ ሳይሆን የዓለም ጭቁን ሕዝቦች ሁሉ የሚኮሩበት ታላቅ ድል፤ለነፃነቱ ታግሎ የተነሳን ሕዝብ ምንም ዓይነት ኃይል ሊያንበረክከው እንደማይችል በድጋሚ አረጋገጠ::

የኢምፔሪያሊዝም ድል መመታት በደቡብ ምሥራቅ እስያ የተወሰነ ብቻ ሳይሆን በያለበት በገሃዱ የሚታይ ነው::በአህጉራችን የዱሮ በፖርቱጋል የቅኝ አገዛዝ ሥር የነበሩት አገሮች ከብዙ ዓመታት መራራ የነፃነት ትግል በኋላ በታሪክ ውስጥ ከፍተኛ ቦታ የሚይዙ ታላላቅ ድሎች ተጎናጽፈዋል::የጊኒ ቢሳው፤የሞዛምቢክና የአንጎላ ሕዝቦች የትግል ታሪክና ድል ለአህጉራችን አኩሪና ከፍተኛ የነፃነት ምልክት ነው::

በአዚንያ በናሚቢያና በዚምባብዌ የሚካሄደው ፀረ አፓርታይድ የነፃነት ትግል ከጊዜ ወደጊዜ እያደገ በመሄዱ የፋሽስቶችን የፕሪቶሪያና የሳሊስበሪ መንግስታት በማንቀጥቀጥ ላይ ይገኛል::አንዳንድ አድሃሪ የአፍሪካ መንግስታት ከፕሪቶሪያ ጋር "የውስጥ ለውስጥ" ስምምነት ለማድረግ እየሞከሩ ቢሆንም የአፍሪካ ሕዝቦች ለደቡብ አፍሪካ ወገኖቻቸው የሚያደርጉት ድጋፍ አልተቋረጠም::የሕዝቦች ትግል በአድሃሪያኑ ሴራ የማይገታ በመሆኑ ድሉ የናሚቢያ የአዚንያና የዚምባብዌ አፍሪካውያን ነው::

በቅርብ ምስራቅና በመካከለኛው ምስራቅ ከፍተኛ ፋሽስታዊና የነፃነት ትግሎች በመካሄድ ላይ ናቸው::የፍልስጤም ሕዝብ የተገፈፈውን መብቱንና ብሔራዊ ነፃነቱን ለማስመለስ ከኢምፔሪያሊዝምና ከጽዮናውያን ጋር የሚያደርገውን ትግል አፋፍሞ ዛሬ በዓለም አቀፍ ደረጃ የማይናቅ የፖለቲካ ድሎች አግኝቷል::አንዳንድ አድሃሪ የአረብ አገሮችና በተለይም ፋሽስቱ የኢራን ሻህ የአማንና የዶፋር ሕዝብ ለብሔራዊ ነፃነቱ የሚያደርገውን ትግል ለመደምሰስ የጦር ወረራ አድርገዋል::ሆኖም በብሔራዊ ነፃ አውጭ ግንባሩ መሪነት የአማንና የዶፋር ሕዝብ በታላቅ ቆራጥነት ትግሉን ቀጥሏል::የአካባቢው አድሃሪያኖች ፀረ ሕዝብ ሴራ ሕዝቡ ለነፃነቱ የሚያደርገውን ትግል ሊገታው እንደማይችል እሙን ነው::

የአሜሪካ ኢምፔሪያሊዝም የስለላ ድርጅት በፋሽስቲክ ስርዐት የተቀረፀውን የአሌንዴን መንግስት ገለበጠ [illegible] [illegible] [illegible] ሕዝቡን ላይ ፋሽስታዊ አገዛዝ የጫነው የጁንታ ቡድን በቺሊ ወዛደሩ ሕዝብ [illegible] ለዲሞክራሲ የሚያደርገውን ትግል [illegible]::ፋሽስቱ ጁንታ [illegible] [illegible] እንዲገለል



የተገደደውን ያህል ጀግናው የቺሊ ሕዝብ ለዲሞክራሲና ለሶሺያሊዝም በሚያደርገው ትግል የጭቁን ሕዝቦች ድጋፍ አልተለየውም::

ለማጠቃለል፤አሁን ባለንበት ወቅት በመላው ዓለም ለዲሞክራሲ ለብሔራዊ ነፃነትና ለአርነት የሚደረገው ትግል ኢምፔሪያሊዝምን መውጫና መግቢያ አሳጥቶታል::አገሮች አርነትን፤ ብሔሮች ነፃነትን፤ሕዝቦች አብዮትን ይፈልጋሉ::ኢምፔሪያሊዝም ሆነ ማንኛውም ይህን የዛሬውን ዓለም የወደፊት ገስጋሴ ሊገታ አይችልም::

የዘመናት ጭቆና በዝበዛ አንገፍግፏቸው ፊውዳሊዝምንና ኢምፔሪያሊዝምን በልዩ ልዩ ሁኔታዎች ሲታገሉ የኖሩት የኢትዮጵያ ሕዝቦች ‹ባገራችን ታሪክ ወደር የሌለውን የየካቲት 1966 ሬቮሉሽናዊ እንቅስቃሴ ከጀመረ ወዲህ ያገራችን ሕዝቦች ትግል ከፍተኛ ደረጃ ደርሷል::ከ13 ዓመታት በላይ የብሔር ጭቆናን፤ኢምፔሪያሊዝምንና ፊውዳሊዝምን በጦር ኃይል ሲታገል የኖረው የኤርትራ ሕዝብ ለነፃነቱ የሚያደርገውን ትግል አፋፍሟል:: የኢትዮጵያ ሕዝቦች ባደረጉት ተጋድሎ በነፃነት ትግላቸውንና ላይ ጉልተው የሚታዩ ድሎች ተጎናጽፈዋል::ከሃምሳ ዓመታት በላይ የኢትዮጵያን ሕዝቦች በፋሽስታዊ አፈና ሲገዛ የኖረው ኃይለ ሥላሴ፤በርሱም አገዛዝ ስር ሕዝቡን ሲዘርፉና ሲያስለቅሱ የኖሩት የፊውዳሉ መደብ ቀንደኞችና የቢሮ ክራሲ አባሎች ከመንግስት ሥልጣን ተወግደዋል::ጥቂቶቹም የሞት ቅጣት ተፈጸመባቸዋል::የዘውድ አገዛዝ ተደምስሷል::በመጨረሻም፤የኢትዮጵያ ሕዝቦች የሥቃይና የጭቆና ምንጭ የሆነውን የፊውዳል ሥርዐት የሚደመስስ አዋጅ ወጥቷል::እነዚህ ሁሉ በዘመናት ትግልና በከፍተኛ መስዋዕትነት የተገኙ ድሎች በመሆናቸው በሰፊው ጭቁን ሕዝብ ሊኮራባቸው ይገባል::

ነገር ግን የኢትዮጵያ ሕዝቦች ትግል ጀመረ እንጂ ገና አላከተመም::የመጀመሪያዎቹ የመሸጋገሪያ ድሎች ተገኙ እንጂ የመጨረሻዎቹ ድሎች ገና ናቸው::አሮጌው ስርዐት ተነቃንቆ እንጂ አልተደመሰሰም፤ፊውዳሊዝምና ኢምፔሪያሊዝም ተደምስሰው አዲስ ሕዝባዊ ስርዐት አልተገነባም::በቀድሞዎቹ የገዥ መደቦች ቦታ ዲሞክራቲክ መብቶችን ገና በፀረ ዲሞክራቲክ አዋጆች የሚገዛ የወታደር አገዛዝ ተተካ እንጂ የሰፊውን ሕዝብ ዲሞክራቲክ መብቶች የሚያስከብር በወዛደሩ መደብ የሚመራ እውነተኛ ሕዝባዊ መንግስት ገና አልተመሰረተም::ይህን ሁሉ ለማድረግ የኢትዮጵያ ሕዝቦች የጀመሩትን ትግል በከፍተኛ ደረጃ ወደፊት መግፋት አለባቸው::

ግንቦት 1 ባለቤት የሆነው የወዛደሩ መደብ በኢትዮጵያ ካሉት መደቦች ሁሉ ፊውዳሊዝምንና ኢምፔሪያሊዝምን ደምስሶ አዲሲቷን ሕዝባዊት ኢትዮጵያ ለመመስረት የሚደረገውን ትግል መርቶ ከፍጻሜ ለማድረስ የታሪክ ኃላፊነት የተጣለበት መደብ ነው::

የኢትዮጵያ ወዛደር በየከተ አንቅስቃሴ ባሳየው ከፍተኛ ተሳታፊነት ባገራችን ሕዝቦች ትግል የሚይዘው ቦታ ከፍ እያለ ሄዷል:: ነገር ግን ይህ መደብ ታሪካዊ ሃላፊነቱን ለመፈጸም ገና አልተዘጋጀም::ለዚህ ታሪካዊ ሚናው ብቁ የሚያደርገው የራሱን ፓርቲ ገና አላገኘም::ሌላው ቀርቶ ከመንግስት ቀጥተኛ ነፃ የሆኑ፣በዲሞክራሲያዊ ሰርዐት የሚሰራ ሙያ ማህበር የለውም:: የተለያዩ የንዑስ ከበርቴ ክፍሎች ሳይንሳዊ ርእዮተ ዓለሙን ለማስፋፋት ይህ መደብ ከሌሎች የኢትዮጵያ መደቦች የተለየ ዘላቂ ዓላማ እንዳለው ለማስካድ በሚሞክሩበት ባሁኑ ወቅት፣የኢትዮጵያን ወዛደር ለታሪካዊ ሚናው የሚያበቃው፣ሳይንሳዊ ርእዮተዓለሙን ከንዑስ ከበርቴ ርዝራዥ የሚያፀዳውን መቀላለውን የኢትዮጵያ ጭቁን ሕዝብ ወደዘላቂ ድል ለመራ የሚችለው የወዛደሩ ፓርቲ ገና አልተፈጠረም:: ባጭሩ ግንቦት 1 በኢትዮጵያ ለመጀመሪያ ጊዜ የሚከበረው በዚህ ሁኔታና የትግል ደረጃ ነው::

ለማጠቃለል፣የኢትዮጵያ ሕዝቦች ባለፉት ዓመታት ትግላቸው ያገኟቸው ድሎች ፍሬ የማይናቅ ናቸው::በሌላ በኩል ደግሞ የኢትዮጵያ ሕዝቦች ትግል ደካማ ጎን አለመደራጀት ነው::ባሁኑ ወቅት ባገራችን የተፋፋመ የመደብ ትግል፣ለጭቁን መደቦች የተመቸ አብዮታዊ ሁኔታ አለ:: የኢትዮጵያ ሕዝቦች ትግል ወደአዲሱ ዲሞክራቲክ ሪፐብሊክን የሚጓዝበት የሽግግር ወቅት ነው ለማለት ይቻላል::በዚህ ታሪካዊ የሽግግር ወቅት፣የሕዝቦችን ትግል በርግጥ ወደአዲሱ ዲሞክራቲክ ሪፐብሊክን እንዲያመራ፣ድልን በድል ላይ እየተጎናፀፈ ዘላቂ ነፃነትን ለመቀዳጀት እንዲችል የወዛደሩ መደብ፣መደራጀት አለበት፣:ገበሬው ለሬቮሉሽናዊ ዓላማ መደራጀት አለበት::ሌሎች ባሁኑ ሰርዐት መደምሰስ ጥቅም ያላቸው የዚህ ሬፐብሊክን አጋዥ መደቦችና የሕብረተሰብ ክፍሎች መደራጀት አለባቸው::ባጭሩ በዛሬይቱ ኢትዮጵያ የመደራጀት ጥያቄ ከፍተኛው የዲሞክራሲና የሪቮሉሽኑ ጥያቄ ሆኗል::

የጦር ኃይሎች ደርግ 'ሶሺያሊዝም'ሆነ 'መሬት ላራሹ'ቢያውጁም አሁንም የኢትዮጵያ ሕዝቦች እንደሁሌዉት አስተገፋበ የሚያስፈልጋቸውን ዲሞክራሲያዊ መብቶች በፀረ ዲሞክራቲክ ሕጎቹና በኃይል እንደከለከለ ነው::ግንቦት 1 እንዲከበር መፍቀዱ ይሁን ፀረ ዲሞክራቲክ አገዛዙን ሊሸፍነው አይችልም::ስለዚህም ግንቦት አንድ በአገራችን በሚከበርበት ቀን ከኢትዮጵያ ዲሞክራቲክ ኃይሎች ጋር የትግል አንድነታችንን በማጥበቅ በሚከተሉት ጥያቄዎች ሥር አብረን እንቆማለን::

የመናገር፣የመሰብሰብ፣የሰላማዊ ሰልፍ፣የጽሁፈት፣የሥራ ማቆም፣የመደራጀት መብቶች ይከበሩ!
የወዛደሩ መብቶች ይከበሩ!
የኤርትራ ሕዝብ የራሱን እድል በራሱ ለመወሰን ያለው መብት ይጠበቅ!
የብሔሮች፣የሃይማኖቶች፣የፆታዎች እኩልነት ይኑር!
መሬት ላራሹ ያለ ምንም ገደብ ሥራ ላይ ይዋል!

የኢትዮጵያ ወዛደርና ሰፊ ሕዝብ በተገዥነት ሳይሆን በገዥነት
ግንቦት አንድን ለሚያከብሩበት ኢትዮጵያ እንታገል!!
የሁሉ አገር ወዛደሮችና የተጨቆኑ ሕዝቦች አንድ ሁኑ!!
ዓለም ዓቀፍ ፀረ ኢምፔሪያሊስት ትግል ይኑር!!
ድሉ የጭቁን ሕዝቦች ነው!!



ሚያዝያ 30 1975

ለአውሮፓ ማህበር ቀ/ማህበራት

ውድ ጓዶች

ዛሬ ሚያዝያ 30 ቀን 1975 የደቡብ ቬየትናም የነፃነት አርበኞች የሳይጎንን ከተማ በእጃቸው በማስገባት በአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም ላይ የመጨረሻውን ድል ተቀዳጅተዋል :: ከሰላሳ ዓመታት ረጅምና መራር ትግል በኋላ በጊዜያዊ ሬቮሉሽናዊ መንግሥት /ፕሮቪዥናል ሪቮሉሽነሪ ገቨርንመንት/ የሚወከሉት የደቡብ ቬይትናም የነፃነት ተዋጊዎች ያገኙት ድል በመላው ዓለም ኢምፔሪያሊዝምን ለሚታገሉ አብዮታዊ የነፃነትና የሰላም ሃይሎች ታላቅ የምስራች ነው ::ይህ ድል እስካሁን በታሪክ ፍጹም አቻ የማይገኝለት የዓለም ጭቁን ሕዝቦች ሁሉ ድል በመሆኑ በታላቅ ኩራትና ፈንጠዚያ የምናከብረው ነው :: ምሳሌነቱ ምንጊዜም ህያው ሆኖ የሚኖረው የጀግኖች ቬፅትናማውያን አቻ የለሹ ድል በአብዮታዊ ታሪክ ውስጥ በጉልህ ምእራፎች ፣ በቀይ ቀለም ባሸበረቁ ገጾች የሚጻፍ ነው ::

በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር ሥራ አስኪያጅ ኮሚቴ ይህንን ታሪካዊ ድል ምክንያት በማድረግ ለደቡብ ቬይትናም ጊዜያዊ ሪቮሉሽናዊ መንግሥት አንድ የደስታ መግለጫ ቴሌግራም አስተላልፏል ::

ወደኋላ ተመልሰን ስናስታውስ የዛሬ 21 ዓመት በዚሁ በግንቦት ወር 1954 ዓ.ም. የፈረንሳይን ቅኝ አገዛዝ በዲየን ቢየን ፉ ላይ ታላቅ ሽንፈት በማከናነብ ድል ያደረጉት የቬፅትናም ሕዝቦች ይኸው ዛሬ ደግሞ የአሜሪካንን ኢምፔሪያሊዝም በመራር አብዮታዊ የጦር ትግል ደምስሰው ከፈረንሳይ የላቀ ሽንፈትን ፣ ቅሌትን ኪሳራና ውርደትን አከናንበው ከሃገራቸው ምድር እንዲወጣ አድርገውታል :: የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም በደቡብ ቬይትናም ማቅ ለበሰ :: በእነ ጊየም ኪሲንጀር በእነ ቲዩ አማካኝነት የሰፈረው ፋሺስታዊ አገዛዝ በሃይል ተደመሰሰ፣ተገረሰሰ :: የቬይትናም ሰፊ ሕዝብ ፣ ከሰሜን እስከ ደቡብ የነፃነቱንና የአንድነቱን ካባ ለበሰ :: ይህ ሁሉ የተገኘው እስከ ዛሬ በጥልቀቱ በስፋቱ ተወዳዳሪ በማይገኝለት አኩሪ መራር ረጅምና አድካሚ የነፃነት ትግል ነው ::

በ1896 ገደማ በቅኝ አገዛዝ ሃገራቸውን ሙሉ በሙሉ ፈረንሳይ በቁጥጥር ሥር ካስገባችበት ጊዜ ጀምሮ ቬይትናማውያን ለነፃነት መታገላቸው መስዋታቸው አለቀረም ነበር :: ይህችን በፈጥሮ ለምለሟ በማዕድን ሃብቷ በጂኦግራፊ አቀማመጧ የኢምፔሪያሊስትን ዓይን አጥብቃ የምታስቀረጥመውን ቬፅትናም ከእነኝህ ዘራፊዎች ፣ ደም አፍሳሾች አጅ ፈልቅቆ ነፃ ማውጣት የከበደና የመረረ ተጋድሎ የሚጠይቅ ነበር:: ለዚሁ ክቡር ለሆነው የነፃነት ትግል በዱር በገደሉ - ለመሰደድ፣ ደማቸውን ለተቀደሰው ለህዝቦች እኩልነትና ደህንነት ለማፍሰስ ቬፅትናማውያን ብቁ ሆነው ተገኝተው ነበር :: ይህንንም ታሪካዊ ግዳጅ ለመሸከም የቆረጡት ግንባር ቀደሞች በ1930 የኢንዶ ቻይናን ኮሚኒስት ፓርቲ በታላቁ ሆ ቺ ሚን መሪነት መሰርተው በቬየትናማውያን ላይ የተጫነውን የፈረንሳይ የቅኝ አገዛዝ ቀንበር ፣ ባርነት ፣ ረሃብና በሽታ የሰፈነበትን ሥርዓት ለመመንጠር ትግሉ ይፋፋም ጀመር :: የዓለም ወዛደር ትግል፣ በተለይም በ1917 በዛርስት ሩስያ የመጀመሪያው የሶሺያሊስት ሬቮሉሺን መደረግ ፣ በቻይና በኮሪያ በአካባቢውና በመላው ዓለም የተፋፋመው የጭቁን ህዝቦች ትግል ለቬፅትናም ሕዝቦች ተጨማሪ አለኝታና ብርታትን መስጠቱ አልቀረም ነበር ::

ይህ ሁሉ ሆኖ የፈረንሳይ ቀኝ አገዛዝን መውጫ መግቢያ አሳጥቶ በ1954 ድምጥ ማጡን በማጥፋት ለማብረር ችሎአል ::

ፈረንሳይ ድል መሆንዋን አምና በ1954 የጄኔቫን ውል በተፈረም በጦርነት ከ80 በመቶ በፈረንሳይ በበተጀርባ ተከታፊነት የነበራት አሜሪካ የጄኔቫን ስምምነት ረግጣ በ1965 በቬትናም ላይ ሙሉ ወረራዋን አደረገች :: የአሜሪካን ኢምፔርያሊዝም በሲ.አይ.ኤ. አማካኝነት "ስፔሻል ዋር"/ልዩ ጦርነት/ "ሊሚትድ ዋር"/ውስን ጦርነት/ ወዘተ የተባሉ ስልቶ የጦርነት ዘዴዎችን በቬትናም ህዝቦች ላይ ፈጸመዋል :: እነዚህ ሁሉ የጦር ንዳኖች አሜሪካኖች በቬትናም መቀጠራቸው በበኩላቸው ዓለም አሜሪካኖች 62 ሬፐብሊካዊ ድርጅት ምንያህል ውጤትን እንደሚያሳዩ ለማየት ነበር :: አሜሪካ የከሚኒዝምን መስፋፋት ለመግታት በቬትናማውያን ላይ አጅግ የሚያሰቅቁ የመዘግንን ጭካኔያዊ ፈጸማለች :: አሜሪካ በቬትናም ህዝቦች ላይ በቻ ያወረደችው ቦምብ በሁለተኛው የዓለም ጦርነት በዓለም ህዝቦች ላይ ከተጣለው እንደሚበልጥ በዛሬ ሁለትና ስስት ዓመታት በፊት ተነግሯል :: አሜሪካን በቬትናምውያን ላይ ያስጠበረችው ዓይነት የረቀቀ የጦር መሣሪያ አይገኝም ::ከቦምብ ውርጅብኝ ሌላ በናፓም ተጠበሰዋል ፤ ደበውን ዘር ይቀርና እንበሳትንና አዝራእትን በሚያወድሙ የርዝ ጪስ ታፍነዋል ፤ ቁጥር ስፍር የሌለው ጥይት ዘንበባቸዋል :: በቬትናማውያ ላይ የደረሰው በደና መከራ እስከዛሬ በሰው ልጆች ላይ ያልደረሰ ነው ::አሜሪካ ይህንን ሁሉ አድርጋ ውጤቱና ፍሬት አልቀረላትም ::ያንን ያህል በበዙ ቢሊዮን የሚቆጠር ብር ከሰከሰች ከ45000 በላይ ወታደሮች አጣች "ቬትናምን በቬትናማውያን" /በቬትናማይዜሽን/ የተባለው ወናኝ የጦር ስልት ከሽፎ እነ ተቆ ተነቀለው ፤ በአሜሪካ ፀረ ከሚኒስት ስሌቶች የታጠረችው ቆይቅን ካለምንም ውለም ዘለም አጀን በጉሁያዊ ሬፐብሊክና ዊ መንግሥት ለሚመራው ለደበብ ቬትናም ነጻ አውጪዎች ሰጥታለች ::

የቬትናማውያን ባለፉት 30 ዓመታት ያደረጉት አብዮታዊ ተጋድሎ ለነጻነት ተጋፋዎች ፤ ለቀኝ አገዛዝ፣ ለኢምፔሪያሊዝም ለሚጋሉ ሃይሎች የሚሰጠው ዐርቀት እጅግ በዙ ፤ አጅግም ግልቅ ከመሆኑ የተነሳ በቃሉ ለገዝቶው ይገባል :: የቬትናማውያን አርአያ ለመከተል የቆረጡ አብዮታውያን ቬትናማውያንን ከማድነቅ ፤ ተገሪም ይገቀ ከማለት አልፎው በመሬ ተግሳቸው ትምህርቱ ለመቀበም መጣደፍ አለባቸው ::በአገራቸው ተጨባጭ ሁኔታ አገደምን ሥራ ላይ እንደሚያውሉት መመከከር አለባቸው::

የነፃነት ትግል የፈለገውን ያህል ቢረዝም ፤ ቁጥር ስፍር የሌላቸው የነፃነት አርበኞች በትግሉ ጫና በወደቁ ፤ በህዝቦች ላይ ይህ ነው የማይባል ገፍ ቢወርድ ፤ ፍጻሜ የሚታበት እንዳለሁ ቬትናማውያን ያስተምሩናል :: ቬትናማውያን እጅግ የሚያስፈራውን በያዘነው ከፍለ ዘመን በሳይንስና በቴክኖሎጂ ጥበብ ተመከ ተ በሠርቶ አደር ህዝብ ላይ የበዘበዛንና የጭቆናን ሥርዓት ለማስፈር በዓለም ዙሪያ ጠረን የሚያዘምተውን፣ በረን የሚመዘውን፣ በፀረ ሪፐብሊካን ተግባር የሰለጠኑ ሰላቆችን በየአገሩ የሚያገክራተውን የአሜሪካንን ኢምፔርያሊዝም በአብዮታዊ ነቃት ፤ ድርጅትና ትግል በሃይል ለመደምሰስ እንደሚቻል ያረጋገጡልናል ::አሜሪካን ኢምፔርያሊዝም ለቬትናምና ለካምቦዲያ ህዝቦች አውነትም በወረቀት ላይ እንደተሳለ ነበር እንደመሰለ አረጋግጠዋል :: የካምቦዲያ ህዝቦች ባለፈው ሚያዝያ 18 ያገኙት የሚያስገርም ድል ለአሜሪካን ኢምፔርያሊዝም ሌላው ከበረት ሰሆን ለእና ደግሞ ሌላው የምኅበራት ድል ነው ::



ወደ እኛ ሃገር መለስ ያለን እንደሆነ አሜሪካን ኢምፔርያሊዝም ዋናው የህዝቦቻችን ጠላት ነው :: ይዋል ይደር እንጂ የኢትዮጵያ ጭቁን ህዝቦች እንዱ ቀን በጦር ሜዳ የሚገጥሙት ነው ::አሜሪካን ኢምፔርያሊዝም በአገራችን ሾር ንዱ ሲል ፓለቲካዊና ሲበዘብዝ የኖረ ነው ::ልክ እንደቬትናምና እንደ ቀረት አሜሪካን ኢምፔርያሊዝም የጭቆና የበዝበዛ ቀንበር እንደ ጫነባቸው አገሮች በኢትዮጵያ ህዝቦች ላይ ደግሞ ቀንበር ተጭኗል :: አሜሪካ አገራችንን በፀረ ሬፐብሊክ ተገኩሎች ከዳር እስከ ዳር እንደ ሸረሪት ድር የተበተበች ነች :: በጦር ሃይል ፤ በአስተዳደሩ በመስሰሉት ሁሉ መስኮች አሽ ድ ይገኛል :: ሰለጠናቸን በቢሮክራሲው መጠቀጠቋ ላይ ታለም የተፈታ ነው :: ...ን በአገራችን ያካተው አብዮታዊ እንቅስቃሴ ከእኛው እንዳይወጣ አስፈላጊውን ሁሉ ከመቀም ወደኋላ አይመለሰም :: ኢትዮጵያን የመሰለች አገር ፤ በተፈጥሮ ሃብቷና በሚያገራፊ አቀማመጥ ሆነ በአስተዳደሩ በወታደራዊ ስትራቴጂ የኢትዮጵያን ያህል አስፈላጊ የሆነችውን አገር አሜሪካኖች በቀላሉ ለማጣት የተዘጋጁ አይደሉም :: የሰሞኑ 15 ሚሊዮን የአሜሪካን ብር ለወታደራዊው መንግሥት ለመስጠት ያደረጉት ስምምነት አብዮታዊ እንቅስቃሴውን ለማፋፈን ከሚወሰዱት እርምጃ አንደኛው ክፍል ነው ::

ወታደራዊው መንግሥት እስከዛሬ የሰፊውን ሕዝብ ዲሞክራሲያዊ ሰብዓዊ መብቶች በተግባር እንዲረጋገጡ አለመፍቀዱ ፤ እንዳንዱ ተራማጆችን ከሕዝቡ ጠላቶች ጋር አብሮ መረሸን አለመደው መሆኑ ፤ እንዲያውም እንዱ ሰዉን ደርግ አራሱ ሲያወግዘው የነበረውን ኢምፔርያሊዝም አሁን ግን በውም እንዳይጠራ ፤ ምንም አይነት የማጋለጥ እርምጃ እንደይወሰድበት መከልከሉ ውሉ አደር ከአሜሪካኖች ጋር እንደሚታረቅ ያሳያል ::ይህ ሁኔታም ከቀጠለ በኢትዮጵያ ሬቮሉሽን ላይ አደጋ ማምጣቱ የማይቀር ነው :: በወታደራዊው ደርግ ውስጥ የሃይል ሚዛን ከቀን ወደ ቀን ወደ አዉሃሪው ወገን የሚያዘነብል ከሆነ እስከ ዛሬ የተወሰዱትን ተራማጅ እርምጃዎች ለመቀልበስ መቀጠሉ በሰሜን ይህን አዝማሚያ የተረዱ አብዮታውያን ይቀርና በራሱ በደርጉ ውስጥ ያሉ ሚገኙት ተራማጆች ከሰፊው ህዝብ ጋር በለፋቸውን ማሰመር ይኖርባቸዋል :: አሜሪካን ኢምፔርያሊዝም አብዮታዊ ትግሉን ለማኮላሸት ፍጹም የማይተኛ መሆኑን የህዝብ ነው ሰፊውን ገበሬ ሠራተኛና ተራማጅን የህዝብ ክፍል በጊዜው መሰበሰብ ማደራጀትና ለማይቀረው የመበገኛ ትግል እንዲዘጋጅ ማድረግ ዋና ተግባር ነው ::

የቬትናማውያንን ምሳሌ ለመከተል የቆረጡ አብዮታውያን ፤ ፀረ ፊውዳልና ፀረ ኢምፔርያሊስት ሃይሎች በአሜሪካን ኢምፔርያሊዝምና በቀፊትም ፀረ አብዮት ሃይሎች እንዳይጠቃው ያስፈልጋል :: የነፃነት ትግል ሊቀጥል የሚችለው የጊዜውን እንገዛዝጋቢ መደራጀትና የማደራጀቱን ሥራ ለመሥራት በነጻደፍ በቻ ነው ::

የቬትናማውያንን ምሳሌ እንከተል!
የቬትናማውያን አብዮት ለዘላለም ይኑር!
የካምቦዲያውያን አብዮት ለዘላለም ይኑር!
አሜሪካ ኢምፔርያሊዝም ይደምሰስ!
የጭቁን ሕዝቦች ትግል ያሸንፋል!

እኢትዮ ሥራ አስኪያጅ ኮሚቴ /ፊርማና ማህተም/

<u>ለጠር ኃይሎች ደርግ የተላከው ቴሌግራም</u>::

የኢትዮጵያን ሕዝቦች ከ50 ዓመታት በላይ በፋሽስታዊ አመጽ ሲገዛ የኖረውና ዓይነሕሊናችን ከተከረተበት ጊዜ ደምር ሲገንታገለው የነበረው የቀደሞ ንጉሠ ኃይለ ሥላሴ ከሥልጣን ሲወገድ ያለተደበቀና ያለደገፈ ተራማጅ አደናርም::በለዚህም ንጉሡ እንደወደቀ ደሀንኑ በመደገፍ በለላለክነው ቴሌግራም ውዝገብ ቢለተፈጠረና እኛም ተመለስን ደሀን ማብራሪት ባለኖረብንም ነበር::ዳሩ ግን ምን ደህናል፤እንጊዜ እንጊዜ ዓይነት ነገሮች ካለገኙ በርዕም ላይ ባለተረባረቡ የፖለቲካ ተገላችው የሚያለቀባችው አደርባዮች ከመሃላችን በላሉ፤ባለፈት 10 ወራት በለዚህ ቴሌግራም ያለወሬትና ያለፈጠሩት ክስ በለሌለ በሬዉ ተባራ የቴሌግራሙን ሙሉ ደዘት ለማየት ይቻል ዘንድ አውጥተነዋል::

ደሀን የቴሌግራም ጉዳይ ለማበፋትና ከቦቹ በርከት ለማደረግ ያለ ተጨባጭ ሀተታዎችና ክቦች የሉም::የሌዘናው ከምባት ደበታ አገላለፃችን እንደገወሰ ከበርቴ በመሆኑ ደከሰናለ::አውርፖ ያሉት የፊዳሬሽን መሪዎች 'ኃይለ ሥላሴን የጣለው ሕዝቡ ሆኖ ባለ ደርጉን ም ቃጉበጠትና ለሕዝቡ ባይሆን ለደርጉ የተለከበት ምክንያት ምን ድን ነው? በሚል ጥያቄ 'ያፋጥጡናል':: ያለደራያዎች ደገሞ 'የናንተ ቴሌግራም በበደብተኛ ወሬ በተከለም ያሉ ኢትዮጵያውያን ደርጉ በአርተራ ላይ የፈጸመውን ወንጀል በመደገፍ የላከትን ቴሌግራም ወለደ' ይለናለ::በቀርቡ ደገሞ የደርመኑ ክንዒ ማኅናወንም'ጊዜያዊ መንገስት የሚያወመውን የ145 ክንዒ ውሳኔ በመጠበ ለ 'ጊዜያዊ' ወታደራዊ መንገስት የድጋፍ መግለጫ ለከቻኋለ በማለት ደከሰናለ::

ከደርዎም ቢሆን የፖለቲካ አይሚያቸውን ለማራዘም፤'የፖለቲካ ተገላቸውን' አደማስ ለማበፋት በአውሮፓ ማህበር ደርጊቶችና እቃች ላይ ቀጥ ያጠ ከበና ሀሜት ማውረድ <u>አንዳለባቸው</u> በለምናቸው፤ደሀን ቴሌግራም 'ከበዙ አቀጣጫ' ተነስተው 'በመተንተን' ከባቸውን ቢያበራከቱ አደገርመንም::በዚህ ዓመት ከፌዴሬሽን ሰዎች አካባቢ የወጡትን ጽሁፎች በጎ መለከት የኢትዮጵያ ወዝደር ዛሬ እንዲት መደራደት አለበት በሚል ጥያቄ ላይ አሥር መስመር ተጽፎ እናገኝም::በለዚህ ቴሌግራም ገን ቢደመር ከመቶ በላይ ገጾች ተጽፈዋል:: የኢትዮጵያን ሬቮሉሽን ከበዙ አቀጣጫ ተነስቶ መርመር ያያተው ወገን፤ደሀን ቴሌግራም 'ከበዙ አቀጣጫ'በመነሳት በዙ ገጾች ካለፃፈበት የፖለቲካ መደረኩ'እንደሚጠብበት' ለመገመት አያስቸግርም::

ከላይ ለጠቀስናቸው 'የፖለቲካ' ክርክሮች መለስ መስጠቱ ጊዜ ማጥፋት ነው:: ቴሌግራሙ የተላከበትን ሁኔታ ባጭሩ ማስረፈ ደበቃል::ኃይለ ሥላሴ ከሥልጣን እንደወረደ የእለቱ ለት ደሀ ቴሌግራም ለደርጉ ተላከ::በዚሁ ቀን ለተባራ ማህበራትና ለኢትዮጵያ



ተራማጅ ደርጅቶች በትገሎቻችን ቀጥር 1፤1967 እንደገና ታትሞ የወጣው በሩ ያለ መግለጫ ተከራዉ:: የኢትዮጵያ ሕዝቦች ተገለ ኃይለ ሥላሴ የማወደቀበትን <u>ሁኔታ</u> ፈጠረ፤የጦር ኃይሎች ደርግ በዚሁ ሁኔታ ተገፋፍቶ ፈላጭ ቆራጩን ከመጣለ <u>እርምጃ</u> ወሰደ::ይህ ተራማጅ እርምጃ ለምን ተደገፈ የሚለ ተራማጅ የሚኖር አይመስለንም::ንጉሡ መቶ ጊዜ ደሽለን ነበር ከሚሉን ተራማጅ.መሰሎች በስተቀር::

ደሀን እርምጃ መደገፍ የደርጉን አገዛዝ መደገፍ እንዳልሆነም እንደዚሁ ገለጸ ነው::ከቴሌግራሙ ደዘት ማየት ደቻላል::ዛሬ ደርጉን ደገፋችሁ ቴሌግራም ላካችሁ እያሉ በሬዉን ተባራ ለማወናበድ የሚቀበሩት የፊዳሬሽን መሪዎች የኃይለ ሥላሴን መውረደ ደገፋችሁ፤ደርጉ ወርደ ጊዜያዊ መንገስት እንዲያም ጠይቃችሁ ለደርጉ ቴሌግራም ላኩ የሚል ቴሌግራም ለከውለን ነበር::ለበ እንበል፤ቴሌግራም እንደደገለከ 'የታዘዘ ነው'ለደርጉ እንጂ 'ለኢትዮጵያ ሕዝብ' አለነበረም::/በነገራችን ላይ ደሀን 'ሥልጣን ልቀቁልን' የሚለ ቴሌግራም እነሱ ለደርጉ ደላኩ አደላኩ አናውቅም::/ማህበራችን 'ጊዜያዊ መንገስት' የሚል መፈ ቃለ እንደማደቀበለና የሚታገለው ለዲሞክራቲክ መብቶች መረጋጫ እንደሆነ በጉባዔ ወስኗለ::ሥራ አስኪያጅ ኮሚቴዎም ደሀንኑ ውሳኔ በመመርኰዝ የንጉሡን መወገድ እንደሚደገፍ፤የንጉሠ አገዛዝ እንዲጠፋና ዲሞክራቲክ መብቶች እንዲረጋገጡ የሚጠይቅ ቴሌግራም ላከ:: የፌዴሬሽን መሪዎች ተያይዘው ሲነሱ የሚቻለው የኃይለ ሥላሴን መውደቅ ደገፍ ለደር ቴሌግራም በመላክ ሳይሆን፤ጊዜያዊ መንገስታቸውን እናም ጠይቀን የነሱን ቴሌግራም ሥራ ላይ ባለማዋላችን ብቻ ነው::በከፍተኛ የፖለቲካና የርእዮተ ዓለም ተገለ ክንዒያችን የጣለውን ጊዜያዊ መንገስታቸው በቴሌግራም ተአዛዝ ሥራ ላይ እንድናውለለችው መጠየቃቸው ራሱ ቀሽነት ነው::ለማንኛውም ሁለቱም ቴሌግራሞች ለበሬ ው ተባራ አቀርበናለ::

———xx———

በናኀገበር ላይ በቀጥ በለተቀጠሩ የቀደሞ ባለሥልጣኖች ማህበራችን የወከደው ተከከለና እቃም እንዲሁ የ'ፖለቲካ ተገላቸውን መደረክ' አስፍተሏቸዋል::በትገሎቻችን ዜና ቀጥር 2 1967 እንደገና ታትሞ በወጣው የአውሮፓ ማህበር ሥ/አ/ኮ መግለጫ መደመሪያ.የተበራዉ ዋቀ ቀጣት በተፈጸመ ማገበት ነበር::መግለጫው በተፃፈበት ወቅት የዓለም ጋዜጦች 'በደብ ያሉ የቀደሞ ባለሥልጣኖች ተገደሉ' የሚል ዜና አሰራጭተው ነበር:: የተመቀሱት ጥቂት በቀቾም ሙሉ የነአስከንደር ደበታ ወዘተ. ዓይነት የቀደሞ ገዥ መደብ አባሎች ሥቃዮች ነበሩ::ከዚህም የተነሳ በመደመሪያዎቹ ቀናት ከተገደሉት ውስጥ ተራ ወታደር፤ ተራማጅ ደናርበታለ የሚል ጥርጣሬ አገቢ ሊያደር አደቻለም ነበር::ደሀንም አገር ሆኖ የበማው ኢትዮጵያዊ ሁሉ ገምተ ባይሆን አይቀርም::በዚሁ ሁኔታ ከላይ የጠቀሰነው መግለጫ ተጽፎ ተከራዉ::ከጥቂት ጊዜ በኋላ ከኢትዮጵያ መንገስት ጋዜጦች የተገደሉት ሰዎች ስም ዝርዝር እንደደረሰን በጣት ያሉ የቀደሞዉ ባለሥልጣኖች ያለሆኑ መሆናቸውን ተረዳን:: በሚቀጥለው መጽሄትም/ከላይ በጠቀስነው ውስጥ/ደሀንኑ በመግለጽ የነዚህ በጣት ሰዎች

ወገደለ ለምን እንደሆነ ለማጧ[illegible] እ'ቃ[illegible] እንደሆነ ገለጸን::

በዚሁ ባቢያ ከፊዳሬሽን ሰዎች አካባቢ አስተያየቶች ከሰቾ ይሰነዘሩ ጀመር:: ከዚሁ አጋርባይ ከንፍ በለዚህ አይም የተጠመው ገዎት ይቃረናል::አንደኛው አስተያየት ዘወይቻቸው ከተገደሉባቸው በኋላ ደርጉን ወቃወም ጀመረ ይላል::ሌላኛው ደገፎ፤ደርጉ ተራማጆች ሲገደሉ ካይደፋር ደገፋቾሁ፤ወዘተ. ይላል::ወይ የመጀመሪያው ወይ የመጨረሻው::ግን የአውሮፓን ማህበር ሥም ያገደፈ አስከመሰለቸው ድረስ የራሳቸው አስተያየት አንገሏ አርሰ በርሱ ቢቃረን ገው አንደሌላቸው የሚያሳየው የሆሳገቱ "ሳበአደር". በሁለተኛው እትመ ላይ እነዚህን ተቃራኒ ገምቶች አትሟል::የመጀመሪያውን ክርክር ለሕፃናትና 'ለአዋንት ቀጣሪዎች" አንተውና ሁለተኛውን ከስ እንመለከት::

ወገለጨው የተሏረው የተገደሉትን ሰዎች ስም ዝርዝር ባናውቅ በሆነም፤እንደዎ በታ የተራማጆችን ወገደለ የሚደገፍ የሚመስል ሀረግ አንገኒ አደገኘበትም::ወገለጨው "እንደ ኢ.አ.በ23/11/74 በእስር ላይ ከሚገኙት የቀድሞ ባለሥልጣናት ወ ሃለ 60 ያህሉ ወገደላቸውን ያለዎ ጋዜጠኛ ገለጠዋል::" ካለ በኋላ፤"ለበዙ ዘመናት የኢትዮ ጵያን ሕዝብ በገፍና በጭቆና ሲገዙ የኖሩ፤የበዙ አገር ወዳጅ ደገኖች ደም በደቻቸው የፈሰሰ የሕዝብ ጠላቶች ወገደል አስደሳች ነው::ከዚህም አልፎ የባለባቶን ወደብ ወኪሎች በቀዮር ወቀነሱ በቻ ባይሆን፤የነዚሁ ገፈኖች ወቃ ይሀን ወደብ አስከተወሰነ ደረጃ የሚያዳክም፤....እያለ ይቀጥላል::እንግዲህ በዚህ ወገለጫ የተራማጆችን ወገደለ ደገፋቸሁ የሚሉን ከየት ተነስተው እንደሆነ ማወቅ አልቻልንም::ተራማጆች የኢትዮጵያን ሕዝብ "በገፍና በጭቆና" አልገዙም::የተራማጆች ወቃት "የፊውዳሉን ወደብ አያዳክምም":: በዚህ ወገለጫ የተደገፈው የገዲ ዓይነቱ ሰዎች ወገደል ነው::

ሁለተኛ ነገር፤ወገለጨው ደርጉን ለመደገፍ ሳይሆን ደርጉን ለማጋለጥ የወጣ ነበር: ደርጉ እነዚህን ፊውዳሎቸቸበመገደሉ ፊውዳሊዝምን ወጥፋቱ አንዳለሆነ፤ቀበሮቿ ወበቶ ቾን ገና ደሀን ፀረ-ቀበሮቿ አገዛዝን በማበረታት ላይ እንደሆነ፤በተራማጆች ላይ የሚ ያደርገውን ዘጆና ማበረራር ያጎየቀጠለበት እንደሆነ፤በአርትራና በሌሎች በገር ላይ ያለ ው ፖለቲካ ፍላጎ አደዋሪ እንደሆነ ለማሳየት የወጣ ወገለጫ ነበር::

ለማጠቃለል፤በለተገደሉት ሰዎች በተጠመደ ወገለጫ ላይ ሆነ በቲሳገራው ባቢያ ከፊዳሬሸኑ አካባቢ በማህበራቸን ላይ የተደረገው "የማጋለጥ አርምጃዎች" በኢትዮጵያ ጽኑ ተራማጆች ፊት ማገን የበለጠ እንደሚያጋልጡ ለመረዳት ቀላል ነው::በኢትዮጵያ ውስጥ ባሉት ወሰበበበ የፖለቲካ ጉዳዩች ላይ አተኩር በፈ ያሉ አስተያየቶች አየሰጠ በፊውን ተማሪ ለሬሽሉኑ ማዘጋጀትን እንደዋና አላማው የሚወስደው ማህበራችን ከንግዲህ በነዚሁ ነጥቦች ላይ አደመለስባቸውም::የፊዳሬሽን ወሪዎችንም፤በወሰበሰቦች ያገራችን ፕርበሎች ላይ የምንወስናቸውን የ"ገወን ከበርቴ አቋማችን" ከ"ወዘደራዊ"ርእ የተባለባቸሁ ተነስ ታቸሁ በተተቹባቸው ጊዜ ነበር፤ይህም ካለሁናቸሁ በለቲሳገራው ወዘተ. የመሪዎቻችሁንን ማጋ ለጥ በርቱ የጥላቻ፤በመጨረሻ ማገ አንደሚጋልጥ በፊው ተማሪ የኢትዮጵያ ሕዝቦች ትገል ያስየናል እንገለጥልን::



1945

ZCZC 32Q
KOELN/17 31 23 192Q

23/9/74


ESUE AMARE 8Q RUE DE PARIS
(913QQ)MASSY/ESSONNEFRANCE

ARB SEPTEMBER 27 BEMELAW ALEM YETEQAWMO SELF STOP
SLOGANOCH VETADERAWI MENGIST AMIFELIGIM SIZIAWI MENGIST
YIQUAQWAM REPUBLIK YITAWEJ YENEGUSUN MEWDEQ ENIDEGIFALEN
TEQAWMO LEDERGU LAKU
FEDERATION

COL 8Q 913Q OCT 27

NNNN
25430Z PALAIS F
25383A VIRY F

0


Deutsche Bundespost
Telegramm
aus Berlin 123
Aufgabe-Nr. 3026 — Wortzahl 27 — Aufgabetag 12.9.74
Datum 12.9.74
Gebührenpflichtige Dienstvermerke = ELT
ARMED FORCES COORDINATING COMMITTEE
BOX 5207 ADDIS ABABA
ETHIOPIE
We hail tyrant Haile Selassie's deposition
DEMAND abolition of monarchy
URGENT implementation of democratic rights
Down with feudalism imperialism
ETHIOPIAN STUDENTS UNION IN EUROPE
Die Abschrift des Telegr. Nr. 3026 wird hiermit bescheinigt
20 DM 25 Pf
3 DM — Pf
23 DM 25 Pf



ከዚህ የሚቀጥለው ጽሁፍ ከብሪታንያ ቅርንጫፍ ማህበር የተላከ ነው፡፡በኢትዮጵያ የየካቲቱ ሕዝባዊ አብዮታዊ ንቅናቄ ከፈነዳ ጀምሮ፣በኢትዮጵያ ተማሪዎች ንቅናቄ ውስጥ የተጀመረው ሬቮሉሽናዊ ትግል እንዴት ይቀጥል?፣የጊዜው አጣዳፊ ተግባሮች የትኞቹ ናቸው?፣ተቀዳሚ የትግሉ ጥያቄዎችስ የትኞቹ ናቸው? በሚሉትና በመሳሰሉ የሬቮሉሽኑ ጥያቄዎች ላይ ከፍተኛ ልዩነቶችና የፖለቲካና የርእዮተ ዓለም ትግሎች ታዩ ተዋለ፡፡ልዩነቶች እየተጋጋሉ የሄዱት የኢትዮጵያ ሕዝቦች ትግል የሚያነሳቸው ጥያቄዎች የበለጠ ተጨባጭ እየሆኑ ስለመጡ ነው፡፡ የሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ የጭቁና ምንጭና ስለዚህም የኢትዮጵያ ሬቮሉሽን አብይ ጥያቄ የሆነው የመሬት ጥያቄ ነው፡፡በዚህ አብይ ጥያቄ ላይ የሚወሰዱ እርምጃ አንዱ መደብ ወይም ድርጅት በኢትዮጵያ ሬቮሉሽን ውስጥ የሚኖረውን ቦታ የሚወስን ጥያቄ እንደመሆኑ፣የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበራት መሬት ላራሹን በሚያፀድቀው የቀርጡ የመሬት አዋጅ ላይ የሚወስዱት እርምጃ ዛሬ በኢትዮጵያ ባለው የመደብ አሰላለፍ የት እንደቆሙ የሚያሳይ መስታወት ነው፡፡ይህን አዋጅ በረቂቁ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ የሚቃወሙ፣በሌላ ሌላ ሰበብ ሥራ ላይ መዋሉን የማይፈልጉ፣የመሬቱን አዋጅ ሥራ ላይ እንዳይውል ከሚጥሩ ኃይሎች ጋር የሚተባበሩ፣ለአዋጁ ሥራ ላይ መዋል እንቅፋት የሚሆኑ መሪ ቃሎችን የሚወረውሩ ሁሉ ከኢትዮጵያ ሬቮሉሽን በገቡበት የወሰዱ ብቻ ነው፡፡

በሌላው ወገን፣ይህ አዋጅ ያለምንም ገደብ ሥራ ላይ እንዲውል፣ (የሚፈልጉት) የአዋጁን መንፈስ የሚያረጉ ወይም ሥራ ላይ መዋሉን የሚያደናቅፉ እክሎች ሁሉ እንዲወገዱ የሚታገለው፣ የተገኘው ድል ሳይቀለበስ ትግሉ ቀጥሎ ወደአዲሱ ዲሞክራቲክ ሬቮሉሽን እንዲሸጋገር የሚጥረው ደግሞ በኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ ጎን የተሰለፈው ነው፡፡የብሪታንያ ማህበር በዚህ ውሳኔው ከሰፊው ሕዝብና ከኢትዮጵያ ሬቮሉሽናዊ ኃይሎች ጎን የሚያሰልፈውን እርምጃ ወስዷል፡፡

ለአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር ፣ ፓሪስ 27/4/75

## ስለመሬት አዋጁ በብሪታንያ የለንደን ቅ/ማ/ የተሰጠ መግለጫ

ሰፊው አርሶ አደር የኢትዮጵያ ህዝብ በአብዮታዊ የደም ሥርና በሀብረቱ ጠባቂ እንሰሳ የሀብቱና የስተናው የሆነው ፣ ለአንቱታውና ለአብአዊ ሰሆነ ዐመጽና ገፍ የተነጠቀውን በየጊዜው በየቦታው በቆራጥነት ሲታገለት ሰጠሬጠፍበት ፣ ደሙን ሲያፈስለትና አጥንቱን ሲከሰክስለት የኖረውን እንደዚሁም ከሱ አብራክ ተከፍለው የወጡት ልጆች ተማሪዎች ከአሥር ዓመታት በላይ የአብዮታዊ ትግላቸው መቀጸም በማድረግ እንደመሪ ቃል በማንሳት ባልተቋጠበ አንደበት ጥሪያቸውን ሲያስተጋቡት መክራና ሰቆቃ ደ፣ እሥራትና ግርፋት የተቀበሉትን ፣ ከዚያም በላይ በመረሸን እስከመጠረግ መስዋዕት የሆኑለትን ፤ ይህ የካቲት 25/67 ዓም የታወጀውን ˙ የገጠርን መሬት የህዝብ

በለማድረግ ፡ የሚለውን ተራማጅ ኢትዮጵያውያን የምንፈታውና የምንቀበለው መራራው የሰ
ፊው ሕዝብ ትግል ያፈራው ውጤ ነው ፡፡

በሰፊው የኢትዮጵያ ጭቁን ሕዝብ ፣ ለአያሌ ዘመናት መሬት ለአራሹ፣ አገ
ራችን ከኢምፔሪያሊስቶች የባህል ፣ የኢኮኖሚና የፖለቲካ ተጽዕኖ ነፃ ትውጣ ፣ መሠ
ረታዊ የሕዝብ ዴሞክራቲክ መብቶች ይከበሩ ፣ በተከታታይ ዓመታት ትግሎች ሥር በመሰለ
ፍ ሲታገል የቆየ መሆኑ ይታወቃል ፡፡ስለዚህም ይህ የወጣው የመሬት አዋጅ አብዮታዊ
ትግሉ የወለደው ውጤትም ከታበት አንዱ ምዕራፍ ሲሆን የተገኘው ውል በአዋጅ ብቻ ተ
ገጠለምሉ እንዲቀር እንደዚሁም ወሳሰብ ባነበቡ በተቀረፁ አብዮታዊ ትግሎቻችን ዘለ
ቄታ ለውጥ በማምጣት ሙሉ ውል እስከተገኘበት ድረስ በገሥጋሤ ላይ መራራው ትግሉ
አይክተምም ፣ ይቀጥላል፡፡

የመሬት ጥያቄ የኢትዮጵያ ሕዝቦች አብዮት ቁልፍ ሆኖ ገቢረን ፣ ቀጥር
ገበረውን ሠራተኛውን ፣ ተማሪውን ምሁሩን ተራውን ወታደር ወዘተ. ባንድ ፊት መሰና
ንቀን ፣ ባለመሬቱንና የገዢውንፍል በሌላ ወገን ፣ ማለትም ገዥና ተገዥን ፣ ጨቋኝ
ና ተጨቋኙን ፣ የጨቋኝ ወገንና የተጨቋኝ ወገንን በመደብ ለይቶ ከፍ ያለ መ
ደብ ትግል የተካሄደበትና የሚካሄድበት ጥያቄ ነው-፡፡

በብሪታንያ የለንደን ውስጡ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር ይህ አዋጅ
አልፎ አልፎ አንዳንድ ቀዳዳዎች የሚታዩበት ቢሆንም በየካቲት ሕዝባዊ እንቅስቃሴ የ
ተዘጋውን የፊውዳል ሥርዓት በይበልጥ ሊያርደውና የፊውዳሉን ሥርዓት ቆንዘት የአሜሪ
ካን ኢምፔሪያሊዝም የሚያስበረግገው መሆኑን በማመን ፣ በተለይም ደግሞ አሁን በአ
ገር ውስጥ ያሉ አድሃሪ ሃይሎችና የሥልጣን ለጋሙን ከያዘው ነዑስ ከበርቴ ጋር ያለ
ውን የመደብ ቅራኔ ገለፃለፃ አይርን የሚያወጣና የተገለሉን ደረጃ ከፍ የሚያደርግ አ
ርካሽ መሆኑን በመገንዘብ ፣ የአዋጁን ዓምደ ሃሳብ ማህበራችን እየተቀበለ፣ የምንጠ
ቁማቸውን ጉድለቶች ለሟሟላትና ያሉብትን ቀዳዳዎች በመድፈን በሥራ ላይ እንዲውል ይ
ጠይቃል ፡፡ ይህንንም ለማድረግ ባገር ውስጥ የሚገኙ ተራማጅ ኀይሎች ፣ ሕዝባዊ ማ
ህበሮች የእድገት በህብረት ዘማቾች በጠቅላላ ገበር ቀድም በመሆን የተሰለፉ ሃይሎ
ችና ድርጅቶች ሁሉ በይበልጥ በጠነከረ አብዮታዊ ትግል አዋጁ በሥራ እንዲተረጎም ከ
ሰፊው ሕዝብ ጋር እንዲተባበሩና እንዲሁም አብዮታዊ ግዴታቸውን እናሳስባለን ፡፡

ሀ/ የመሬት ነገር ሲነሳ ፣ ተንገዋሎ ሊታይ የማይችለው ከዲሞክራቲክ
ጥያቄዎች አንዱ የብሄር ጥያቄ አብሮ ይወሳል ፡፡ ስለዚህም መሬት ለአራሹ በደለደለ
በከፍተኛ ጥንቃቄ እንዲሰራ መጠየቅ ይገባ በመሆኑ ነው ፡፡ የሚደጋፉት የገበሬ



ማህበራት መሬትን መደልደል የማስተካከልና የማስተዳደር መብት ሙሉ በሙሉ የነሱው
ነው ፡፡ የነሱው ነው ስንል የራሳቸው የሆነውን በራሳቸው መወሰኑ ዕድል የገላቸ
ው መሆኑን በጥበቅ ለማስገንዘብ ነው ፡፡ እንዲሁም የብሄር ጥያቄ በመሬት ሁኔታ
ና ይዞታ በንፈታው ፣ መሬት የማግኘት መብት በአንዱ ከፍለ ሃገር የሚኖረው የአንዱ
ብሄር ሰፊው ጭሰኛ ገበሬ በቀደሚያ እሱ ሳያገኝ በሰው መሬት ላይ ከሌሎች ብሄሮች
እንዲሞጡ ማስፈር ማለት አይደለም ፡፡ ለምሳሌ በአርሲ ብሄር ላይ የአርሲው ሰፊው
ደሃ ገበሬ ሳያገኝ ከአማራው ብሄር የመጣውን አርሶ አደር አምጥቶ ማስፈር ፈጽሞ የ
ተከሰተ ድርጊት ከመሆኑም በላይ ፣ ወለቀ በለን በንመረምረው የጊዜው እንገባጋቢና
አጣዳፊ የሆነውን ጥያቄ ፣ እንዳልነበረና እንደሌለም በማስመሰል ሽፋፍኖ ደባበሶ
ስለሚያልፍ ነው፡፡

ለ/ በአዋጁ ከታዩት ጉድለቶች መካከል አንደኛው የገበሬ ማህበራት የ
ሚደገሙበትን ሥርዓት ይመለከታል ፡፡ ይህ የመሬት አዋጅ ወጥቶ ያለበት ወሳኝ ፣
ሰው ሆኖ በሰው ጫማ በረገጥ ፣ አምርቶ ሲያበስል ፣ አሰብቶ ሲያቀርብ ቆይረውን ፣
ሰውነቱን በነበረው ሥርዓት እንዲረባ የተደረገውን በፊውዳሊዝም ሥርዓት ተገጠ ተለጥ
የተከሳውን የደሃ ገበሬ ቆራል ለማንቃት መሆኑ ሲታወቅ ከእንግሊዝ ወዲህም ,ባካባቢ
ው ያሉትን የፊውዳል ከበርቴ ርዝራዦች ወርስ እንዲያወድሙቸው ማንቃትና ማስታጠቅ መ
ሆኑ ሲታወቅ ፣ መብቱ ካለተነካ መለስተኛ ይዞታ ካለው ባለመሬት ጋር ተመሰስ ማህበ
ር እንዲያደርግ ማድረግ ተከሳውን ለምድ አለበስ ከበጎች ጋር እንደመደባለቅ ቀጥረነ
ዋል ፡፡ የታሠረበትን ሰበር ፣ ሰውነቱን አውቆ ጠላቱን ለይቶ እስከወቀበት ጊዜ -
ድረስ ሰፊውን ደሃ ገበሬ ፣ የቀጥር ገበሬ ፣ ጭሰኛ ፣ መሬትና መተዳደሪያ የሌለው
ን ሥራ አጥ ሠራቶት ለብቻዉ ማስተማር ማንቃትና ማደራጀት የጊዜው ዓይነተኛ አብዮታ
ዊ አርምጃ ነው፡አንላለን ፡፡ "የሰንከፈ መነቀስና" ..... "የዐንበው መድረቅ"
አምኑ ላይ ነው ፡፡

ጠ/ ከዚህም ተያይዞ ሊታይ የሚገባው ፣ በገበሬዎች ማህበር የፍርድ
ሸንጎ አደጃጀም ጉዳይ ነው ፡፡ ከየካቲት እንቅስቃሴ በፊት ከዚያም በኋላ አሁንም ወ
ደፊትም ከፍተኛ ሕዝባዊ አብዮት በመካሄዱ እንደነበረ ፣ በመካሄዱም ላይ መሆኑን የ
ሚጠየቅ አይመስለንም ፡፡ እስከአሁን የአብዮቱ በለፈኞች ሠፊው ሠራተኛ ገበረው ምራ
አጡ ፣ ተማሪው ቁሉ ሽኩ ወታደሩ ምሁሩ ተራማጅ ንዑስ ከበርቴው ወዘተ ሲሆኑ አሁን
ግን ንዑስ ከበርቴው የተገሉን የማፍሪያ ማምረቻዎችን እጅ ውስጥ አስገብቶ የስልጣን
ወንበር ላይ ከተቀመጠ በኋላ ተደላድሉ ሥር በመስደዱና ዕድሜውን ለማራዘም የረቀቁና

ከምእራብ የፈለሰ የበር ሥርዓትን በማንበራፋትና ይዞታውን በማጠንከር ላይ ይታያል ።
የዚህ ምልክት እኳ በርዓት ዝብሉ በተነገረው በገበሬዎች ማህበር የአውራጃና የወረ
ዳ የፍርድ ሸንጎ ላይ የበላይ ወሬነትን የአስተዳደር / የመዝገብ አያያዝ ይለዋል/
ባለስልጣንነትን ወምድድ ወያዙ ነው ። የመደብ አሰላለፍ ለየ ። የሰፊው ህዝብ
ትግል በበለጠ ኀይል ይቀጣጠላል ። አሁን ተያይዟል ። በበለጠም ይነዳል ። ሌላ
በርቱትና ሊያጠፉት የሚሞክሩትን ወገኖችም ያጋልጣቸዋል ። ታሪክ እንዳይደገም እ
ንደዚህ ዓይነት የአኗ ለወቀለ ክሁሉ አርፈህ ተቀመጥ ዝንቡ ተበርዞ ህዝቡ ራሱን በራ
ሱ እንዲያደርግ እንዲያስተዳድር እንዲመራ እንዲደረግ እንጠይቃለን ።

ባጭሩ ይህን ለማጠቃለል ያህል ከዚህ በላይ ከአየኹ ጠቅ በማውጣ
ት ተገትነን ለማሳየት የሞከርናቸውን መሠረታዊ ጉዳዮች ለብ በለን ያናጠናቸው በኢ
ትዮጵያ ህዝቦች መካከል ነባራዊ የሆነውን የመደብ ቅራኔን በመዝለል፣መደብ የለሽ ህ
በረተሰብ የተገነባ ይመስል ሁሉን ባንዴ ዐከል ለማድረግ ይሞክሩ ። የሰፊውን ህ
ዝብ አብዮታዊ ትግል የዘገበ መልክና ትርጓሜን በመስጠት ሊያጠምዱና ሊቀንዱሉ በሰዊ
ችሎም የተጠየቁት ጉዳዮች በቀጥታ ታርመው ይህ የሰፊው ህዝብ የአያሌ ዘመናት ትግል
ውጤት የሆነውን አዋጅ በፍጥነት በተግባር እንዲተረጎም አሁንም ወደፊትም ደጋግመን
የምናስጠው ጽኑ ጥሪያችን ነው ።

መንግሥታችን የምናጠቃልለው አስካሁን በህዝብ ድል የተገኘውን ድል
በማጠናከር አብዮታዊ ትግሉን በማፋፋም በእውነተኛው ህብረተሰባዊነት /ሳይንቲፊክ ሶ
ሻሊዝም/ ፍልስፍና ጥላ ሥር አንዲት ኢትዮጵያን እንደገና መገንባት ይቻላል በሚ
ለው ጥያቄ ነው ። እንግዲህ ህብረተሰባዊት ኢትዮጵያ የምትገነባው ህዝቦቿ እንዲ
ደራጁና መብታቸውን እንዲያስከብሩ ፣ ለመናገር ለመጻፍ እንዲችሉ በማስተማርና በመማ
ር እንዲነቁ እንዲያነቁ የህብረተሰባዊነት አቋም መሠረት የሆኑትን ሰፊው ህዝብ የ
ታገለላቸውን የሰው ልጅ መሠረታዊ ዲሞክራሲ መብቶች አለማክበር መሆኑን ሲታወቅ ከ
ጥበት ሁኔታው ገና የምንረዳው ያላሰበነውና ያልጠበቅነው ሆኖ አግኝተነዋል ። አበ
ው ሲቲር ቶ ቃግም ሺህ ቢታሰብ ያው በገሌ አላቸ ልጆት እንዳሉት ምንም ህብረተሰ
ባዊነት ባለፈ ከደርጉ ወደ ዝንፍ ። ይህ የኢትዮጵያ ህዝቦችን ትግል ወደ ከፍተ
ኛ መራራነት ደረጃው የሚያደርሰውን፣ በዙ ህዝብ ያስወረሰውን አሁንም በማስወረስ ላይ
ዘር
ያለውን የሰውን መብት የሚገፈውን ፀረ ዲሞክራሲ አርምጃ በህዝብ ላይ የተደረገባቸ
የሚደረገን ዐመጽ አጥብቀን እንቃወማለን እናወግዛለንም ።

ማህበራችን እስካሁን ያወጣቸውና የደረሰባቸውን ፀረ ዲሞክራሲ ድር
ጊቶችን ባጭሩ ከዚህ ቀጥለን በመዘርዘር ጥያቄያችን እና ቁርጣችን መፍትሄዎቻችንም እና
መለስታን ።



1ኛ/ ጊዜያዊው የወታደር አስተዳደር መስከረም 2/67 ዓም ያወጣው ፀረ
ዲሞክራሲ አዋጅ የሰፊውን ህዝብ ነፃነት ከመገፈፉም በላይ በተለይ ለሰፊው ህዝብ
የቆመውን ተራማጅን ክፍል ሆነ ብሎ ለማጥቃት የታወጀ በመሆኑ በአስቸኳይ እንዲነሳ

2ኛ/ ዲሞክራሲ ሕዝባዊት ኢትዮጵያ የምትገነባው በመጀመሪያ በውስጧ የሚ
ኖሩት ሕዝቦቿ ልዩ ልዩ ብሄረተኞች መሆናቸውን በማመን ቢሆን፣ይህን ባይቀበሉ በ
ኃይል እንገነባለን ብሎ መነሳት በድጡማት ላይ ቤት እንደመሰራት መሆኑን እየሰገነዘ
ብን እንዲት ኢትዮጵያ ለመገንባ የምትችለው በነዚሁ በውስጧ የሚገኙት ብሄሮች በመፈ
ቃቀድና በመተሳሰብ፣በእኩልነት በመተባበር አብሮ ለመኖር ለመኖር ሲችሉ ብቻ መሆኑ
እየታወቀ፣ተርገም የለሽ አንድነት በኃይል ለመፍጠር መሞከር ከንቱ ነው።።ይህንንም
በንል ለምሳሌ በቀርጡ በኤርትራ ሕዝቦች ላይ የተፈጸመውን አስከፊ ድርጊት ያስታውሳ
ል።።የኤርትራ ጥያቄ እንደሌሎው የብሄር ጥያቄ ባይገባቸው ተገቢና በመከተል መብትን
በማወቅ መፍትሄ በሰላማዊ ሊገኝ ሲችል ኃይል በመጠቀም የሰላማዊ ሕዝብን ነፍስ ደም
ማፍሰስ፣ንብረትን ማጥፋት፣ሰፊውን የኢትዮጵያ ሕዝብ በኤርትራ ሰፊ ሕዝብ ላይ ቅራኔ
እንዲኖረው በጎርጅጋገዱ ማወናበድ፣በረሃብ በመቀላቀት፣በበሽታ በመሰቃየት፣በጭንቀትና
ታጋር ያለን ህብረተሰብ ህብት በጦር መሳሪያ ገዥ በማከከንና የአምፕሪያሊስቶች የ
ሸቀጥ አገር መሆን ፍጹም ፀረ ዲሞክራሲ ድርጊት በመሆኑ እያወገዝን፣ድርጊቱ በአስ
ቸኳይ እንዲቆም እንጠይቃለን።።

3ኛ/ከዚህ አያይዘን የምናነሳው በየጊዜው የተገደሉትና የታሰሩትን የሰፊው
ሕዝብ ወገኖችን በረዥም ጊዜ ትግል በተማረው በሰራተኛው በወቀሳው ከሰፊው ሕዝብ ተው
ጣጥተው በፀረ ፊውዳሊስት ፀረ ኢምፔሪያሊስት ጥላ ሥር ተሰልፈው የአብዮት ተካፋይ የነ
በሩትንና አሁንም እንዳይበሩ በኃይል የተከለከሉትን የተማሪ የሠራተኛ ወዘተ. ማህበ
ጉዳይ ቢሆን፣እነዚህ ማህበራት
ራት ዲሞክራሲ መብታቸው ተጠብቆ ሥራቸውን እንዲቀጥሉ እንዲደረግ እንጠይቃለን።።

4ኛ/ የሰፊውን ሕዝብ ጥያቄ በማስተጋባት ከወዛደሩ ጋር በመሰለፋቸው የተ
ገደሉትን የሌሎች ልዩ ልዩ ወታደርና ሠራተኛ ክፍሎች ያለፍርድ መገደል በተለይም7
1.ሻለቃ በላይ ፀጋዬ፣2.ደምሴ ቢፈራው፣3.ወለደ ዳዊት ዘርጋው፣4.ኤን ሲ በቀለ
6
ወልደጊዮርጊስ፣5.ሲፒያርን ተስፋዬ ተክሌ፣ኝንየር አር.ከ. ዳዊት ፍትዊ፣7.
ሰርጀንት ሜጀር መንግስቱ አበ ኃይሌ፣8.ኮርፖራል መኩንን ካሳ፣9.ባሰው ኃ.ሚካኤል
10.በርሄ ዱቄ ፼፣11.ወልደሚካኤል ከበደ፣12.ረከሱ ቢዳኒ፣ገብረ ሥላሴ፣17.
ተማሪ መለስ ተክሌን መገደል በጥብቅ እናወግዛለን።።ባለተገለጸ ጥፋት ተዘዞው በእም
ራት ላይ በመማቀቅ የሚገኙትን ተራማጅ ምሁራንና የሰፊው ሕዝብ ወገኖች በጠቅላላ፣

በተለይም ማንነታቸውን ለይተን እስካሁን የደረሰንባቸውን
1.ዶር.አበቶ ሞላ ፣2.አቶ ፋሲል ደማሱ፣3.ተማሪ አበባ ምትኩ
ወታደር አያወገዝን ያለአገባብ የተገረፉትን ነፃነት በለሰቸዉ እንዋለለሳቸው እየ
ጨ የቀገ፣በማገናዎም ደረጃ በወታደርም ሆነ በሲቪል ክፍል ለነኚህ ዶክተሮች ኃላፊ የ
ሆኑ ሁሉ በሕዝባዊ ሸንጎ ቀርበው ፍርዳቸውን እንዲቀበሉ አጥብቀን እንጠይቃለን::

- የወጣው አዋጅ በተግባር ይዋል
- የደርጉን ፀረ ዲሞክራቲክ እርምጃዎች እናወግዛለን
- የበ ሄሮች አከላነት ይታወቅ
- የመደራጀት/ የፖለቲካ ፓርቲዎች መመስረት/መብት ይረጋገጥ
- የታሰሩት ተራማጆች ይፈቱ
- ድሉ የሰፊው ሕዝብ ነው

ማህተም/ኢትዮጵያን በተደንተሰ ቆኔዮን
ኢን በሬቴን/